በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
የባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ

የቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክ ዳር ድንበርን ለማስፋት የጎላቴና ታቦር ተራራዎች ወደ ጥብቅ ስፍራዉ የመግባት አቅም፤ የየጎፍና የወለቃ አባይ የተፈጥሮ ደኖች ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም የመጀመሪያ ደረጃ የዳሰሳ ጥናት

ደቡብ ወሎ

በልስቲ ፈጠነ
ግዛቸዉ አላምረዉ
ዮሴፍ ሃይለስላሴ

የዱር እንስሳት ጥናት፤ልማት፤ ጥበቃና ዐጠቃቀም ዋና የስራ ሄደት

ባህዳር የካቲት 2003 ዓ.ም

1. መግቢያ

በክልሉ የሚገኙ በርካታ የደን ክልሎች ለረጅም ዓመታት በሰዎች ተፅዕኖ ውስጥ ሆነው ቆይተዋል። መሬቱና በውስጡ የሚገኙ ሌሎች የተፈጥሮ ሐብቶች በከፍተኛ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ በክልሉ 4 ብሄራዊ ፓርኮች ያሉና ይህም በIUCN መስፈርት መሰረት ከጠቅላላው የመሬት ስፋት 10 ከመቶ መሸፈን ያለበት ቢሆንም እነዚህ ጥብቅ ስፍራዎች ከጠቅላላ የክልሉ ቆዳ ስፋት የሚሸፍኑት 2 ከመቶ ብቻ ነው። ከዚህ አንፃር በቀጣዮቹ 5 ዓመታት በክልሉ ያሉ የጥብቅ ስፍራዎችን ቁጥር ከ4 ወደ 11 በማሳደግ በክልሉ የሚገኘውን ወካይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህዳር መጨመር ከስትራቴጅክ ዘመኑ የተቋሙ ቁልፍ ግቦች አንዱ ነው። ስለሆነም ተቋሙ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት አንዱ በክልሉ ውስጥ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ያለቸውን የተፈጥሮ ደን ቦታዎች በአለም የተፈጥሮ ጥበቃ ሕብረት (IUCN) መስፈርት መሠረት በማጥናትና በመከለል ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ማስቻል ነው።

በአለፉት ዓመታት ተቋሙ በአደረገው ከፍተኛ ጥረት የአላጥሸና ቦረና ሳይንት ብሔራዊ ፓርኮችን በማጥናትና በመከለል ህጋዊ ሰውነት ይዘው በአዋጅ እንዲቋቋሙ እና በሰው ኃይልና በፋይናንስ በማጠናከር ራሳቸውን ችለው እንዲተዳደሩ አድርጓል። ከዚህ ሌላ በውስጡ የሚገኙት ብርቅየ የዱር እንስሳት ለመጥፋት በመቃረባቸው የተነሳ በቀይ መዝገብ ዝርዝር (Endangered Red List of IUCN) ውስጥ ገብቶ የነበረውን የስሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ አስፈላጊውን የሰው ኃይልና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ ዛሬ ለሚገኝበት ጥሩ ደረጃ ማብቃት ችሏል። በተጨማሪም የመንዝ ጓሳ እና የባኩሳ ማሪም ታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች በቅርቡ የማቋቋሚያ አዋጃቸውና ደጋፊ ሰነዳቸው ተጠናቆ በቅርቡ ህጋዊ ሰውነት ያገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ስለዚህ የክልሉን ወካይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህዳር ለማሳደግ በደቡብ ወሎ ዞን የቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክን ለማስፋፋት በሳይንት፣ ለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኝውን የታቦርና ጎላቴ ተራራዎች አካባቢ፣ በወግዲ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የወለቃና አባይ ሸለቆች የተፈጥሮ ደንና በደሴ ዙሪያና አልብኮ ወረዳዎች እንዲሁም በደሴና ኮምቦልቻ ከተሞች ውስጥ የሚገኘውን የየጎፍ የመንግስት ጥብቅ ደን ማጥናት ተቋሙ በዚህ ዓመት ለመስራት ከያዛቸው ተግባራት መካከል አንዱ በመሆኑ የእነዚህን ቦታዎች ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅማቸውን ለማረጋገጥ የሚስችል ጥናት ከጥቅምት 5 እስከ ህዳር 5/2003 ዓ.ም በመስክ በመገኘት ጥናት ተካሂዷል።

በመሆኑም በዚህ የጥናት ሪፖርት ከዳሰሳ ጥናቱ የተገኙ የተሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ዝርዝር ተፈጥሮዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ሃብቶች፣ ስርዓተ ምህዳር ዓይነትና ሁኔታ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች፣ ቁልፍ ችግሮች እና ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅማቸውን ለማረጋገጥ የሚስችሉ መረጃዎች ተካተዋል።

ስለሆነም ከጥናቱ የተገኙ መረጃዎችን እና የIUCN ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መገምገሚያ መስፈርቶችን በመጠቀም ታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎቹ በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ ሊመደቡ እንደሚችሉ አማራጮችን በማሳየትና ሊያሳኩ የሚችለቋቸውን ዓላማዎች በመጠቆም እንዲሁም ወደ ፊት መከናወን ያለባቸውን ስራዎችና የባለድርሻ አካላትና የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶችን ተግባርና ኃለፊነት በመለየት ውሰኔ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል።

2. ጥናቱ የተካሄደባቸው ቦታዎች አጠቃላይ ሁኔታ

2.1. ጥናቱን ለማካሄድ የተመረጡ ቦታዎች፣ መገኛና ስፋት

የጎላቴና ታቦር ተራራዎች የተፈጥሮ ደን

የጎላቴና ታቦር ተራራዎች የተፈጥሮ ደን የቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክ ዳር ድንበርን ለማስፋፋት በዚህ የዳሰሳ ጥናት ትኩረት ተሰጥቷቸው ከተዳሰሱት ቦታዎች መካከል የመጀመሪያው ሲሆን የሚገኘውም በደቡብ ወሎ ዞን በሳይንት፣ ለጋምቦ፣ ቦረና እና ተንታ ወረዳዎች ውስጥ ከፓርኩ ጋር ተያያዥ የሆኑ እና በተፈጥሮ ሀብት ይዘታቸው፣ በስርዓተ ምህዳራዊ ጠቀሜታቸው እና ተፈጥሮዊ አቀማመጣቸው ለዱር እንስሳት መራቢያ፣ መመገቢያና መጠለያ አመቺ በሆኑ አካባቢዎች ነው። እነዚህ ወረዳዎች በመካከለኛው አማራ የልማት ቀጠና የሚገኙ ሲሆን የዞኑንም ሆነ የልማት ቀጠናውን ከፍተኛ ቦታዎች አካተው የያዙ ናቸው።

በመሆኑም የተፈጥሮ ደኑ በአጠቃላይ በ18 ቀበለዎች (ከሳይንት 8፣ ከለጋምቦ 7፣ ከተንታ 2፣ ከቦረና 1) ወስጥ የሚገኝ ሲሆን ከ20000 ሄ/ር በላይ ስፋት ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል። ይህ ቦታ ከቦረና ወረዳ ጭሮ ቃዲስ (031) ቀበሌ ከፓርኩ ድንበር ተነስቶ እስከ ተንታ ወረዳ ጋያ (027) ቀበሌ ልዩ ስሙ ተሪ እና ለጋምቦ ወረዳ ጠሙ (027) ቀበሌ ልዩ ስሙ መርከብ አፋፍ ድረስ በግምት ከ$10^0$22’02” እስከ $10^0$32’31" ሰሜን ላቲቲዩድና ከ$38^0$27’51" እስከ $38^0$34’49” ምስራቅ ሎንግቲውድ ላይ ይገኛል።

የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን

የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን በዚህ የዳሰሳ ጥናት ሊታዩ ከተመረጡት የተፈጥሮ ደን ቦታዎች መካከል ሁለተኛው ሲሆን የሚገኘውም በደቡብ ወሎ ዞን በወግዲ ወረዳ የወለቃና አባይ ሸለቆዎችን ተከትሎ ነው። ወረዳው በደቡብ ወሎ ዞን በምዕራብ ጫፍ የሚገኝ ሲሆን በመካከለኛው አማራ የልማት ቀጠና ከሚገኙ 31 ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ነው። ወረዳው ከአዲስ አበባ 584 ኪ.ሚ፣ ከባህር ዳር 619 ኪ.ሚ፣ ከደሴ ደግሞ 184 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል።

የተፈጥሮ ደኑ በዋነት በ7 ቀበሌዎች (013፣ 015፣ 016፣ 017፣ 018፣ 026 እና 034 ቀበሌዎች) ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከ15000 ሄ/ር በላይ ስፋት ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል። ይሁን እንጅ በጥናቱ ወቅት ባናረጋግጥም ከዞን ግብርናና ገጠር ልማትና እንዲሁም ከአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ በአገኘነው መረጃ መሰረት የተፈጥሮ ደኑ ሳይቆራረጥ እስከ ከለላ ወረዳ ድረስ እንደሚቀጥል ይታመናል። በተጨማሪም በ1993 ዓ.ም አቶ ጫኔ ገበየሁ ለሁለተኛ ድግሪ ማሞያ በዚህ አካባቢ በ4 ቀበሌዎች ላይ (013. 015 እና 034 ቀበሌዎችን ሳይጨምር) ባደረጉት ጥናት የተፈጥሮ ደኑ ወደ 8245 ሄ/ር ስፋት ሊኖረው እንደሚችል ገምተዋል። ከዚህ ውስጥ 3478 ሄ/ር የሚሆነው የተፈጥሮ ደኑ ከ1100 እስከ 1500 ሜ ከፍታ የሚገኝ ሲሆን 4767 ሄ/ር የሚሆነው ደግም ከ1500 እስከ 1800 ሜ ባለው ከፍታ ውስጥ ይገኛል። በተጨማሪም 42 ከመቶ የሚሆነው የደን ሽፋን ለእጣንና ሙጫ ምርት አገልግሎት ለሚውሉ ሀገር በቀል ዕፅዋቶች (*Boswellia papyrifera* and *Commiphora africana*) ተፈጥሮዊ መኖሪያ ቦታ እንደሆነ ታውቋል። ይህ ቦታ 013 እና ከፊል 015 ቀበሌዎችን ሳይጨምር በግምት ከ$10^0$22’02” እስከ $10^0$32’31" ሰሜን ላቲቲዩድና ከ$38^0$27’51" እስከ $38^0$34’49” ምስራቅ ሎንግቲውድ ላይ ይገኛል።

የየጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን

የየጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን በዚህ የዳሰሳ ጥናት በደቡብ ወሎ ዞን ሊታዩ ከተመረጡት የተፈጥሮ ደን ቦታዎች መካከል ሶስተኛው ሲሆን ከቃሉ ወረዳ፣ ኮቦልቻ ከተማ፣ ደሴ ከተማ፣ አልብኮና ደሴ

ዙሪያ ወረዳዎች ጋር ይዋሰናል። ይህ ደን በአጠቃላይ ከ8 ቀበለዎች (ከደሴ ዙሪያ 4፣ ከኮምቦልቻ 2፣ ከአለብኮ 1፣ ከደሴ ከተማ 1) ጋር የሚዋሰን ሲሆን ጠቅላላ ስፋቱም ከ13000 ሄ/ር በላይ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

ዮጎፍ በሰው ልጅ ጥረት ወደ ተፈጥሮዊ ሁኔታው የተመለሰ በመሆኑ በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ላይ ላሉና ወደ ተፈጥሮዊ ይዘታቸው መመለስ ለሚኖርበቸው አካባቢዎች እንደ ሰርቶ ማሳያ ሊወሰድ የሚችልን ስርዓተ ምህዳር የሚወክል ደን ሲሆን የሚገኝውም ከደሴ ከተማ ቀበሌ 015 ጋር ከሚዋሰነው የሐረጎ ደን እስከ ደሴ ዙሪያ ወረዳ 09 ቀበሌ ጫፍ ድረስ በግምት ከ$10^0$22’02” እስከ $10^0$32’31" ሰሜን ላቲቲዩድና ከ$38^0$27’51" እስከ $38^0$34’49” ምስራቅ ሎንግቲውድ ላይ ነው።

2.2 የአየር ንብረት

የንላቴና ታቦር ተራራዎች የተፈጥሮ ደን

የተፈጥሮ ደኑ የሚገኝባቸው ወረዳዎች የመሬት አቀማመጥ እንደሚያመለክተው ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ ከ2500-4280 ሜትር የሚደርስ ሲሆን አካባቢው በተለምዶ አጠራር አራቱን ዓይነት የአየር ንብረት በውስጡ የያዘ ሲሆን እነሱም ውርጭ፣ ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ አየር ንብረት ናቸው። ይሁን እንጅ ይህ የደን ክልል የያዘው የመሬት መጠን አብዛኛው ከ3000 ሜ ከፍታ በላይ በመሆኑ በስፋት ደጋና ውርጭ አየር ንብረቶችን እንደያዘ ከሳይንት፣ ለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ያገኘናቸው መረጃዎች ያመለክታሉ። በተለይ ደጋማው አካባቢ ገብስና ስንዴ የመሳሰሉ ሰብሎችን ለማልማት ተስማሚ ሲሆን ለበግ እርባታ ምቹ ነው።

በኮምቦልቻ ሜትሮሎጅ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መረጃ መሰረት በቀጠናው ውስጥ በሐርቡ ጣቢያ ከ1987-1998 ዓ.ም በተወሰደ መረጃ መሰረት ቀጠናው በዓመት ከ500 እስከ 2000 ሚ.ሜ የሚደርስ የዝናብ መጠን የሚያገኝ ሲሆን አማካይ አመታዊ የዝናብ መጠን ድግሞ 933.2 ሚሜ ነው። በተጨማሪም እንደ አቶ አባተ ሽፈራው (2002) ከሆነ የቦረና ወረዳና አካባቢው በዓመት ከ889 እስከ 1500 ሚ.ሜ የሚደርስ የዝናብ መጠን የሚያገኝ ሲሆን አመታዊ አማካኝ የሙቀት መጠን ከ14 እስከ 19 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እንደሚደርስ ይገመታል።

የመካከለኛው አማራ የልማት ቀጠና የመኸርና በልግ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በመሆኑ በአብዛኛው አካባቢ በዓመት ሁለት ጊዜ የሰብል ምርት ማምረት ይቻላል። የተፈጥሮ ደኑና አካባቢው በዚህ የልማት ቀጠና የሚገኝና በቂ ዝናብ ከሚያገኙ አካባቢዎች የሚመደብ በመሆኑ ሁለት የእርጥብ ወቅቶች /Bimodal Rain fall/ ያሉት ሲሆን እነርሱም ከሰኔ እስከ መስከረም ያለው የመኸር እና ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያለው የበልግ ዝናብ ወቅቶች ናቸው። ይሁን እንጅ የእነዚህ ወረዳዎች አብዛኛው ክፍል በተፈጥሮ ሃብት መመናመንና መራቆት ምክንያት የመኸርና የበልግ ዝናብ ዘግይቶ የመጀመርና አስቀድሞ የማቆም አዝማሚያ የሚታይበት በመሆኑ የዚህን አካባቢ ስርዓተ ምህዳር መጠበቅ የአካባቢው አየር ንብረት እንዳይዛባ እና የተስተካከለ የዝናብ ወቅት እንዲኖር ያስችላል።

የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን

ከወግዲ ወረዳ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በአገኘነው መረጃ መሰረት የወረዳው አየር ንብረት በ3 አግሮኢኮሎጅካል ዞን የተከፈለ ነው። የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደንን ጨምሮ የተወሰኑ ቦታዎች (39.07 ከመቶ) ቆላማ ሲሆኑ አብዛኞቹ ግን ወይና ደጋና ደጋ የአየር ንብረት ያላቸው ናቸው። የወረዳው ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ ከ1100 እስከ 2964 ሜ ይደርሳል። የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን የአየር ንብረት ከባህር ወለል

በላይ በሚገኝበት ከፍታ የሚወሰን ሲሆን የተፈጥሮ የደን ክልሉ ደግሞ ከ1100 ሜ (አባይና ወለቃ መጋጠሚያ ቀበሌ 016) እስከ 1821 ሜ (ወይናያ ት/ቤት ቀበሌ 015) ክፍታ ድረስ በሸለቆው ውስጥ ያለውን ከቀበሌ 013 ጫፍ እስከ ቀበሌ 034 የአባይና የሹም ወንዝ መጋጠሚያ ድረስ ሜዳማ፣ ተራራማና ወጣገባ የደን መሬት የሚያጠቃልል በመሆኑ በአብዛኛው ቆላማ የአየር ንብረት አለው፡፡

ከወረዳው አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በአገኘነው መረጃ መሰረት የወረዳው ዓመታዊ የዝናብ መጠን ስርጭት ከ600 እስከ 1100 ሚ.ሚ የሚደርስ ሲሆን አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን 850 ሚ.ሚ ነው፡፡ የሙቀት መጠኑም 20 እስከ 27^0C ይደርሳል፡፡ ይሁን እንጅ እንደ አቶ ጫኔ ገበየሁ (1993) ከሆነ የተፈጥሮ የደን ክልሉ አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ከ1200 እስከ 1400 ሚ.ሚ ይደርሳል፡፡ እንዲሁም አማካይ ዓመታዊ የሙቀት መጠን 18.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲሆን ዝቅተኛው ዕለታዊ የሙቀት መጠን 11.4 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ከፍተኛው ደግሞ 25.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እንደሚደርስ ይታመናል፡፡

የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደንና አካባቢው በሁለት እርጥብ ወቅቶች /Bimodal Rain fall/ የተከፈለ ነዉ፡፡ እረጅሙ የእርጥብ ወቅት ከሰኔ እስከ መስከረም ያለው ወቅት ሲሆን ሌላው ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያለው የበልግ ዝናብ ወቅት ነው፡፡ በአጠቃላይ ሸለቆውና አካባቢው ዝቅተኛ የዝናብ መጠን ከሚያገኙት አካባቢዎች የሚመደብ ነው፡፡

የየጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን

የጎፍ ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ ከ2000-3000 ሜትር የሚደርስ በመሆኑ የደጋና ወይና ደጋ አየር ንብረት አለው፡፡ በኮምቦልቻ ሜትሮሎጅ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መረጃ መሰረት የአካባቢው ያለፉት ዓመታት (1977 እስከ 1998 ዓ.ም) ዓመታዊ አማካኝ የዝናብ መጠን 1038 ሚ.ሜ ሲሆን ሁለት የእርጥብ ወቅቶች /Bimodal Rain fall/ አሉት፡፡ በበልግ ወቅት የአካባቢው (ከመጋቢት እስከ ግንቦት) አማካኝ ወርሃዊ የዝንብ መጠኑ 264 ሚ.ሜ ሲሆን በመኸር ወቅት (ከሰኔ እስከ መስከረም) ደግሞ 435 ሚ.ሜ እንደሚደርስ ከኮምቦልቻ ሜትሮሎጅ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የአካባቢው አማካኝ የሙቀት መጠንም ከ12.3 እስከ 26.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ የሚደርስ ሲሆን አማካኝ የሙቀት መጠን ደግሞ 18.7 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እንደሆነ ይገመታል፡፡

2.3 የመሬት አቀማመጥ

የጎላቴና ታቦር ተራራዎች የተፈጥሮ ደን

የተፈጥሮ ደኑ በ4 ወረዳዎች ውስጥ ከ18 ቀበሌዎች ጋር የሚዋሰን በመሆኑ ጀግራፊያዊ አቀማመጡን በመቶኛ ለማስቀመጥ ቢያስቸግርም በአብዛኛው ከፓርኩ ጋር ተያይዞ የታቦር፣ አሞራ ገደል፣ ጎላቴ፣ ጋያ ተራራ ሰንሰለቶችን ተከትሎ የሚገኝ የአፍሮ አልፓይንና ሰብ አፍሮ አልፓይን ደን ነው፡፡ ይሁን እንጅ ደኑ አልፎ አልፎ ገደላ ገደል ሆነው ጥቅጥቅ ያለ የአስታና አምጃ ደን ያለባቸው አካባቢዎች ያሉት ሲሆን በተለይ በጎላቴ፣ ጋያና ታቦር ተራራዎች አናት ላይ እጅግ ሲፊ፣ ሜዳማ፣ ጨረፌ፣ ጅብራና አሸንዳ የሚበዛባቸው ቦታዎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡ የጎላቴና አሞራ ገደል ተራራዎች አቀስታ ከተማን፣ ተንታ አጅባር ከተማንና በዞኑ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች አካባቢዎችን ቁልቁል ለማየትና ማራኪውን መለከአ ምድራዊ ገጽታ ለመቃኘት የሚያመቹ ቦታዎች ናቸው፡፡

የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን

የወግዲ ወረዳ የመሬት አቀማመጥ 50 ከመቶ ሜዳማ፣ 11 ከመቶ ሸለቆማ፣ 27 ከመቶ ወጣገባ፣ 12 ከመቶ ተራራማ እንደሆነ ከወረዳው አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል። የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን ከፍታው ከ1100 ሜ ጀምሮ እስከ 1800 ሜ እየጨመረ የሚሔድ በመሆኑ በውስጡ የተለያዩ መልከአምድራዊ ገፅታዎች አሉት። የወለቃና አባይ ወንዞችን ተከትሎ የሚገኙ የውሃ ዳር ደኖችን (Riverine Vegetation) የሚወክል ስነ ምህዳር የያዙ ስፍራዎች ሙሉ በሙሉ ሜዳማ ሲሆኑ እጅግ ማራኪ በመሆናቸው የቱሪስት መስህብነታቸው የጎላ ነው። አጋማይት፣ አቡ ጠንጠቃ፣ ደድሃሬ፣ ጠማሜ፣ መጋጠሚያና ዲዳ ዋጮ ሜዳማ ከሆኑ ቦታዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እነዚህ ደኖች በውስጣቸውም እጅግ በጣም ግዙፍና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎችን አቅፈው የያዙ በመሆናቸው ለዘቦታ ጥበቃ (In-situ Conservation) ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። በተለይ የወለቃና የአባይ ወንዝ መጋጠሚ አካባቢ ያለው ቢች ከተፈጥሮ ደኖቹ ጋር ተጣምሮ በሌላ አካባቢ የማይገኝ የተለየ መልከዓምድር ይጥራል። በተለይ በበጋ ወቅት የተለየ መዝናኛና መዋኛ መሆን ይችላል። የውሃው አቀማመጥ ለጀልባ ትራንፖርት አመቺ ነው። ከሜዳማ ቦታዎች ቀጥሎ የተፈጥሮ ደኑ ክፍታው እየጨመረ የሚሄድና ለአይን ማራኪ የሆኑ የተለያዩ ሰንሰለታማና ወጣገባ ኮረብታዎች ያሉት ሲሆን በውስጡም በዋናነት አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (Acacia-Boswellia-Commiphora ecosystem) የሚወክል የተፈጥሮ ደን ይገኛል ።

የየጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን

ጎፍ በጆአግራፊያዊ አቀማመጡ ከዳር ወደ ውስጥ ሲገባ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድና የደኑ ክፍተኛ ቦታ (3000 ሜ) ከመሃል ላይ የሚገኝ በመሆኑ የኮምቦልቻን ከተማ ከ8 ኪ.ሜ ርቀት እንዲሁም አጠቃላይ የደኑን ክልል በቀላሉ ለማየት ያስችላል። አካባቢው ለክለት የተጋለጠ (Fragile Land) ስለነበር የደን ተከላው ሲካሄድ ገደላማ፣ ወጣ ገባና ተራራማ አካባቢዎችን ያካተተ ነበር። በመሆኑም ደኑ በገደላማ፣ ወጣ ገባና ተራራማ ቦታዎች የተሞላ ነው። የምስራቃዊ ደን ክልሉ ደግሞ ከታራራው ጫፍ ጀምሮ ቁልቁል በሚፈሱ የመጠራ፣ ቦሰና፣ ማርዬ፣ ጓሮ ሸለቆዎች የተከፋፈለ ነው። የደን ክልሉ በተለይም በታችኛው አካባቢ በአብዛኛው በእርሻና በመንደር የተከበበ በመሆኑ እንደ ውሃ ቋትና የተፋሰስ አናት ሁኖ ያገለግላል።

3. የጥናቱ መነሻ

በዓለምና አገር አቀፍ ደረጃ እየተባባሰ የመጣውን የሙቀት መጨመርና የአየር ንብረት መዛባት ለመከላከል የተፈጥሮ ሃብቶችን መጠበቅና ማልማት የወቅቱ ዋነኛ ትኩረት ሁኗል። በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ የምክክር መድረኮችም ዋነኛ አጀንዳ ከመሆኑም በላይ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ትኩረት ሰጥተው ለሚሰሩ እንደኛ ላሉ ድሃ ሀገራት ባላቸው የተፈጥሮ ወካይ ስርዓተ ምህዳር ስፋት መሰረት ድጎማ የሚደረግበት አሰራር እየተዘረጋ ይገኛል። ስለዚህ በክልል ደረጃ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራቱ እየደረሠ ያለውን አካባቢያዊ ለውጥና የአየር መዛባት ከመታደግም በላይ ሀገራችን ለድሃ ሀገራት የሚሰጠውን ድጎማ ከሌሎች ሀገሮች በተሻለ ሁኔታ እንድታገኝ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ በክልሉ የሚገኘውን ወካይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህር ለማሳደግ የሚስችል በመሆኑ ነው።

ሌላው ለጥናቱ መነሻ የሆነው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልሉን በስድስት የልማት ቀጠናዎች በመክፈል በወጣው የአምስት አመት (2002-2007) ስትራቴጅክ እቅድ በመካከለኛዉ የልማት ቀጠና ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸው የመንግስት ደኖች እና የብርቅየ የዱር እንስሳት የሚኖሩባቸው ሌሎች የተፈጥሮ ደን ቦታዎች በእርሻ መስፋፋት፣ በልቅ ግጦሽና ደን ጭፍጨፋ

ምክንያት ከፍተኛ ጥፋት እየተፈፀመባቸው ስለሆነ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው በመገለጹና ይህንንም በጥናት ማረጋገጥ በማስፈለጉ ነው፡፡

በተጨማሪም የአባይ ወንዝ ባለው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች የተነሳ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረትና ዕውቅና የተቸረው አካባቢ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የአባይ ሸለቆን ተከትሎ ያለው የዕጣን ዛፍ ደን በህገ-ወጥ መንገድ የእርሻ ማሳን ከማስፋፋት ጋር ተያይዞ በአብዛኛው በመጨፍጨፍ ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ይህን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና የተቸረውን አካባቢ የሚወክል ስርዓተ ምህዳር ማግኘት በማስፈለጉ ሌላው የጥናቱ መነሻ ሁኗል፡፡

4 የጥናቱ አስፈላጊነት

በቀጣዮቹ 5 ዓመታት በክልሉ ያሉ የጥብቅ ስፍራዎችን ቁጥር ከ4 ወደ 11 በመጨመር በክልሉ የሚገኘውን ወሳይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህዳር ማሳደግ በማስፈለጉ፣

በሳይንት፣ ለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች የሚገኙ የአፍሮ አለፓይንና የሰብ አፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳሮች በማጥናትና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅማቸውን በማረጋገጥ የቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክን ማስፋፋት በማስፈለጉ፣

በሳይንት፣ ለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች አፍሮ አለፓይንና የሰብ አፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳሮች ውስጥ ተጠልለው የሚገኙ ቀይ ቀበሮችን መኖሪያ፣ መመገቢያና መራቢያ ቦታዎች ከሰውና ከቤት እንስሳት ንክኪ ነፃ ማድረግ ማስፈለጉ፣

በየጎፍ የመንግስት ጥብቅ ድን አሁን ባለው የአጠባበቅ ስልት ዘላቂነቱ ሊረጋገጥ የማይችል በመሆኑ ለጣውላ ምርት ሲባል ከፍተኛ የደን ጭፍጨፋ የሚደርስበት በመሆኑ፣ የደኑ ስፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱና በውስጡ የሚገኙ የዱር እንስሳት ቁጥር በመመናመናቸው ቦታውን በማጥናት ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅሙን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፣

በወለቃና አባይ ወንዞች አካባቢ የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖች ውስጥ የሚገኙ ለመጥፋ የተቃረቡና እድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎች ለጣውላ ምርት ሲባል ከፍተኛ የደን ጭፍጨፋ የሚደርስባቸው በመሆኑ፣ በዚህ አካባቢ የሚገኘው የእጣንና የሙጫ ዛፎች ለእርሻ መስፋፋት ሲባል ከፍተኛ ጥፋት የሚደርስባቸው በመሆኑ፣ በብዙ ቦታዎች በክልሉ የአባይ ሸለቆን ሊወክል የሚችሉ ቦታዎች እየጠፉ ስለሆነ ይህንን አካባቢ ሊወክል የሚችል ስርዓት ምህዳር በማጥናት ተፈጥሮዊ ወሳይ ስርዓተ ምህዳር ማግኘት በማስፈለጉ፣

5. የዳሰሳ ጥናቱ ዓላማ

በዮጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን፣ በታቦርና ጎላቴ ተራራዎች እና በወለቃና አባይ ወንዞች አካባቢ የሚገኘውን የተፈጥሮ ደን በIUCN የጥብቅ ስፍራዎች መምረጫ መስፈርት መሰረት ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅማቸውን ማጥናትና ማረጋገጥ፣

5.1. ዝርዝር ዓላማ

- የቦረና-ሳይንት ብሔራዊ ፓርክን ለማስፋት በቦረና፣ በሳይንት፣ ለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች የጎላቴና ታቦር ተራራዎችን አካባቢ የብዝሃ- ህይወት ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታ ይዘት ማረጋገጥ ፣

- ❖ የየጎፍ የመንግስት ጥብቅ ደን (በደሴ ዙሪያ ወረዳ፣ አልብኮ ወረዳ፣ ኮምቦልቻ ከተማና ከተማ አሰተዳደር) አካባቢን የብዝሃ- ህይወት ሃብትና የተፈጥሮ ገጽታ ይዘት ማረጋገጥ፣
- ❖ ወግዲ ወረዳ በወለቃና አባይ ወንዞች አካባቢ የተፈጥሮ ደኖች (የብዝሃ- ህይወት) እና ተፈጥሮ ገጽታውን ይዘት በIUCN የጥብቅ ስፍራዎች መምረጫ መስፈርት መሰረት ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅማቸውን በዳሰሳ ማጥናትና ማረጋገጥ፣
- ❖ በጎላቴና ታቦር ተራራዎች፣ በየጎፍ የመንግስት ጥብቅ ደንና በወለቃና አባይ ወንዞች አካባቢ የሚገኙ የቱሪስት መስህ ሃብቶችን በመለየት ለቱሪዝም ዕድግት ያላቸውን አቅም ማጥናት፣
- ❖ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አጋር አካላት ሊኖራቸው የሚችለውን ተግባርና ኃላፊነት በመለየት ወደፊት እነዚህ አካባቢዎች ወደ ጥብቅ ስፋራነት የሚመጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

6. የጥናቱ ስልቶችና ቁሳቁሶች

6.1. ስልቶች

- በዮጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን፣ በታቦርና ጎላቴ ተራራዎች እና በወለቃና አባይ ወንዞች አካባቢ የተፈጥሮ ደኖች ውስጥ የዳሰሳ ጥናት ለማረድግና የአካባቢዎችን ዋና ዋና የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ኢኮሲስተም፣ ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህብ ሃብቶች ለመለየት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት (አስተዳደር፣ ግብርናና ገጠር ልማት፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ባህልና ቱሪዝምና አካባቢውን በደንብ የሚያውቁ ግለሰቦች) ድጋፍ ተጠቅመናል፣
- የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ኢኮሲስተምና የቱሪዝም አቅም ጥናት ለማካሄድ የጥናት መስመሮችን (Transect lines walk) ተጠቅመናል። የጉዞ መስመሮችን ቀኝት ከማድረጋችን በፊት በጥንቃቄ መርጠናል። የተመረጡ ሁሉም የጉዞ መስመሮች ቢያንስ አንድ ጊዜ ታይተዋል። በጉዞ መስመሩ ግራና ቀኝ እስከ 200 ሜትር ርቀት ድረስ የሚታዩ የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋትና ኢኮሲስተም ተመዝገበዋል።
- በጉዞ መስመራችን መነሻና መድረሻችንን ጨምሮ አስፈላጊና የተመረጡ የጅፒኤስ መረጃዎችን ወስደናል። የዱር እንስሳት ቅኝት ለማካሄድና ለመለየት በዋናነት እይታችንን፣ በተለይም አእዋፋትን ለመለየት ባይኖኩላር እንዲሁም በቅኝታችን ወቅት ማግኘት ያልቻልናቸውን የዱር እንስሳት ለመለየት ፎቶግራፍ በመጠቀም የአካባቢውን ሰዎች ምስክርነት ተጠቅመናል። በተጨማሪም ቀጥተኛ ያልሆኑ የዱር እንስሳት መለያ ዘዴዎችን እንደ በጠጥ፣ የእግር ዱካ፣ ድምፅ፣ ማደሪያ ቦታዎች፣ መመገቢያ ቦታዎችን ወዘተ ተጠቅመናል።
- የዱር እንስሳትና ዕፅዋትን ለመለየት ፊልድ ጋይድ መፅሃፍትና የረጅም ጊዜ ተሞክሯችንን ተጠቅመናል። እንዲሁም ለተጨማሪ ማረጋገጫ በባለሙያዎች አማካኝነት በሁሉም የጉዞ መስመሮች የፎቶ ግራፍና የፊልም ቀረፃ ተካሂዷል።
- በIUCN መስፈርት መሰረት የተቀመጡ መመዘኛ ነጥቦች በመጠቀም ታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎችን የመግለፅና መረጃዎችን የመተንተን ስራ ተሠርቷል።
- የሚመለከታቸውን የዞንና የወረዳ የመንግስት መሣሪያ ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን በማነጋገር ሁለተኛ ደረጃ መረጃ ለማሰባሰብና እንዲሁም ግብረ መልስ ለመስጠት ተሞክሯል፣
- በአካባቢው ላይ ከአሁን በፊት የተሰበሰቡና የተጠኑ መረጃዎችን ተጠቅመናል፣

ከላይ በተዘረዘሩት ስልቶች መሠረት የተጠኑ ስፍራዎች ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅማቸውን የሚያሟሉ መሰረታዊ እውነታዎች፣ ዓላማዎች፣ ባለድርሻ አካላት ተግባራት እና ወደ ፊት ተግባራዊ መሆን ያለባቸው ጉዳዮች ለመለየት ተችሏል።

6.2. በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች

- ይህን የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ እንደ ጂፒኤስ፣ ባይኖኩላር፣ ዲጂታል ፎቶ ካሜራ፣ ቪዲዮ ካሜራ፣ ጋይድ ቡክ (የአእዋፋት፣ የአጥቢዎችና ዕፅዋት ማረጋገጫ መጽሐፍት)፣ በዓለማቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት /IUCN/ ጥብቅ ሥፍራዎች ምደባ መስፈርት መሠረት ለመገምገም የሚያስችል የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ ወዘተ የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ብዝሀ ህይዎትና የተፈጥሮ ገጽታዎችን፣ በአካባቢው የሚገኙ ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህብ ሀብቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት በ3ቱም ቦታዎች የዳሰሳ ጥናቱ ተካሂዷል።

6.3. በመስክ ጥናቱ የተከናወኑ ተግባራት

- ❖ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ስርዓተ ምህዳርና የብዝሃ ሕይወት ሃብቶች ተለይተዋል፣
- ❖ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች በIUCN መስፈርት መሠረት ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅምና ደረጃ በሚገባ ተተንትኗል፣
- ❖ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ውስጥና ወጭ ለቱሪዝም ምቹ የሆኑ ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶች ተለይተዋል፣
- ❖ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና እንስሳትና እጽዋት ዝርዝርና ሳይንሣዊ መጠሪያ ተለይቷል፣
- ❖ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ጥበቃ ላይ ያሉ መሰረታዊ ችግሮች ተተንትነዋል፣
- ❖ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎችን ለመከለልና ህጋዊ ለማድረግ ወደ ፊት መከናወን ያለባቸው ተግባራት ተዘርዝረዋል፣
- ❖ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ጥብቅ ስፍራ ቢሆኑ የሚያሳኳቸው ዓላማዎች ተለይተዋል፣
- ❖ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎችን ለመከለልና ህጋዊ ለማድረግ የአጋር አካላት ሚና ተተንትኗል፣

7. የጥናቱ ሂደትና የተዳሰሱ አካባቢዎች

በአጅባር፣ በወግዲና በደሴ ከተሞች ለዳሰሳ ጥናት ዝግጅት በምናደርግበት ወቅት ከፍተኛ የዱር እንስሳት መኖሪያ የሆኑና ለቅኝት የሚያመቹ 14 ያህል የጉዞ መስመሮችን ለይተናል። የእያንዳንዳቸው ርዝመትም ከ6 እስከ 33 ኪ.ሜ ይሆናል። በቅኝታችን የተጠቀምናቸው የጉዞ መስመሮችም የሚከተሉት ናቸው።

1. ከበሌጨማ መንደር እስከ ካራ አባቦጊ የቦ/ሳ/ብ/ፓርክ ኬላ ያሉ ቦታዎች (ርዝመት፡ 9 ኪ.ሜ)፣
   - ☞ *በጉዞ መስመሩ የተቃኙ አካባቢዎችና ቀበሌዎች፡-*
     1. የቦረና ወረዳ፡ 031 ቀበሌ (ጭሮ ቃዲስ)፣
     2. የለጋምቦ ወረዳ፡ 01 ቀበሌ (ድንገታ)፣ 03 ቀበሌ (ጌደራ)፣
     3. የሳይንት ወረዳ፡ 08 (ቤጃ ጭላጋ)፣ 010 ቀበሌ (ዱርካ)፣
   - ☞ ይህ መስመር የዱር እንስሳት መተላለፊያ ኮሪደር ሲሆን ወደ ጎን ከ400 ሜትር እስከ 2.5 ኪ.ሜ ይረዝማል። ጠቅላላ ስፋቱም 1039 ሄ/ር ይገመታል።
   - ☞ አሳሳቢውና አስጨናቂው የቤሌጨማ መንደር የሚገኘውም በዚህ የጉዞ መስመር ውስጥ ነው።
2. ከለጋምቦ ወረዳ 01 እና 03 ቀበሌዎች፣ ከሳይንት ወረዳ 08 እና 09 ቀበሌዎች መገናኛ እስከ ከሳይንት ወረዳ 09 እና 05 ቀበሌዎች መገናኛ አካባቢ (ርዝመት፡ 12 ኪ.ሜ)፣

- ☞ ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍነው በሳይንት ወረዳ ውስጥ የሚገኙ 09፣ 010 እና 05 ቀበሌዎችን ነው።።

3. ሳይንት ወረዳ ውስጥ 019 ቀበሌ የታቦር ታራራ ጫፍ (ርዝመት 6 ኪ.ሜ፡ መመልከቻ ቦታ)፣
   - ☞ ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍነው በሳይንት ወረዳ ውስጥ የሚገኙ 019 እና 031 ቀበሌዎችን ነው።።
4. ከቤሌጨማ አፋፍ እና ለጋምቦ 03 ቀበሌ እስከ 019 ቀበሌ (ሽምቦሳ ማሪያም ቤተክርስቲያን) አካባቢ ድርስ (12 ኪ.ሜ)
   - ☞ ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍነው በሳይንት ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን 019 ቀበሌን ብቻ ነው።።
5. ቤሌጨማ መንደር እና ለጋምቦ ወረዳ 05 ቀበሌ እስከ ሳይንት ወረዳ 029 ቀበሌ (መልካ ገርባ) አካባቢ ድረስ (ርዝመት 13 ኪ.ሜ)፣
   - ☞ *በዚህ የጉዞ የሚሸፍናቸው አካባቢዎችና ቀበሌዎች፡-*
     1. የለጋምቦ ወረዳ፡ 05፣ 06፣ 030 እና 031 ቀበሌዎች ናቸው፣
     2. የሳይንት ወረዳ፡ 020፣ 029 እና 031 ቀበሌዎችናቸው፣
   - ☞ *በዚህ አካባቢ አረር የሚባል መንደር ያለ ሲሆን የዱ/ እንስሳት መተላለፊያውን የዘጋው ስለሆነ መክፈት ያለበት ቦታ ነው።።*
   - ☞ *በዚህ የጉዞ መስመር ውስጥ ያለው ይህ ኮሪዶር 6 ኪ.ሜ ጠቅላላ ርዝመት ያለው ሲሆን ወደ ጎን ከ500 ሜ እስከ 1.5 ኪ.ሜ ይረዝማል።።*
6. ከመልካ ገርባ ሳይንት ወረዳ 029 ቀበሌ የአደባባይ መስክን፣ የጎላቴና የጋያ ተራራዎችን አልፎ እስክ ጭሮ ከተማ አፋፍ (ተሪ) ድረስ (ርዝመት 18 ኪ.ሜ)፣
   - ☞ *ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍናቸው አካባቢዎችና ቀበሌዎች፡-*
     1. የለጋምቦ ወረዳ፡ 027፣ 030 እና 031 ቀበሌዎች ናቸው፣
     2. የተንታ ወረዳ፡ 0120 እና 027 ቀበሌዎች ናቸው፣
   - ☞ *በዚህ የጉዞ መስመር ውስጥ ሶስተኛ የዱር እንስሳት መተላለፊያ ኮሪደር ያለ ቢሆንም ይዞታው ከሌሎቹ በጣም የተሸለ ሲሆን በመጠኑ በእርሻ እየተጣበበ ስለሆነ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ቦታ ነው።። ይህ ኮሪዶር 5 ኪ.ሜ ጠቅላላ ርዝመት ያለው ሲሆን ወደ ጎን ከሌሎች ኮሪደሮች በጣም ይሰፋል።።*
   - ☞ *በዚህ የጉዞ መስመር ውስጥ የቦረና፣ ሳይንት፣ ለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች ከፍተኛው ተራራ ‹‹ የጎላቴ ተራራ-4280 ሜ ከፍታ ›› ይገኛል።።*
7. ወግዲ ወረዳ ቀበሌ 015 ከወይናያ ት/ቤት ጀምሮ በጥቁር እንጨት አድርጎና የወለቃና የአባይ ወንዞችን ተከትሎ እስከ ቀበሌ 017 ደድሃሬና ቀበሌ 018 አቡ ጠንጠቃ አካባቢ ድረስ (ርዝመት 33 ኪ.ሜ)፣
   - ☞ *ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍነው 015፣ 016፣ 017 እና 018 ቀበሌዎችን ነው።።*
   - ☞ *በዚህ የጉዞ መስመር ውስጥ ቀዋ ዳባ፣ ዲዳ ዋጮ፣ ሰንበቶ፣ መጋጠሚያ፣ ጠማሜ፣ ደድሃሬ፣ አቡ ጠንጠቃ፣ አጋማይት የሰውን ቀልብ በደንብ የሚስቡ ቦታዎች ናቸው።።*
8. ወግዲ ወረዳ ቀበሌ 025 ዘሙድ እስከ የሹምና አባይ ወንዞች መጋጠሚያ ድረስ (ርዝመት 17 ኪ.ሜ)
   - ☞ *ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍናቸው 018፣ 025፣ 026 እና 034 ቀበሌዎች ነው*
   - ☞ *በዚህ የጉዞ መስመር ውስጥ የሶማ በርሃ፣ የአባይና የሹም ወንዞች መጋጠሚያ፣ አቡ ጠንጠቃ፣ አጋማይት፣ የአባይና ደብረ ወርቅ ወንዞች መጋጠሚያ፣ የቀለምና ጣቀት ወንዞች፣ የአባይ ወንዝንና ገባሮቹን ለማየት የሚያስችል የቁንዲ አፋፍ ይገኛሉ፣*
9. ወግዲ ወረዳ ከወግዲ ከተማ አስከ አብየ ጎርባ ድረስ (ርዝመት 30 ኪ.ሜ)፣
10. ኮምቦልቻ ከተማ ቀበሌ 010 ዳኛ ት/ቤት ጅምሮ እንዲሁም የመኪና መንገዱን ተከትሎ እስከ ቀበሌ 010 እና 09 ድንበር ድረስ (ርዝመት 7 ኪ.ሜ)፣
   - ☞ *ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍነው የቀበሌ 010 አካባቢዎችን ብቻ ነው*

11. ኮምቦልቻ ከተማ ቀበሌ 010 ዳኛ ት/ቤት ጅምሮ እስከ የጎፍ ደን ጫፍና የቀበሌ 09 እና 010 ህዝቦች የአምልኮት ቦታ ድረስ (ርዝመት 8 ኪ.ሜ)፣

- *ይህ የጉዞ መስመር የሚሸፍነው የቀበሌ 010 እና 09 አካባቢዎችን ብቻ ነው*

12. ደሴ ዙሪያ ወረዳ ቀበሌ 041 የይጅራ ደን አካባቢ (ርዝመት 7 ኪ.ሜ)፣

- *ይዚህ የጉዞ መስመር የሚሸፍናቸው አካባቢዎችና ቀበሌዎች፡-*
    1. ደሴ ዙሪያ ወረዳ፡ 09፣ 040 እና 041 ቀበሌዎች ናቸው፣
    2. የአልብኮ ወረዳ፡ 014 ቀበሌ ነው፣
    3. ኮምቦልቻ ከተማ፡ 010 ቀበሌ ነወ፣
    4. ቃሉ ወረዳ፡ ቀበሌ 031 ነው፣
- *በዚህ የጉዞ መስመር በተለይም በቀበሌ 041 አካባቢ በይጃራ ደን ውስጥ የሚኖሩ 5 መንደሮች ይገኛሉ፣*
- *የቃሉ ወረዳ ቀበሌ 031 ሙሉ በሙሉ ተቆርጧል፣*
- *በዚህ አካባቢ ማይባር የሚባል ሐይቅ ይገኛል፣*

13. ከሐረጉ ደን ደሴ ከተማ ቀበሌ 015 ጅሚ ከተማ አፋፍ ጀምሮ እስከ ደሴ ዙሪያ ወረዳ 012 እና 040 ቀበሌዎች አካባቢ ድረስ (6 ኪ.. ሜ)፣

- *ይዚህ የጉዞ መስመር የሚሸፍናቸው አካባቢዎችና ቀበሌዎች፡-*
    1. ደሴ ዙሪያ ወረዳ፡ 012 እና 040 ቀበሌዎች ናቸው፣
    2. ደሴ ከተማ፡ 015 ቀበሌ ነው፣
    3. ኮምቦልቻ ከተማ፡ 011 እና 10 ቀበሌዎች ናቸው፣

14. ኮምቦልቻ ከተማ ቀበሌ 010 አካባቢ ዳኛ ት/ቤት ጀምሮ እንዲሁም በመካከለኛ ካምፕ አድርጎ እስከ ደሴ ዙሪያ ወረዳ ቀበሌ 09 የጎፍ ሽንቁር ድንጋይ/ቡልኮ/ ድረስ (8 ኪ.ሜ)፣

- *በዚህ የጉዞ መስመርም በቀበሌ 09 አካባቢ ውስጥ የሚኖሩ 3 መንደሮች ይገኛሉ፣*
- *በዚህ አካባቢ ያለው ደን በሰፈራና በእርሻ የተቆረጠ ነው፣*

ከላይ በተገለፀው ቅደም ተከተል መሠረት ከፍተኛ የዱር እንስሳት መኖሪያ የሆኑና ለቅኝት የሚያመቹ 6 ያህል የጉዞ መስመሮችን በመጠቀም በቦረና፣ ሳይንት፣ ለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች የታቦርና ጎላቴ ተራራዎችን ጥበቅ ስፍራ የመሆን አቅም ተጠንቷል።



ምስል1. በታቦርና ጎላቴ ተራራዎች፣ በወለቃና አባይ ወንዞች እና በየጎፍ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች በጥናቱ ወቅት የተሳተፉ የክልል፣ የዞንና ወረዳ ባለሙያዎች፣ የአካባቢው ሰዎችና ዘበኞች

ከዚህ ቀጥሎ የወለቃና አባይ ወንዞችን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም 3 ያህል የጉዞ መሰመሮችን በመጠቀም ለመዳሰስ ተሞክሯል። በመጨረሻም የጎፍ የመንግስት ደን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም 5 ያህል የጉዞ መሰመሮችን በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዶ አስፈላጊ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

የጥናት ቡድኑ ከክልል 3 ባለሙያዎችን፣ ከወረዳዎች 8 ባለሙያዎችን እንዲሁም 2 መንገድ መሪዎችን ያካተተ ነበር። በአጠቃላይ በዳሰሳ ጥናቱ ወቅት ወደ 140 ኪ.ሜ ርቀት በእግር ጉዞ ተሸፍኗል።

8 አዳሰሳ ጥናቱ የተገኙ ውጤቶች

8.1. የኳላቴና ታቦር ተራራዎች ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ

8.1.1. የኳላቴና ታቦር ተራራዎች ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ዝርዝር የተፈጥሮ ሃብት ሁኔታ ትንተና

የስርዓተ ምህዳር ሁኔታ

በአሁኑ ጊዜ ከሠሃራ በታች ባሉ አፍሪካ ቦታዎች 11817 ካ. ኪ.ሜ ስፋት ያላቸው ከፍተኛ ቦታዎች በአፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳር /Afroalpine ecosystem/ **የሚገኙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ** 73 **ከመቶ የሚሆነው (8626.41 ካ. ኪ.ሜ) የሚሆነው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ነው። ከዚህ ውስጥም 1509.62 ካ. ኪ.ሜ በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ፣ 412 ካ. ኪ.ሜ በሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ተጠበቀ ሲሆን 43.75 ካ. ኪ.ሜ በቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክ ውስጥ ተከልሎ እንዲጠበቅ ተካቷል።**

ይሁን እንጅ ተመሳሳይ ስርዓተ ምህዳር ያላቸው በርካታ አካባቢዎች በሣይንት፣ ለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች ከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙ ሲሆን በከፍተኛ ሁኔታ ለጉዳት ተጋልጠው ይገኛሉ። እነዚህ አካባቢዎች እንደ ፓርኩ 2 ዓይነት ስርዓተ ምህዳሮችን ይወክላሉ።



ምስል 2. **በሳይንት ወረዳ** 09 **እና** 019 **ቀበሌዎች እንዲሁም በለጋምቦ ወረዳ** 05 **ቀበሌ የሰብ አፍሮ አልፓይንና የአፍሮ አልፓይን ስረዓተ ምህዳር የሚወክሉ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የተፈጥሮ ገፅታ**

የመጀመሪያው በመጠኑ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ያለውና አመቱን በሙሉ አረንጓዴ ሁኖ በሳይንት ወረዳ 09 **እና** 019 **ቀበሌዎች እንዲሁም ለጋምቦ ወረዳ** 05 **ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው የሰብ አፍሮ አልፓይን ስነ ምህዳርን ሚወክለው ነው። ሁለተኛው በጓሳ ሳር ብቻ አልፎ አልፎ ጅብራና አሸንዳ እንዲሁም ጥቅጥቅ ያለ ጨረፈፋ፣ የዋልያ እሾህ፣ ጅብራና አሸንዳ ያለበት ሆኖ በታቦርና ኳላቴ ተራራዎች የሚገኘውን ዓይነት የሚወክለው የአፍሮ አልፓይን ስነ ምህዳር ነው። ስለዚህ እነዚህ አካባቢዎች በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን አቅፈው የያዙ በመሆናቸው እና**

በአፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳር ወካይነታቸው በፓርኩ ክለል ውስጥ መካተት ያለባቸው መሆኑን ያመለክታል።



ምስል 3. በለጋምቦ ወረዳ 030 እና 031 ቀበሌ በጎላቴ ተራራና አደባባይ መስክ የአፍሮ አልፓይን ስረዓተ ምህዳር የሚወክሉ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የተፈጥሮ ገፅታ

የዱር እንስሳት

ይህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ በቤሌጨማና አረር መንደሮች የተቋረጠ ቢሆንም የተራራ ሰንሰለቶች ግን በቀጥታ ከቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክ የተራራ ሰንሰለቶች ጋር ይገናኛል። በፓርኩ ወስጥ 23 ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት እንደተጠለሉበት ይታወቃል። በተመሳሳይ ሁኔታም በእነዚህ የተራራ ሰንሰለቶች ከ15 በላይ የዱር እንስሳት የሚኖሩ ሲሆን በዋናነት በፓርኩ ውስጥ የሚኖሩና በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ እንደ

- *ቀይ ቀበሮ /Canis simensis/*
- *ጭላዳ ዝንጀሮ /Theropithecus gelada/*
- *የስታርክ ጥንቸል /Lepus starckii/*

የዱር እንስሣት ዝርያዎች በዚህ አካባቢም ይገኛሉ። በተለይም በጎላቴ ተራራና አደባባይ መስክ በፓርኩ ከሚኖሩት የበለጠ ቁጥር ቀይ ቀበሮ እና ጭላዳ ዝንጀሮ እንደሚገኝ ተረጋግጧል።



ምስል 4. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ብዝሃ ህይወት በከፊል

በተጨማሪም በአካባቢው የሚኖሩ ከ40 በላይ አዕዋፋት የተመዘገቡ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 4 ያህሉ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡


- *ራስ ጥቁር መጫ* /Abyssinian siskin/
- **ግንደ ቀርቁር** /Abyssinian Woodpecker/
- **የአበሻ ድመት መሳይ ወፍ**/Abyssinian catbird/
- Abyssinian long claw

ከእነዚህ ሌላ ከኤርትራ ጋር ብቻ የምንጋራቸው

- *ጋጋኖ* (Wattled ibis)፣
- **ኋይት ኮላርድ ፒገን** (White collard pigeon)፣
- **ቁሱ** (Thick billed raven)፣
- **ብላክ ዊንግድ ላቭ በርድ** (Black winged lovebird or Abyssinian lovebird)፣
- **ኋይት ባክድ ብላክ ቲት** (White backed Black Tit)፣

መጠልያ ነው፡፡ እንዲሁም በብዙ ቦታ የማይገኘው ቅልጥም ሰባሪ (Lammergeyer) **ተፈጥሮዊ መኖሪያው ቦታ ነው፡፡**

ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) **እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል** (Bird Life International) **በዓለም አቀፍ ደረጃ በአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም** (Afrotropical Highland Biome) **ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 49 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 26 የአዕዋፍት ዝርያዎች በፓርኩ ውስጥና በአካባቢው ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል፡፡ በዚህ መሰረትም ከአዕዋፍት ጥበቃ አንፃር በፓርኩና በአካባቢው ያሉ ቦታዎች በአይ በ ኤ መስፈርት** (IBA Criteria) *መሰረት* **ኤ ደረጃ 3** (A3 Category) **እንደሚያሟላ ታውቋል፡፡**



ምስል 5. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ብዝሃ ህይወት በከፊል

ስለዚህ እነዘህ 26 የአዕዋፍት ዝርያዎች ከአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም (Afrotropical Highland Biome) **ውጭ በሌላ ባዮም** (Biome) **የማይገኙ በመሆኑ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ወደ ፓርኩ ተከልሎ መጠበቅ እንዳለበት በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡**

ስለሆነም ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በዱር እንስሳት ሃብት ክምችቱና በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ አጥቢዎችና አዕዋፍት መጠለያነቱ IUCN **ለጥብቅ ስፍራዎች ማቋቋሚያ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች** (IUCN criteria for protected areas selection) **የሚያሟላ በመሆኑ የሚያሟላ ወደ ፓርኩ እንዲከለልና እንዲጠበቅ ያስችለዋል፡፡**

የዱር ዕፅዋት

በተመሳሳይ መልኩ በዚህ የዳሰሳ ጥናት የተለዩት አካባቢዎችም ከፓርኩ ክልል አካባቢዎች ጋር አንድ ዓይነት የዕፅዋት ሽፋንና ስርጭት እንዳላቸው ታውቋል፡፡ ይሁን እንጅ አብዛኞቹ በጥናት የተለዩት አካባቢዎች ከፍታቸው በአማካኝ ከፓርኩ ክልል የበለጡ ሲሆን ሜዳማ ናቸው፡፡ የዕፅዋት ሽፋንና ስርጭታቸውም በአብዛኛው የልም መስክን ይመስላል፡፡ በተለይ በጎላቱ ተራራ ያለው አካባቢ በጣም ሰፊ፣ ጅብራ፣ አሸንዳና ጨረፌ በብዛት የሚታይበትና ከፍታውም ከ4200 ሜ በላይ ሲሆን ቀይ ቀበሮም በብዛት የሚገኝበት ነው፡፡ በሳይንት ወረዳ ቀበሌ 09 ጫንጮ ውርማ ደን ጥቅጥቅ ያለ ገደላማ ደን ያለበትና ከፍተኛ የጭላዳ ዝንጀሮ መንጋ የሚታይበት አካባቢ ነው፡፡

በእነዚህ አካባቢዎች ከ20 በላይ ዕፅዋት የተመዘገቡ ሲሆን በውስጣቸው ከሚገኙ ዋና ዋና ዕፅዋት መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

- ***አሰታ****/Erica arborea/*
- ***ጓሳ*** */Festuca spp/*
- ***ጅብራ*** */Gaint lobilea/*

- ቀጋ /*Rosa abyssinica*/
- አምጃ /*Hypericum spp*/
- ሽነት /*Myrica salicifolia*/
- ኮሶ /*Hagenia abyssinica*/
- አሸንዳ/*Kniphofia foliosa*/

8.1.2. የሶሸዮ ኢኮኖሚ ሁኔቶች፣

የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ እና የኑሮ ሁኔታ፣

ይህ የዳሰሳ ጥናት በሚሸፍናቸው 17 ቀበሌዎች በጥቅሉ፣ በ2002ዓ/ም ላይ ከ20,311 በላይ ቤተሰቦች (15186. አባወራ እና በ5125 እማወራዎች የሚመሩ) እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡ የአካባቢው አጠቃላይ ነዋሪም 90,320 (44885 ወንድና 45430 ሴቶች) እንደሚሆን ከሳይንትና ለጋምቦ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤቶች የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ሰንጠረዝ 1 በጥናቱ የተሸፈኑ ቀበሌዎች እና የቤተሰብ መሪዎችና አጠቃላይ ነዋሪዎች ብዛት በወረዳ

የጥናቱ ቀበሌዎች		የቤተሰብ መሪ ብዛት በወረዳ				የአጠቃላይ ነዋሪው ህዝብ ብዛት			
የሚገኙበት ወረዳ	ብዛት	የአባወራ ብዛት		የእማወራ ብዛት		የወንድ ብዛት		የሴት ብዛት	
		በቁጥር	በ%	በቁጥር	በ%	በቁጥር	በ%	በቁጥር	በ%
አማራ ሳይንት	8	5,383	35.45	1,767	34.48	15,289	32.96	15,277	32.51
ለጋምቦ	7	7,448	49.05	2,553	49.81	23,637	50.95	23,667	50.36
ተንታ	2	2,355	15.51	805	15.71	7,462	16.09	8,051	17.13
ድምር	17	15,186	100.00	5,125	100.00	46,388	100.00	46,995	100.00

ምንጭ፡ በገጽ .... ላይ ከአባሪ .... ላይ የተጠቃለለ፣

ለእነዚህ ነዋሪዎች፣ የሰብል እርሻና እንስሳት እርባታ ጥምር ግብርና ዋነኛ የኑሮ መተዳደሪያ ነው፡፡ ስለዚህ፣ በአሁኑ ጊዜ ከ29,359.48 ሄክታር በላይ የሚሸፍን መሬት ለአካባቢው ነዋሪ የሰብል ምርት እና ለቤት እንስሳት ግጦሽ በመዋል ላይ ይገኛል፡፡ 10,717 ሄክታር መሬት በጓሳ ሳር እና፣ በሌሎች የተፈጥሮ ዕፅዋትና ቁጥቋጦዎች የተሸፈነ እንደሆነ ይገመታል፡፡ [ዝርዝሩ በአባሪ ... ላይ ይገኛል፡፡]

በጥናቱ የተሸፈኑት ቦታዎች ከባህር ጠለል ከ2500 ሜትር በላይ የሚገኙ በመሆኑ፣ የአካባቢው ነዋሪ በዋናነት የሚያመርተው ለደጋ አየር ንብረት ተስማሚ የሆኑ የሰብል አይነቶችን ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በዚህ ደጋማ ሥነ ምህዳር ገብስ፣ስንዴ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ሰላሌ፣ ምስር፣ ተልባ፣ አጃና ድንች ይበቅላሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ገብስ፣ስንዴና ባቄላ ዋነኛ ሰብሎች ናቸው፡፡

በአካባቢው የሚገኘው የተፈጥሮ እጽዋት ለዱር እንስሳት መጠለያ ከመሆን ባሻገር፣ በዙሪያው ለሚገኘው ማህበረ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጋር ጠንካራ ትስስር ያለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ፣ አካባቢው በንብ እርባታ ተግባር ያለው ልምድ አንዱ ተጠቃሽ ነው፡፡ ምንም እንኳን የአካባቢው አመታዊ የማር ምርት መጠኑ የሚገልጽ መረጃ እጥረት ቢኖርም፣ የአካባቢው ህብረተሰብ የተፈጥሮ እጽዋቱ

የፈጠረለትን አመቺ ሁኔታ በመጠቀም ከሚያረባቸው ንቦች በገበያ ተፈላጊ የሆነ ልዩ ማር በማምረት ይታወቃል። በ2002ዓ/ም ላይ በየወረዳ ጽ/ቤቶች በተሰበሰበው መረጃ መሰረትም፣ በአካባቢው በድምሩ 317 ዘመናዊ፣ 50 የሸግግር እና 2652 ባህላዊ የንብ ቀፎዎች እንደሚኖሩ ይታመናል።

የአካባቢው ነዋሪ ከንብ እርባታው ጎን ለጎን የቤት እንስሳትን አርብቶ ይጠቀማል። በአሁኑ ወቅት በአካባቢው የሚረቡት የቤት እንስሳት በትሮፒክ አካባቢ ከሚረቡ የቤት እንስሳት መጠን ጋር ሲማዘኑ 47,025 እንደሚደርሱ ይገመታል። የቀንድ ከብት፣ በግ፣ ፍየልና ዶሮ ነዋሪው በዋናነት ከሚያረባቸው የቤት እንስሳት መካከል በቀዳሚ ተጠቃሾች ናቸው።፤ በአካባቢው በስፋት የሚገኘው ጓሳ ሳር፣ ለእነዚህ የቤት እንስሳት ዋነኛ መኖ ነው።

ጓሳ ሳር ከቤት እንሰሳት መኖነት በተጨማሪ፣ በአካባቢው ነዋሪ የእለት ተእለት ህይወት ውስጥ ያለው ጉልህ ድርሻ በቀላሉ የሚታይ ነው። ይህ የሳር ዘር በአሁኑ ወቅት ለቤት ክዳን፣ ለመኝታ ፍራሽ፣ ለማሰሪያ ገመድ መስሪያና ለሌሎች በርካታ ተግባራት እያገለገለ ይገኛል። በዚህ ምክንያት፣ ጓሳ ሳር የአካባቢውን ህብረተሰብና አስተዳደር አካላት ልዩ ትኩረት እና ጥበቃ እንዲያገኝ አድርጎታል።

በዚህ ረገድ፣ የአማራ ሳይንት ወረዳ ቀበሌ 07፣ 08፣ 09 እና 010 በየአካባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮ እጽዋት መብቀያ ቦታዎችን ከሰውና ከቤት እንስሳት ንክኪ ከልሎ በመጠበቅ እና የደረሰ ጓሳ ሳርን አጭዶ ለአካባቢው ነዋሪና ለጋራ ማህበራዊ አገልግሎቶች በማቅረብ እየሰሩት ያለው ስራ ለአብነት የሚጠቀስ ነው። የአካባቢው ነዋሪም፣ "የተቀረጠፉ" [ከሰውና የቤት እንስሳት ንክኪ የተከለከሉ] መሬቶችን ድንበር በማክበር ለጥበቃው ተገቢውን ድጋፍ የማድረግ ልምድ አዳብረዋል።

ይሁን እንጂ፣ በአካባቢው ያለው የመኖሪያ መንደር፣ እርሻና የግጦሽ መሬት መስፋፋት በተፈጥሮ ሀብቱ ላይ ያሳደሩት ጉዳት እጅግ ጎልቶ ይታያል። ለዚህ ችግር መባባስ በአካባቢው ያለው ከፍተኛ የሰው ውልደት መጠን ዋነኛ ምክንያት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

በ2001ዓ/ም በተካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ መሰረት የነዋሪዎች ውልደት መጠንን ለመመልከት የሚያስፈልገውን የቀበሌዎቹ ነዋሪዎች ብዛት በእድሜ ለይቶ የሚገልጽ መረጃ ማግኘት አልተቻለም።፣ ነገር ግን፣ የጥናቱ አካባቢ አማካኝ የቤተሰብ ስፋት 4.6 ሰው መሆኑን የሚጠቁም መረጃ በአባሪ 1 ላይ ይገኛል። ይህ ሰፊ የቤተሰብ መጠን በጥናቱ አካባቢ ያለውን ከፍተኛ የሰዎች ውልደት አመላካች ነው።

በአንፃሩ፣ ተዳፋታማ መሬቶች በሚበዙበት በዚህ አካባቢ በቤተሰብ ደረጃ ያለው አማካኝ የእርሻ መሬት ይዞታ ከ 0.8 ሄ/ር የማይበልጥ ነው። አብዛኛው ነዋሪ ይህን አነስተኛ መሬት በባህላዊ መንገድ በማረስ የሚያገኘው ምርት፣ ለቤተሰቡ አመታዊ ፍላጎት የሚበቃው አለመሆኑን በመስክ ከተገኙ አንዳንድ ነዋሪዎች ጋር ከተደረገው መደበኛ ያልሆነ ውይይት ለመረዳት ይቻላል።

ከዚህ ውይይት ይበልጥ ለመገንዘብ የሚቻለው ፣ የአካባቢው ዱር እንስሳት መጠለያዎች ፣በተለያዩ ጊዜያት ህጋዊና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ፡

- *የቤተሰብን አመታዊ ፍላጎት ለማሟላት በታረሱ መሬቶች ፣*
- *አዲስ ቤተሰብ ለሚመሰርቱ ወጣቶች እርሻና የቤት መስሪያ አገልግሎት መመናመናቸው ።*

ህጋዊ መሰረት ካላቸው ተግባራት መካከል ለተደራጁ ወጣቶች የደን ልማት በየወረዳዎቹ የተሰጠው መሬት ዋነኛው ነው። ይሁን እንጂ፣ ወጣቶቹ በረጅም ጊዜ ከደን ልማት የሚያገኙትን ጥቅም በመተው፣ መሬቶቹን ለሰብል እርሻ እየተጠቀሙበት ይገኛል።

በሌላ በኩልም፣ ከግብርና ጽ/ቤቶች በተገኘው መረጃ መሠረት፣ በአሁኑ ወቅት በጥናቱ ቀበሌዎች ያለ 1 ሄክታር የግጦሽና የግብርና መሬት የሚያገለግለው የቤት እንስሳት መጠን በቅደም ተከተል አቀማመጣቸው ከትሮፒክ አካባቢ 3.58 እና 1.6 እንስሳት ጋር ተመጣጠሰኝ የሆነ ነው። ይህ መጠን በከፍተኛ (ደጋማ) ቦታዎች መኖር ከሚገባው 0.9 መጠን ከሁለት እጥፍ በላይ የሚበልጥ ነው።

በዚህ ምክንያት፣ በአሁኑ ወቅት የአካባቢውን ዱር እንስሳት ተራራማና ገደላማ እስከሆኑት የዱር እንስሳት መጠለያዎች ድረስ ለግጦሽ ተሰማርተው መመልከት እጅግ በጣም ቀላል ነው። ይህ ልቅ ግጦሽ፣ ከእርሻ የመኖሪያ መንደሮች መስፋፋት ጋር ተዳምሮ የዱር እንስሳቱ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ አነስተኛ መጠለያዎች ውስጥ ተበታትነው እንዲኖሩ ምክንያት ሆኗል። የዱር እንስሳቱን ነፃ ዝውውርና የእርስ በርስ ግንኙነትን ገድቧል። የአካባቢውን ተፈጥሯዊ ውበት እንዲመናመን በማድረግ ላይ ይገኛል።



ምስል 7. በሳይንት እና ለጋምቦ ወረዳዎች የሚገኙ የቤለጨማና አረር ሜዳ መንደሮች

8.1.3. የጎላቴና ታቦር ተራራዎች ተፈጥሮዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ የቱሪዝም መስህብ ሃብቶች

በጥናቱ ትኩረት ተሰጥቷቸው የተዳሰሱት አካባቢዎች ለበርካታ ብርቅዬና በመጥፋት አደጋ ውስጥ ላሉ ዱር እንስሳት መጠለያ በመሆን በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቀው የአገራችን አፍሮ አልፓይን ስነምህዳር አካል ነው። በመሆኑም፣ ቀይ ቀበሮና ጭላዳን ጨምሮ፤ ከላይ በተራ ቁጥር .... የተዘረዘሩት ዱር እንስሳትና እጽዋቶች ለአካባቢው ቀዳሚ መስህብ ሀብቶች ናቸው።

በሌላ በኩልም፣ ለዱር እንስሳት ተገን አድርገው የሚኖሩባቸው ቁጥቋጦዎች፣ ኮረብቶችና ተራሮች ተፈጥሯዊ ውበት የአካባቢው ልዩና ተጨማሪ መስህብ ሀብቶች ናቸው። እስከ አይን እይታ መጨረሻ ድረስ ተሰናስሎ የተዘረጉት የሳይንት ከፍተኛ ቦታዎች፣ ተራሮችን በመውጣት የሚረኩ በርካታ አለም አቀፍ ቱሪስቶችን ትኩረት መሳብ ይችላሉ። ከባህር ጠለል 4,280 እና 3,821 ሜትር ከፍታ ያላቸው የጎላቴና ታቦር ተራሮች የዚህ ሰንሰለት አካል ናቸው። በአማራ ሳይንት ወረዳ የሚገኙት የቀበሌ 08፣ 09 እና 010 ጓሳ መሬትና ኮረብታማ ቦታዎች፤ እንዲሁም በለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች ሰፊ የጨረፈ ቁጥቋጦ፣ በዱር እንስሳት መጠለያዎች የእግር ጉዞ በማድረግ ለሚረኩ ጎብኚዎች የተመቹ ናቸው።

ከተፈጥሯዊ ሀብቱ ጎን ለጎን፣ በጥናቱ አካባቢ ካለው ሰፊ ባህላዊ እሴት ጋር፣ ያገራችንን ቀደምት የባህል፣ የስልጣኔና ታሪካዊ ሁነቶች ገላጭ የሆኑ በርካታ ቅርሶች በታሳቢ ጥብቅ ቦታው የጉዞ መስመር ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል፣ እጅግ አስገራሚና ማራኪ የሆኑ በርካታ ቅርሶችን አሰባስቦ የያዘው የተድባበ ማርያም ቤተክርስቲያን፣ በ335ዓ/ም የታነፀው የቤተ ማርያም ፍልፍል ገዳም፣ በ12ተኛ ክፍለ ዘመን ከፍልፍል ዋሻ የተሰራው የፋላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን እና የአፄ ቴዎድሮስ ጀግንነታዊ ተጋድሎዎች መገለጫ የሆነው የመቅደላ አምባ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ 2 በድንበር ማስፋፊያው አካባቢና የጉዞ መስመር ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ባህላዊና ታሪካዊ መስህብ ሀብቶች፣

ተ.ቁ	የሚገኝበት ወረዳ	ዝርዝር	ልዩ የሆነው መስህባዊ ሀብት መገለጫ
1.	አ. ሳይንት	የተድባበ ማርያም ቤተክርስቲያን	የቤተክርስቲያኗና የቀደምት ነገስታት መገልገያ የነበሩ በርካታ ቅርሶች
2	ተንታ	የጃፋ መድሐኔ አለም ቤተክርስቲያን	በአብርሀ ወ አፅብሐ ዘመን የተገነባው ህንፃ እና፣
		የቤተ ማርያም ገዳም	ከፍልፍል ዋሻ በ2ተኛው የኢኦቤክ ጳጳስ /አቡነ ሙሴ/ የተገነባው ህንፃ እና በውስጡ ያሰባሰበው የብራና መጽሐፍትና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መገልገያ ቅርሶች፣
3		የፋላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን	ከፍልፍል ዋሻ በ 12ተኛው ክፍለ ዘመን የተገነባው ህንፃ እና እና በውስጡ ያሰባሰበው የብራና መጽሐፍትና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መገልገያ ቅርሶች፣
4		የመቅደላ አምባ ታሪካዊ ቦታዎች	አፄ ቴዎድሮስ በ1868ዓ/ም ከእንግሊዞች ጋር ያደረጉትን ጀግንነታዊ ተጋድሎዎችን የሚዘክሩ ታሪካዊ ቦታዎች
5.		የታች ተንታ ሚካኤል ቤተክርስቲያን	በንጉስ ሚካኤል የተገነባው ህንፃና በውስጡ ያሰባሰበው የቤተክርስቲያን መገልገያ ቁሳቁስ፣
6.	በ3ቱም ወረዳዎች	አሁን በአካባቢው ያለው ማህበራዊ እሴቶች	የአካባቢው ነዋሪ የአኗኗር፣ የአመጋገብና አምልኮ ስርአት

ስለዚህ፣ የቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክ [የቦሳብፓ] ድንበር ወደ ታቦርና ጎላቴ ታሳቢ ጥብቅ ቦታ ማስፋፋት፣ የፓርኩን የቱሪዝም እንቅስቃሴ በአካባቢው ከሚገኙ ባህላዊና ታሪካዊ መስሕቦች ጋር አስተሳስሮ ለማልማት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡

ከዚህ ባሻገር፣ የፓርኩን ድንበር ለታሳቢ ጥብቅ ቦታው ወደ ተጠኑት ቦታዎች ማስፋፋትና ማጠናከር የአካባቢውን ተፈጥሯዊ ውበት ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ፣

1. *በቦሳብፓ ድንበር ዙሪያ የሚገኙ የሳይንት ሰንሰለታማ ተራሮች እና፣ በተፈጥሮ ሀብት ይዘትና ውበታቸው ማራኪ የሆኑ የአማራ ሳይንት፣ ለጋምቦና ተንታ ወረዳ አካባቢዎች በፓርኩ አስተዳደር ተጠብቀው እንዲለሙ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤*

2. *የድንበር ማስፋፊያው በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ አነስተኛ መጠለያዎች ተነጣጥለው የሚኖሩ ዱር እንስሳትን ነፃ ዝውውርና የእርስ በእርስ ግንኙነትን በማጠናከር፣ ለጎብኚዎች እይታ ምቹ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።*



ምስል 6. በሳይንት ወረዳ በተድባበ ማሪያም ከሚገኙ ቅርሶች በከፊል

ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንያቶችና ጊዜ በጥናቱ አካባቢ እየተስፋፋ ያለው የእርሻና ግጦሽ መሬት ከመኖሪያ ቤት ግንባታ ጋር ተዳምረው በተፈጥሮ ሀብቱ ላይ ያሳደሩት ጉዳት እጅግ ጎልቶ ይታያል። በደን ክልሉ ውስጥ ከ123 ሄ/ር በላይ የወል መሬት በህገ ወጥ መንገድ የታረሰ ሲሆን ከ75 በላይ የቤት እንስሳት መጠበቂያ የደረባ ቤቶች ይገኛሉ። በቤሌጨማና አረር ሜዳ መንደሮች ምክንያት መተላለፊያዎቹ በመዘጋታቸው በአካባቢው የሚገኙ ብርቅዬና ሌሎች ዱር እንስሳት በየቦታው በሚገኙ አነስተኛ የተፈጥሮ ደን መጠለያዎች ውስጥ ተነጣጥለው እንዲኖሩ አድርጓል። በዚህ ረገድ፣ በቦረና፣ ሳይንት፣ በለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች ተነጣጥለው የሚኖሩት የቀይ ቀበሮና ጭላዳ ዝንጀሮ ለአብነት የሚጠቀሱ ብርቅዬ የዱር እንስሳት ናቸው። በበሌጨማ በአጠቃላይ 26 ቤቶች (16 ቆርቆሮና 10 የሳር) የሚገኙ ሲሆን በመንደሩም 16 የቤተሰብ መሪዎች (ወ 10 ሴ 6) እና 53 ነዋሪዎች (ወ 19 ሴ 34) ይኖሩባታል። ቀጥሎ በሚገኘው የአረር ሜዳ መንደር 32 ቤቶች (12 የቆርቆሮ 20 የሳር) የሚገኙ ሲሆን 40 ነዋሪዎች (ወ 19 ሴ 21) ይኖሩባታ።

8.1.4. በጎላቴና የታቦር ተራራዎች የተፈጥሮ ደን ላይ እየደረሱ ያሉ ችግሮች

1. **የእርሻ መስፋፋት፡-** በሳይንት፣ ቦረና ለጋምቦና ተንታ ወረዳዎች የወል መሬቶች ወደ እርሻ ቦታነት እየተቀየሩ ስለሆነ ቀይ ቀበሮና ጭላዳ አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ሌላ ቦታ እንዲሰደዱ ወይም ጭርሶ እንዲጠፉ እያደረገ መሆኑ፣
2. **የዱር እንስሳት መተላለፊያ በሰፈራና በእርሻ መዘጋት፡-** ታሣቢ ጥብቅ ስፍራው በበሌጨማና አረር ሜዳ መንደሮች እንዲሁም በእርሻ የተቆራረጠና የተጣበበ በመሆኑ ወደ ፊት ለዱር እንስሳት እንቅስቃሴ አስቸጋሪ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ፣



ምስል 8. በለጋምቦና ተንታ ወረዳ ልቅ ግጦሽ፣ ጓሳ አጨዳና ህገ ወጥ እርሻ ተዕዕኖ

3. **ከፍተኛ ልቅ ግጦሽ፡-** በሁሉም ታሣቢ ጥብቅ ስፍራዎች ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የቤት እንስሣት ዘልቀው የሚገቡ መሆኑና ከ75 በላይ የደረባ ቤቶች (በሳይንት ወረዳ 71 እንዲሁም በለጋምቦ ወረዳ 4) በደን ክልሉ ውስጥ መኖራቸው፣
4. ለደን ልማት በሚል ዓላማ ለገጠር ወጣቶች የተሰጠው ሰፊ የደን መሬት ለእርሻ እየዋለ መሆኑ፣
5. **ጓሳ አጨዳና ደን ጭፍጨፋ፡-** የአካባቢው ህብረተሰብ ጅብራውንና ጨረፈውን ለቤት ግንባታና ለማገዶ ስለሚጠቀምበት ከፍተኛ ውድመት እየደረሰበት መሆኑና እንዲሁም ጓሳው ለከብት መኖ፣ ለቤት ክዳንና ለጉዝጓዝ ስለሚታጭድ በከፍተኛ ሁኔታ የተጎዳ መሆኑና ለቀይ ቀበሮ በምግብነት የሚያገለግሉትን የአይጥ ዝርያዎች የመራቢያ ሥፍራ በመረበሽ በአካባቢው ላይ ከፍተኛ ተዕዕኖ እያደረሰ መሆኑ፣

8.1.5. የጎላቴና የታቦር ተራራዎች ወደ ቦ/ሳ/ብ/ፓርክ የመካተትና የመከለል አቅም

ከዳሰሳ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክትው የጎላቴና ታቦር ተራራዎች በአብዛኛው ተፈጥሮዊ ይዘታቸው ያለ ሲሆን ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ በተመሳሳይ ከፍታ በተፈጥሮ ይዞታቸው አሉ ከሚባሉ ጥቂት አካባቢዎች መካከል የሚመደቡ በመሆናቸው ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ቢደረግላቸው ለዱር እንስሳት ደህንነት፣ ለሥርዓተ ምህዳር ጥበቃና ለቱሪዝም ከሚሠጡት ጥቅም ባሻገር ለትምህርትና ለበርካታ ሣይንሣዊ ምርምሮች በሚኖራቸው አስተዋጽዖ ወደ ፓርኩ ሊከለሉ የሚገባቸው ልዩ ተፈጥሮዊ ይዘት ያላቸው ቦታዎች ናቸው።

1. ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች

የአለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት /IUCN/ ለጥብቅ ስፍራነት ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የታቦርና ጎላቴ ተራራዎች በፓርኩ ክልል ውስጥ ለመካተት የሚያስችላቸውን ነጥቦች የሚያሟሉ የተፈጥሮ ዕፅዋትና የዱር እንስሣት ማዕከል እንደሆኑ በሚከተለው ሁኔታ ተዘርዝረዋል።

1. ***<u>ወካይ የሆነ ስነ ምህዳር (Representativeness)፦</u>*** የጎላቴና ታቦር ተራራዎች እንደ ቦ/ሳ/ብ/ፓርክ በአፍሮ ትሮፒካል ከፍተኛ በታዎች /Afrotropical highlands/ ስርዓተ ምህዳር ይጠቃለላሉ፡፡ ይህ ስርዓተ ምህዳር ለክለት የተጋለጠና ጥበቃን የሚሻ ሥርዓተ ምህዳር ነው፡፡ በፓርኩ ክልል ውስጥ የሚገኙት የተለያዩ ትላልቅ ዛፎች፣ አጥቢ እንስሣትና አዕዋፍትም በተመሳሳይ ሁኔታ በእነዚህ አካባቢዎችም የሚገኙ ሲሆን በሃገራችን ብቻ ከሚገኙ ታላላቅ አጥቢዎች 57% ቱን አቅፎ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም በአደጋ ላይ ያለችው የሶረኔ ቆቅ የጥበቃ ሽፋን ልታገኝ የምትችለው በእነዚህ አካባቢዎች ጭምር ነው፡፡ በአገራችንም ሆነ በክልላችን እንዲህ ባለ ከፍተኛ አልትቲዩድ መሬቶች ተፈጥሯዊ የብዝሃ-ሕይወት ገጽታቸው ሙሉ ለሙሉ ተቀይሮ ለግብርና ስራ የዋሉ ሲሆን እነዚህ አካባቢዎች ግን እስካሁን ድረስ ተፈጥሯዊ ይዘታቸውን ከሞላ ጎደል ጠብቀው የቆዩ በመሆኑ ወካይነታቸው የጎላ ነው፡፡ በተጨማሪም በከፍተኛ አልትቲዩድ የሚገኙ ደኖች /Afroalpine ecosystem/ በተለይ በክልላችን በዚህ መጠን የትም ቦታ የማይገኙ በመሆኑ እነዚህ አካባቢዎች በይዘታቸው ለየት ያሉና በክልላችን ለመጥፋት የተቃረቡ ሥነ ምህዳርን የሚወክሉ በመሆናቸው ወደ ፓርኩ ሊከለሉና ሊጠበቁ ይገባል፡፡
2. ***<u>የብዝሃ ህይወት ክምችት (Diversity)፦</u>*** የጎላቴና ታቦር ተራራዎች በውስጣቸው ከ15 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሣት፣ ከ40 በላይ የአዕዋፍት ዝርያዎችና ከ20 በላይ የተለያዩ የእፅዋት ዝርያዎችን ያቀፈ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 3 ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት፣ የሶረኔ ቆቅን ጨምሮ 4 አዕዋፍትና 11 የእፅዋት ዝርያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡
3. ***<u>ማራኪና ለየት ያለ የተፈጥሮ ገፅታ (Distinctiveness)፦</u>*** የጎላቴና ታቦር ተራራዎች በርካታ የዱር እንስሣት የዱር እፅዋትና ማራኪ ገፅታ ያላቸው ከፍተኛ የተራራ ሰንሰለቶች፣ ሸለቆዎች፣ ወንዞች፣ ሰፋፊ ዋሻዎች እና ሌሎች የተፈጥሮ ገፅታዎች ያሏቸው ሲሆን የታቦር ተራራ (3821ሜ)ና የጎላቴ ተራራ (4280 ሜ) በራሳቸው የቦታዎችን ማራኪነት የሚያጐሉ የተፈጥሮ ስጦታዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህን አካባቢዎች ባሉበት ሁኔታ በመጠበቅና ተፈጥሯዊ ውበታቸውን በማጉላት ከቱሪዝም የሚገኘው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም ህገ-ወጥ በሆነ መልኩ በእነዚህ አካባቢዎች የሚከናወኑ ተግባራትን በመከላከልና በመቆጣጠር ቦታዎችን መከለልና መጠበቁ በአስከፊ ሁኔታ እየተስፋፉ ያሉ ህገ ወጥ እርሻዎችንና ሰፈራዎችን፣ ልቅ ግጦሽና የደን ጭፍጨፋዎችን የሚገታና የሚስቀር ነው፡፡ የእነዚህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች የመሬት አቀማመጥ ማራኪ ገፅታ ያላቸውን ከፍተኛ ቦታዎች የያዘ ሲሆን በተለይ በጎላቴ ተራራ አካባቢ የማንኛውንም ቀልብ የሚሰብ ‹‹**የአደባባይ መስክን**›› ይዞ ይገኛል፡፡ ይህ መስክ ከቦ/ሳ/ብ/ፓርክ ልም መሰክ የሚበልጥ ሲሆን በጓሳ፣ ጨረፈ፣ ጅብራና አስታ የተሸፈነና ከ4200 ሜ ከፍታ በላይ በሆነ አካባቢ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ ይህ አካባቢ በደቡብ ወሎ ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች ከፍተኛው ቦታ ሲሆን ከፍተኛ የቀይ ቀበሮ ቁጥር የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡ በዚህ አካባቢ ከቀይ ቀበሮ በተጨማሪ ጭላዳ ዝንጀሮና የስታርክ ጥንቸል በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ አጥቢ እንስሳት ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም ጋጋኖ፣ ቅልጥም ሰባሪ፣ ሶረኔ ቆቅ የመሳሰሉ የአእዋፍት ዝርያዎች ይኖሩበታል፡፡
4. ***<u>ስነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ (Ecological Importance)፦</u>*** የአካባቢውን ብዝሃ ህይወት የአፈር ለምነት የውሃና አየር ሁኔታ ተሻሽሎና ተስተካክሎ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራውና በአካባቢው የሰብ አፍሮ አልፓይንና የአፍሮ አልፓይን ሰርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡ በአካባቢው ያለውን ያልተስተከለ የዝናብ ሥርጭት የተስተካከለ እንዲሆን በእጅጉ ያግዛል፡ አካባቢያዊ ውበትን ይጨምራል፣ ማራኪ የሆነ ገፅታ ይኖረዋል፡፡ ይህ አካባቢ በክልሉ ውስጥ ለመጥፋት የተቃረቡትን ኮሶ፣ ዝግባና የወይራ ዛፎችን ተፈጥሮዊ በሆነ ገፅታቸው ለመጠበቅ ያስችላል፡፡ በውስጡ የሚኖሩ የዱር እንስሳትና እፅዋት በዓይነትም ሆነ በብዛት በተፈጥሮዊ አኗኗራቸው ተጠብቀው፣ ተደጋግፈውና ተመጣጥነው እንዲኖሩ ያስችላል፡፡ በአካባቢው የምነጮች፣ወንዞችና ጅረቶች ፍሰት የተስተካከለና አስተማማኝ እንዲሆን የደርጋል፡፡

5. ***<u>በታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ላይ እየደረሱ ያለ አሉታዊ ተፅዕኖዎች /</u>***Degree of interference/

1. በታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች አጐራባች ያሉ ቀበሌዎች መሬት በአፈር ክለት ምክንያት የአፈር ለምነቱን ያጣ በመሆኑና ምርታማነቱም ዝቅተኛ በመሆኑ ተጨማሪ የእርሻ መሬት ለማግኘ ት ከፍተኛ የእርሻ መሬት መስፋፋት መከሰቱ፣
2. ታሣቢ ጥብቅ ስፍራዎች በሰፈራና በእርሻ የተቆራረጡና የተጣበቡ በመሆናቸው ለዱር እንስሳት እንቅስቃሴ አስቸጋሪ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ (1ኛ. የቤሌጨማ መንደር፣ 2ኛ. የአረር መንደር፣ 3ኛ. የጎላቱንና የጋያ ተራራን የሚያገናኘው የዱር እንስሳት መተላለፊያ/ኮሪዶር/ በእርሻ የተጣበበ መሆኑ)፣
3. ጓሳ በሚገኝበት የታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች አካባቢ አሁንም ጓሣን አጭዶ የመጠቀም ከፍተኛ ፍላጎት ያለ መሆንና ይህም ለቀይ ቀበሮ በምግብነት የሚያገለግሉትን የአይጥ ዝርያዎች የመራቢያ ሥፍራ የሚረብሽና በአካባቢውም ላይ ተፅዕኖ የሚያደርስ መሆኑ፣
4. በከፍተኛ የልቅ ግጦሽ ምክንያት ወደ ታሣቢ ጥብቅ ስፍራዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የቤት እንስሣት ዘልቀው የሚገቡ መሆኑ፣ ከዱር እንስሣቱ ጋር የመኖ ሽሚያ (Competition for food) መኖሩና ከቤት እንስሣትም ጋር እረኞች ውሻ ይዘው ስለሚሄዱ ቀይ ቀበሮዎችን በውሻ ማደንና ለእብድ ውሻ በሽታ እንዲጋለጡ የሚያደርግ መሆኑ፣
5. በስፋት የተስፋፋ ነው ባይባልም ወደ ታሣቢ ጥብቅ ስፍራዎች በመግባት ለግንባታና ለማገዶ አገልግሎት የሚውል ዛፎችን መቁረጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ አየጨመረ መሄድ፣
6. ለደን ልማት በሚል ዓላማ ለገጠር ወጣቶች የተሰጠው ሰፊ የደን መሬት ለእርሻ ዕየዋለ መሆኑ፣
7. ለበግ እርባታ ኢንቨስትመንት በሚል ከፍተኛ የቀይ ቀበሮና የጨልዳ ዝንጆሮ መራቢያና መመገቢያ ቦታ ለግል ባለሃብቶች እየተሰጠ ያለ መሆኑ፣

6. ***<u>የቦታዎች ሳይንሳዊ ጠቀሜታ</u>*** **/Scientific and monitoring uses/**፡-የዱር እንስሳትንና ዕፅዋትን የተፈጥሮ አካባቢያቸውን ለማጥናት በሞዴልነት ያገለግላል፡፡ የዱር እንስሳት በሽታ ክስተትን በተለይም የእብድ ውሻ በሽታንና ሌሎች በሽታዎችን በቤትና በዱር እንስሳት ፣መካከል ያለውን ስፍርጭት ለማወቅ ያግዛል፡፡ ለአካባቢ ክትትል በሚኖረው ጠቀሜታ የተፈጥሮ ሚዛን ለውጥን ለመለካት ያስችላል፡፡ የዱር እፅዋት ናሙናና ተፈጥሮዊ ዕድገትንና በሰዎች ጣልቃ ገብነት የሚመጣውን ለውጥ ለመለካት ያስችላል፡፡
7. ***<u>የቦታ ስፋት</u>*** **/area size/**፡-ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከቦ/ሳ/ብ/ፓርክ ጋር የተያያዘ ሲሆን በውስጡ በያዛቸው የዱር እንስሳትና ዕፅዋት ዓይነትና ብዛት ተመሳሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ስፋቱ አሁን ካለው የፓርኩ ስፋት 5 እጥፍ ይበልጣል፡፡ ስለዚህ በፓርኩና በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ የሚገኙ የዱር ዕፅዋትና እንስሳት ጠብቆ ለማቆየትና ፓርኩን ለማስፋፋት ይህንን አካባቢ ወደ ፓርኩ መከለል ያስፈልጋል፡፡
8. ***<u>ቅርጽ (መጠነ ዙሪያ)</u>*** **/**shape/፡- ጥብቅ ስፍራዎች በሚቋቋሙበት ጊዜ በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መጠነ ዙሪያ እንዲኖራችው ይጠበቃል፡፡ ሆኖም ግን የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የፈጥሮ ደን በአብዛኛው ተራራማ ሰንሰለቶች ላይ የሚገኝ፣ ዙሪያውን የእርሻ መሬትና መንደር የበዛበት በመሆኑና ደጀን ስሌለለው፣ የዳር ድንበር መጣገባትና ቅርፁም ሾጣጣ በመሆኑ ከስፋቱ አንፃር ሲታይ ረጅም መጠነ ዙሪያ አለው፡፡ሆኖም ዋናው ደን በገደልና በተራራዎች ላይ የሚገኝ በመሆኑ ለቁጥጥርና ጥበቃ አመችነት አለው፡፡
9. ***<u>በውስጡ የሚገኙ ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች</u>*** **/Endemicity/ ፡-** ከታላላቅ አጥቢዎች ውስጥ ቀይ ቀበሮና ጭላዳ ዝንጆሮ፣ ከአእዋፋት መካከል ጋጋኖና ሶረኔ ቆቅ፣ እንዲሁም ዕፅዋት መካከል ደግሞ ጅብራ፣ ጓሳና አምጃ የሚገኙበት በመሆኑ መከለልና መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

2. የተጠኑ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ወደ ፓርኩ አስተዳደር ጥበቃ ውስጥ ቢካለሉ የሚሠጡት ጠቀሜታ

1. ስርዓተ ምህዳራዊ ጠቀሜታ (Ecosystem values)፡-

ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ያላቸው ግብግብ ዘለቄታዊ የተፈጥሮ ገፅታ መኖርን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ ያስችላል፡፡ በዚህም ዘለቄታዊ ጥቅም አለው፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ውስጥ እና በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡ ለመጥፋት የተቃረቡትን ኮሶ፣ ዝግባና የወይራ ዛፎችን ተፈጥሮዊ በሆነ ገፅታቸው ለመጠበቅ ያስችላል፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሚዛኑን ጠብቆ እንዲኖር ያስችላል፡፡ የአካባቢው የአየር ሚዛን እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡ በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሣትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት ይጠበቃሉ፡፡ በተለይም በአገራችን ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት ባሉበት ሁኔታ ተጠብቀው እንዲኖሩና እንዳይጠፉ ያደርጋል፡፡ ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚወጡ ምንጮችና ጅረቶች ዓመቱን በሙሉ እንዲፈሱ ስለሚያስችል የተስተካከለ የውሃ ሃብት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

2. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ (Economical values)፡-

በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከጐብኝዎችጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ ገቢዎች ለህብረተሰቡና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጥበቃ ሠራተኝነትና በተፈቀደ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ በመሣተፍ የአካባቢው ህብረተሰቡ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ በታሳቢው ጥብቅ ስፍራ ደጀን አካባቢ ለሚካሄዱ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ሰለዘላቂ የአካባቢ ጥበቃና ልማት ጠቀሜታና አስፈላጊነት ትምህርት ይሰጣል፡፡ ከምርምርና ሣይንሣዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፡፡ የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴ ስለሚስፋፋና ስለሚጠናከር ለአካባቢው ህብረተሰብ አማራጭ የገቢ ምንጭ ይሆናል፡፡ የአካባቢው የአየር ሚዛን ስለሚስተካከልና ስለሚጠበቅ ከእርሻ ስራ የሚገኘው ገቢ ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል፡፡ በሆቴልና በሌሎች መስተንግዶ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ለቱሪስቶች አግልግሎት በመስጠት በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ኑሮቸውን እንዲያሻሽሉ ያግዛል፡፡

3. ማህበራዊ ጠቀሜታ (Social values)፡-

አለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህል ልውውጥ እንዲኖር ያስችላል፡፡ ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጋር ተያይዞ በአካባቢው የመሠረተ ልማቶች መስፋፋት ስለሚኖር ት/ቤት፣ የኢኮ-ቱሪዝም ማህበራት መደራጀት፣ የሰውና የእንስሳት ጤና ኬላዎች ግንባት ወዘተ ይኖራል፡፡

4. ሳይንሳዊ ጠቀሜታ (Scientific values)፡-

የዱር እንስሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈጥሮዊ አኗኗሯቸው ለሚደረግ ምርምር በማዕከልነት ያገለግላል፡፡ የባህላዊ መድኃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሳይንሳዊ ጥናትም ለማከሄድ ይረዳል፡፡ በመጥፋት ላይ ላሉ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት ሳይንሳዊ ምርምር ሊደረግ ይችላል፡፡ የተፈጥሮ ደኑና ገፅታው ለአካባቢያዊ ደህንነት፣ ለብዝሃ ህይወትና ለስርዓተ ምህዳር መስተካከል ያላቸው አስተዋፅዖ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ ለሚደረጉ ምርምሮች የመስክ ላቦራቶር ሊሆን ይችላል፡፡

5. የተፈጥሮዊነት ጠቀሜታ (Naturalness)፡-

ምንም እንኳን አካባቢው ከሰው ልጆች ተፅዕኖ ነፃ ባይሆንም በአንፃራዊነት ከአካባቢው የተሻለ በመሆኑ ተፈጥሮዊነትን ጠብቆ ለማቆየት ያስችላል፡፡ በውስጡ ያሉትን ብዝሃ ሕይወትና ሌሎች (አፈር፣ ውሃና የመሬት አቀማመጥ) በተፈጥሮዊ ገፅታቸው ቆይተው ዘለቄታዊነት ባለው መልኩ ጥቅም እንዲሰጡና ተፈጥሮዊ ይዘታቸው እንዳይጓደል ይረዳል፡፡

6. የመስህብነት ጠቀሜታ (Aesthetic values)፡-

አካባቢው የሰው ልጆችን ቀልብ ሊገዙ የሚችሉ መመልከቻ ቦታዎችና ማራኪ ገፅታዎች የያዘ ሲሆን ከእነዚህም ቦታዎች ውስጥ እንደ ታቦር፣ አሞራ ገደል፣ ጎላቴ፣ ጋያ፣ ወዘተ የመሳሰሉ የመመልከቻ ታራራዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ አካባቢዎች እራሳቸው ማራኪ ከመሆናቸው ባሻገር የደኑን ስብጥርና ሽፋን እንዲሁም የብዝሃ ህይወት ክምችት ለመቃኘት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ በተፈጥሮ ይዘቱ

ለጎብኝዎች ማራኪ የሆነ መዝናኛና እርካታ ሊሰጡ የሚችሉ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች ያሉበት ነው ማለት ይቻላል፡፡
የቦ/ሳ/ብ/ፓ ድንበር መስፋፋትና መጠናከር የፓርኩና የአካባቢውን የቱሪዝም እንቅስቃሴና እድገት ለማፋጠን ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ፣ የድንበር ማስፋፊያው የፓርኩና የአካባቢውን ተፈጥሮዊ ውበት ለማጎልበት የሚፈጥረው ምቹ ሁኔታ ቀድሞ መጠቀስ የሚችል ነው፡፡ የድንበር ማስፋፊያው ከሚያካትታቸው የሳይንት ሰንሰለታማ ተራሮች በተጨማሪ በተፈጥሮ ሀብት ይዘትና ውበታቸው ማራኪ የሆኑ አካባቢዎች በፓርኩ አስተዳደር ተጠብቀው እንዲለሙ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም ወደፊት ለጉብኝት ወደ ብሄራዊ ፓርኩ የሚመጡ ቱሪስቶች እስከ እይታ አድማስ መጨረሻ ድረስ ሰንሰለት ሰርተው የተዘረጉትን የሳይንት ከፍተኛ፣ ተንታና ለጋምቦ ቦታዎች ወጥቶ በመጎብኘት ወይም በለጋምቦና ተንታ ወረዳ በሰፊና ሜዳማ በሆነው፣ በጨረፌ ቁጥቋጦና ጅብራ ተሸፍኖ እስከሚገኘው የጎላቱ ተራራ ተፈጥሮዊ አካባቢ ድረስ ጉብኝታዊ ጉዞ በማድረግ ይበልጥ እንዲረኩ ያግዛል፡፡

የድንበር ማስፋፊያው በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ አነስተኛ መጠለያዎች ተጎጣጥለው የሚኖሩ ብርቅዬ ዱር እንስሳትን ነፃ ዝውውርና የእርስ በእርስ ግንኙነትን በማጠናከር ለጎብኚዎች እይታ ምቹ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ሌላው ተጠቃሽ ፋይዳ ነው፡፡ በፓርኩ ውስጥና ደጀን አካባቢዎች የሚከወኑ የልማትና ጥበቃ ስራዎችን ተከትሎ የአካባቢው ዱር እንስሳት ነፃ ዝውውር እና የእርስ በእርስ ግንኙነት እንደሚጠናከር ይታመናል፡፡ ይህም የአካባቢውን ተፈጥሯዊ ውበትና ማራኪነት ይበልጥ እንዲጎለብት ያደርገዋል፡፡

በሌላ በኩልም ይህ የድንበር ማስፋፊያ የቦሳብፓ ቱሪዝምን በጉዞ መስመር ውስጥ ከሚገኙ ባህላዊና ታሪካዊ መስሕቦች ጋር አስተሳስሮ ለማልማት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡ ከአብርሀ ወ/አጽብሐ ዘመነ መንግስት እስከ የወሎው ንጉስ ሚካኤል (ከ1896-1903ዓ/ም) ድረስ ተሰርተው ለአገልግሎት የበቁት ቤተክርስቲያናትና ገዳማት በውስጣቸው እጅግ በርካታ አስገራሚ ቅርሶችን ይዘው በአካባቢው ይገኛሉ፡፡

እነዚህ ባህላዊ ቅርሶች አፄ ቴዎድሮስ በ1868ዓ/ም ከእንግሊዞች ጋር ያደረጉትን ጀግንነታዊ ተጋድሎን ከሚዘክሩት የመቅደላ አምባ ታሪካዊ ቦታዎች ጋር ተዳምረው የፓርኩና አካባቢውን ጎብኚዎች ፍሰት እና የቆይታ ጊዜ ለማሳደግ የሚያስችል ጠንካራ አቅም እንደሚፈጥሩ ይታመናል ::

8.1.6. ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ለመከለል ያሉ መልካም አጋጣሚዎችና ፈታኝ ሁኔታዎች

1. ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ለመከለል ያሉ መልካም አጋጣሚዎች

- ☞ ታሳቢ ጥብቅ ቦታው ተያያዥነት ባለው መልኩ የIUCN መስፈርት ከሚጠይቀው ዝቅተኛ ስፋት /1000ሄ/ር/ በላይ መሆኑ፣
- ☞ በቦረና ወረዳ 10 ሄ/ር (በአንድ ቀበሌ)፣ በሳይንት ወረዳ 9465 ሄ/ር (በስምንት ቀበሌዎች)፣ በለጋምቦ ወረዳ 6870 ሄ/ር (በሰባት ቀበሌዎች)ና በተንታ ወረዳ 4150 ሄ/ር (በሁለት ቀበሌዎች) በጠቅለላው 20495 ሄ/ር ሊከለለል የሚችል ለዱር እንስሳት መኖሪያነት አመቺ የሆነ በጣም ሰፊ የወል ይዞታ የደን መሬት መኖሩ፣
- ☞ ከፓርኩ ውስጥ ይልቅ ከፍተኛ የቀይ ቀበሮ ቁጥር ከፓርኩ ውጭ በእነዚህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች መኖሩ፣
- ☞ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚገኝባቸው ወረዳዎች የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ቦታው እንዲከለልና በፓርኩ ውስጥ እንዲካተት ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው መሆኑና ከዞን እስከ ቀበሌ

ድረስ የሚገኘው አመራር እና ባለሙያ ለተፈጥሮ ሀብቱ ጥበቃ የሰጠው ትኩረት፣ የፓርኩን ድንበር ለማስፋፋት መሰረት የሚሆን ትልቅ ግባት ነው።

☞ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው እስኪከለል ድረስ ወረዳዎችና ዞኑ ህገ ውጥ እንቅስቃሴዎችን ለማስቆም ያሳወቁን መሆኑ፣

2. **ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ለመከለል ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎች**



የበሌጨማና አረር ሜዳ መንደሮች እንዲሁም የጎላቴንና የጋያ ተራራን የሚያገናኘው የዱር እንስሳት መተላለፊያ/ኮሪዶር/፡- በቤሌጨማ፣ በአረር ሜዳ እና የጎላቴንና የጋያ ተራራዎችን በሚያገናኘው ቦታዎች የተስፋፋው የመንደር ግንባታ፣ የእርሻና የቤት እንስሳት ግጦሽ የፓርኩን ድንበር በተንታና ለጋምቦ ወረዳ እስከሚገኙ ቦታዎች ድረስ ለማስፋፋት በተያዘው እቅድ ላይ ከተጋረጡ ማነቆዎች መካከል ቀዳሚና ዋነኞቹ ናቸው። በአሁኑ ወቅት በእነዚህ አካባቢዎች ይገኝ ከነበረው የአስታና ጓሳ ሳር መብቀያ መሬት ውስጥ፣ አብዛኛው ለመንደር ግንባታ፣ ለእርሻና ለቤት እንስሳት ግጦሽ እየዋለ ይገኛል። በአካባቢው ለዱር እንስሳቱ መጠለያ እና ከነባሩ የፓርኩ ክልል ወደ አዲሱ የፓርክ ክልል መዘዋወሪያ የቀረው አነስተኛ መሬት ወይም ጠባብ ኮሪደር ነው። ስለዚህ በፓርኩ የዱር እንስሳት የእርስ በእርስ ግንኙነትና ዝውውር ላይ ትልቅ እንቅፋት የሚሆነውን ይህን ችግር ለማስወገድ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ትብብር የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ፣

1. **የእርሻ መስፋፋ፡-** በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ሊከለል ከታሰበው የደን መሬት ውስጥ በአዋሳኝ ቀበሌዎች 123 ሄ/ር የታረሰ የወል መሬት መኖሩና ከወዲሁ ካልተገታ የእርሻ መስፋፋቱ የሚቀጥል መሆኑ፣
2. **ልቅ ግጦሽ፡-** በከፍተኛ የልቅ ግጦሽ ምክንያት ወደ ታሣቢ ጥብቅ ስፍራዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የቤት እንስሳት ዘልቀው የሚገቡ መሆኑና ከ75 በላይ የደረባ ቤቶች (በሳይንት ወረዳ 71 እንዲሁም በለጋምቦ ወረዳ 4) በደን ክልሉ ውስጥ መኖራቸው፣
3. **የበግ እርባታ ኢንቨስትመንት፡-** ለበግ እርባታ ኢንቨስትመንት በሚል ከፍተኛ የቀይ ቀበሮና የጨልዳ ዝንጆሮ መራቢያና መመገቢያ ቦታ በተለይም በለጋምቦ (37 ሄ/ር) እና ተንታ (200 ሄ/ር) ወረዳዎች ለግል ባለሃብቶች የተሰጠ መሆኑ እንዲሁም በተንታ ወረዳ 313 ሄ/ር የደን መሬት ተጠንቶ ለግል ባለሃብቶች ሊሰጥ የታሰበ መሆኑና የፓርኩን ድንበር ለማስፋፋት በተያዘው እቅድ ላይ ትልቅ ስጋት የሚፈጥሩ መሆናቸው፣
4. **ለገጠር ወጣቶች የሚሰጠውመሬት፡-** በሳይንትና ተንታ ወረዳዎች ውስጥ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ለደን ልማት በሚል ዓላማ ለገጠር ወጣቶች የተሰጠው ሰፊ የደን መሬት ለእርሻ እየዋለ መሆኑ፣

5. **የፓርኩ የስያሜና ተጨማሪ እስካውት ቅጥር ሁኔታ፡-** ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከተከለለና ወደ ፓርኩ ውሥጥ ከተካተተ በኋላ የፓርኩ የስያሜና ተጨማሪ እስካውት ቅጥር ሁኔታ መፍትሄ የሚሻ ጉዳይ መሆኑ፣
6. **ጊዜ አጠቃቀም፡-** በዳሰሳ ጥናቱ ወቅት የተለየው ቦታ ቶሎ ተከልሎ ህጋዊ እውቅና አግኝቶ እንዲጠበቅ አለማድረግ፣

8.1.7. የጎላቴና ታቦር ተራራዎች በቦረና ሳይንት ብሄራዊ ፓርክ ውስጥ የመከለል ዋና ዓላማ

የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ወደ ፓርኩ የመካለል አቅም ባለው የብዝሃ ህይወት ሃብት፣ ከሚሰጠው ጠቀሜታ እና ካሉት መልካም አጋጣሚዎች አንፃር የተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመፍታት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ ችግሮች ሙሉ በሙሉ እስከተወገዱ ድረስ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚከተሉትን ዓላማዎች የሚያሳካ ይሆናል፡፡

ለብዝሃ ህይወት ጥበቃ፡- የቀይ ቀበሮና ጭላዳ ዝንጀሮ መመገቢያ፣ መራቢያና መኖሪያ የሆነው የሰብ አፍሮ አልፓይንና የአፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳር እንዲለማና እንዲጠበቅ፣

ለትምህርትና ምርምር፡- ብዝሃ ህይወትን፣ የሰብ አፍሮ አልፓይንና የአፍሮ አልፓይን ስርዓተ ምህዳር አካባቢዎችን ለትምህርትና ምርምር ማዕከል በማድረግ በዘርፉ የሚጠበቀውን ሳይንሳዊ ዕድገት ማምጣትና የተፈጥሮ ሃብታችንን አግባብ ባለው መንገድ ማልማትና መጠቀም፣

የተፈጥሮ መስህቦችን በመጠበቅና በማልማት ለቱሪዝም መጠቀም፡- ተፈጥሮዊና ማራኪ የሆነውን የመሬት አቀማመጥ በመጠበቅ፣ መሰረተ ልማቶችን በማሳደግ፣ ለአካባቢው ህብረተሰብ አማራጭ የገቢ ምንጭ በመፍጠር በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ እየደረሰ ያለውን ጫና መቀነስ

8.2. የወለቃና አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን


8.2.1. የወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ዝርዝር የተፈጥሮ ሃብት ሁኔታ ትንተና

የስርዓተ ምህዳር ሁኔታ

የተፈጥሮ ደኑ በዋናነት አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (*Acacia-Boswellia-Commiphora* ecosystem) የሚወክል ቢሆንም ቆላማና ሜዳማ የሆኑ የወለቃና አባይ ወንዞችን ተከትለው የሚገኙ የውሃ ዳር ደኖችን (Riverine Vegetation) የሚወክል ስነ ምህዳር የያዘ የተፈጥሮ ደን ማዕከል ነው፡፡

ይሁን እንጅ የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ይህን አካባቢ በ1991 ዓ.ም የኦፕን ውድላንድ ኤንድ ሽራብ ላንድ (open woodland and shrub land) ቅሪት ደን (remnant vegetation) እንደሆነ አስቀምጠው ነበር፡፡ በ1993 ዓ.ም አቶ ጫኔ ገበየሁ ለሁለተኛ ድግሪ ማሞያ በዚህ አካባቢ በ4 ቀበሌዎች ላይ (013. 015 እና 034 ቀበሌዎችን ሳይጨምር) ባደረጉት ጥናት የተፈጥሮ ደኑ የዕፅዋት ሽፋንና ስርጭት (vegetation cover and distribution) የአፈር ዓይነት (soil type)፣ የከፍታ መጠን (elevation)ና የቶፖግራፍ ልዩነትን (topographic gradient) መሰረት አድርጎ እንደሚለያይ ሪፖርት አድረገዋል፡፡ በዚህ መሰረትም የወለቃና አባይ ወንዞችን ተከትሎ የውሃ ዳር ደኖችን (Riverine Vegetation) የሚወክል ስነ ምህዳር የያዘ የተፈጥሮ ደን (ጥቁር

እንጨት፣ዋርካ፣ ገባ፣ እንኮይ፣ ስምንት ልብ)፣ ቀጥሎ ኮረብታዎችን ተከትሎ (hills of river banks) አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (የግራር፣ የእጣን ዛፍ፣ አንቋ፣ ዘንፎቅ ዝርያዎች) የያዘው ደን በዋናነት ይገኛል። ከዚያም በሸለቆው ከፍተኛ ቦታዎች አደርና ሸፈሬ በብዛት የሚገኙበት ሸረብ ላንድስ (shrub lands) ይገኛል።



ምስል 9. በቀበሌ 017 የሚገኘው የደድሃሬ የውሃ ዳር ደን (Riverine Vegetation) እና በቀበሌ 015 የሚገኘው አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ (*Acacia-Boswellia-Commiphora* ecosystem) ስርዓተ ምህዳር

በተለይ የወለቃና አባይ ወንዞች ሜዳማ አካባቢዎችን ተከትለው የሚገኙት እነዚህ ደኖች በውስጣቸው እጅግ በጣም ግዙፍና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎችን አቅፈው የያዙ ናቸው። ይህ ደን ምናልባትም በክልላችን የአባይ ሸለቆ በሚገኝባቸው በየትኛውም አካባቢዎች ጨርሰው የጠፉ ወይም የሌሉ ቅሪት ደኖችን የያዘ የተለየና ማራኪ ስፍራ ነው። አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን የሚወክለው አካባቢ የሚገኘው ከቀበሌ 013 ጀምሮ ወጣገባማና ተራራማ በሆኑት 015፣ 016፣ 017፣ 018፣ 026 እና 034 ቀበሌዎች የአባይና ወለቃ ሸለቆዎች ውስጥ ነው። የውሃ ዳር ደኖችን (Riverine Vegetation) የሚወክለው ስነ ምህዳር ግን የሚገኘው ከሶማ በረሃ ከየሹም እና አባይ ወንዞች መጋጠሚ ጀምሮ በቅደም ተከተል 034፣ 026፣ 018፣ 017፣ 016፣ 015፣ 013 ቀበሌዎችን በማቋረጥ እስከ ከለላ ወረዳ ይዘልቃል። ወንዞችን ተከትለው ከሚገኙ የደን አካባቢዎች መካከልም አጋማይት፣ አቡ ጠንጠቃ፣ ደድሃሬ፣ ጠማሜ፣ መጋጠሚያ፣ ሰንበቶ፣ ዲዳ ዋጮ፣ ቀዋ ዳባ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እነዚህ የደን ቦታዎች በጣም ሜዳማ፣ በዚህ ዓይነት፣ ቁመትና ውፍረት የትም ቦታ የማያገኙ ዛፎችን አቅፈው የሚገኙ ቢሆንም ሜዳማና ለመስኖ እርሻ አመቺ በመሆናቸው የተነሳ ለእርሻ ኢንቨስትመንት እንዲውሉ ለማድረግና ለኢንቨስተሮች ለመስጠት በመታሰቡ ከፍተኛ ችግር ያሉ መሆናቸውን ተረድተናል። በአጠቃላይ ይህ የተፈጥሮ ደን በውስጡ በሀገራችን በማንኛውም ቦታ እንደልብ የማይገኙና ለመጥፋት የተቃረቡ እንደ ጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ኮመር፣ የጣን ዛፍ፣ ዛና፣ ላሎ፣ ዳርሌ፣ አባሎ፣ ዋርካና ባምባ ያሉ ዕፅዋቶችን የያዘ

ስለሆነና አነዚህን ዕዕዋቶች ለመጠበቅ (In-situ Conservation) ተፈጥሮዊ ቦታ በመሆኑ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን እንደሚገባው ያመላክታል፡፡

የዱር እንስሳት

በአጠቃላይ የመካከለኛው የአባይ ወንዝ ተፋሰስ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደኖች ውስጥ ያለው የብዝሃ ህይወት ሃብት ቦታው አመቺ ባለመሆኑ የተነሳ በዝርዝር እንዳልተጠናና እንደማይታወቅ ያሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ የዳሰሳ ጥናት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከ20 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት፣ ከ35 በላይ አዕዋፋት፣ 3 የዓሳ ፣ 4 የተሳቢና ተራማጅ ዝርያዎች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በአሁኑ ሰዓት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚታወቁት ነብር፣ ተራ ቀበሮ፣ አነር፣ የደልጋ አንበሳ፣ መጎዛ፣ ሽልምልም ጅም፣ ተራ ጅብ፣ ጃርት፣ ሚዳቋ፣ ሰሳ፣ ጉሬዛ፣ ተራ ዝንጅሮ፣ ሽክኮ፣ ከርከሮ፣ የዱር ዓሳማ፣ ተራ ጥንቸልና ተራ ድኩላ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የተፈጥሮ ደኑ የሚገኝበትን ቀበሌ 13 ጨምሮ በወረዳው ውስጥ በ26 ቀበሌዎች ብርቅየው ዱር እንስሳ የጭላዳ ዝንጀሮ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም እንደ

- ዝግራ (Vulturine guineafowl)፣
- የሶረኔ ቆቅ (Harwood's Francolin)፣
- ርኩም (Abyssinian ground hornbill)፣
- ዳክዬ (Egyptian goose)፣
- ገደ (Augur buzzard)፣ ወዘተ የመሳሰሉ አዕዋፋት በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) በሀገር አቀፍ ደረጃ በመካከለኛው ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች እንደሚክ ቢርድ ኤርያስ (Central Ethiopian Highlands Endemic Bird Areas) ክልል ውስጥ ከሚገኙ 4 የአዕዋፍት ዝርያዎች ሁሉም በሀገራችን ብቻ እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 2 የአዕዋፍት ዝርያዎች በክልላችን በደቡብ ወሎ ዞን ውስጥ በጀማ እና ጃራ ሸለቆዎች እንዲሁም በመካከለኛው የአባይ ወንዝ ተፋሰስ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደኖች ውስጥ ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል፡፡

በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ በሱዳን ጉይንያ ሳቫና ባዮም (Sudan-Guinea Savanna Biome) ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 16 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 6 የአዕዋፍት ዝርያዎች በጀማ እና ጃራ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደኖች ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም በአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም (Afrotropical Highland Biome) ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 49 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 14 የአዕዋፍት ዝርያዎች በደን ክልሉ ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህ ወንዞች ደግሞ የአባይ ወንዝ ገባሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም በውል ባይጠናም የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) በተመሳሳይ ሁኔታ የመካከለኛው የአባይ ወንዝ ተፋሰስ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደኖች ለሱዳን ጉይንያ ሳቫና ባዮም እና ለአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም ክልል የአዕዋፍት ዝርያዎች ተፈጥሮዊ ቦታ ሊሆኑ እንደሚችሉ አስቀምጠዋል፡፡

በዚህ መሰረትም ከአዕዋፍት ጥበቃ አንፃር ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውና አካባቢው በአይ ቢ ኤ መስፈርት (IBA Criteria) መሰረት ኤ ደረጃ 2 (A2) እንደሚያሟላ ታውቋል፡፡

ስለዚህ እነዘህ በሀገራችን ብቻ የሚገኙ 2 የአዕዋፍት ዝርያዎች፡

- የሶረኔ ቆቅ (Harwood's Francolin)፣

☞ ሩፔልስ ቻት (Rupell's chat)

ከሌሎች አካባቢዎች በተሻለ ሁኔታ ዋነኛ ተፈጥሮዊ መኖሪያቸው በመሆናቸው የተፈጥሮ የደን ክልሉ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም እንዳለው ያመላክታል። ስለሆነም ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በዱር እንስሣት ሀብት ክምችቱ እና IUCN ለጥብቅ ስፍራዎች ማቋቋሚያ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች (criteria for protected areas) በቀጥታ የሚያሟላ በመሆኑ ጥብቅ ስፍራ ሆኖ እንዲከለልና እንዲጠበቅ ያስችለዋል።

የዱር ዕፅዋት ሽፋንና ዓይነት

የወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ በተፈጥሮ የበቀሉ ከቁጥቋጦ ጀምሮ እስከ ትላልቅና ዕድሜ ጠገብ ዛፎች ድረስ ከ62 በላይ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የያዘ የተፈጥሮ ደን ነው። የአባይና ወለቃ ወንዞችን ተከትሎ የሚገኘው ደን በአብዛኛው በረጃጅም፣ ዕደሜ ጠገብና ግዙፍ በሆኑ የዋርካ ዝርያ፣ የጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ገባ፣ ሱማያ፣ ዛና፣ ኮመር፣ የግራር ዝርያ፣ የአርጡማ፣ ዛፎች የተሸፈነ ነው። ወጣ ገባና ተራራማ ቦታዎችን ተከትሎ ግን አንቃ፣ ዋጫና ነጭ ግራር፣ የእጣን ዛፍ፣ አደር፣ አባሎ፣ በትረ ሙሴ ወዘተ የመሳሰሉ ዕፅዋት ይገኛሉ።

ስለዚህ ይህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ በየትኛውም ቦታ እንደልብ የማይገኙና ለመጥፋት የተቃረቡና መጠበቅ የሚገባቸው እንደ ጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ኮመር፣ የጣን ዛፍ፣ ላሎ፣ ዋርካና ባምባ ያሉ ዛፎች ለዘቦታ ጥበቃ /In-situ conservation/ አገልግሎት ሊውል የሚችል ቦታ ስለሆነ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን የሚገባው ስፍራ ነው።

በተለይም በአማራ ክልል በተመሣሣይ ስርዓተ ምህዳር የዚህ ዓይነት የእጽዋትና የደን ስብጥር በዚህ ሁኔታ ማግኘት አስቸጋሪ ነው።

8.2.2. የሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁነቶች፣

የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ እና የኑሮ ሁኔታ፣

የጥናት ቡድኑ በሸፈናቸው የወግዲ ወረዳ 7 ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ብዛት 27,115 እንደሚደርስ ይገመታል። ከዚህ ውስጥ 13,580 ሴቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 13,535 ደግሞ ወንዶች ናቸው።

የሕዝቡ ኑሮ በዋናነት የተመሰረተው በአነስተኛ የግብርና ስራ ላይ ነው። የጥናቱ አካባቢ በወይናደጋና ቆላማ ስነ ምህዳር ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በመሆኑም፣ የአካባቢው ነዋሪ በቤተሰብ ደረጃ በአማካኝ ባለው 1.5 ሄ/ር መሬት ላይ፣ ጤፍ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ሽንብራ፣ ኑግ፣ ተልባና ሌሎች የቅባት እህሎችን በማምረት ይተዳደራል።

በአካባቢው ባለው ሰፊ የእጽዋት ሽፋን እና በርካታ ወንዞች ዙሪያ የሚኖረው የዚህ ህዝብ ግብርና ከእንስሳት እርባታ በሚገኝ ገቢም የሚደገፍ ነው። በአሁኑ ወቅትም ቢያንስ 23 105 TLU የሚሆኑ የቤት እንስሳት ይገኛሉ። በሬ፣

ምንም እንኳ፣ የጥናቱ ቀበሌዎች የመሬት አጠቃቀምና አመታዊ የማር ምርት መጠን ገላጭ መረጃ ማግኘት ባይቻልም፣ የአካባቢው ነዋሪ በዙሪያው ባለ የተሻለ የተፈጥሮ ዕፅዋትና ቁጥቋጦ ሽፋን

ተጠቅሞ የሚያመርተው ማር በጣእሙና ጥራቱ ሰፊ ገበያ ያለው ነው፡፡ ለዚህም በ 7ቱ ቀበሌዎች ከ3735 ባህላዊ፣ 12 የሽግግርና ከ 250 ዘመናዊ ቀፎዎች የማያንሱ የንብ መንጋዎች ይረባሉ፡፡እንደ ወግዲ ወረዳ አካባቢ ጥበቃና መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ባለሙያዎች ገለፃ፣ የወረዳው የተፈጥሮ ዕፅዋትና ቁጥቋጦ ሽፋን በዋናነት የሚገኘው የወለቃና አባይ ወንዞችን ሸለቆ ተከትሎ ነው፡፡ በክልሉ የጥብቅ ቦታ አስተዳደር ስርአት ተጠብቆ እንዲለማ የታጨው ይህ የዱር እንስሳት መጠለያ ደን በቆላማ ስነምህዳር ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ በአካባቢውም፣ ለሰዎች ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች አይገኙም፡፡ ይህ ሁኔታ የአካባቢው ነዋሪ ከታሳቢ ፓርኩ ርቀው በሚገኙ ቦታዎች መንደር መስርቶ እንዲኖር አድርጎታል፡፡

ይሁን እንጂ፣ በተለያዩ ምክንያቶች እና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የታረሱ እርሻዎች በተፈጥሮ ደን ውስጥ አልፈው አልፈው ይገኛሉ፡፡ ከአጎራባች ክልል በመጡ ነዋሪዎች ጭምር ባለፈው የ2002/03 እርሻ ዘመን በታረሱ መሬቶች ላይ የነበረው የተፈጥሮ እጽዋት ተመንጥሮ እንዲጠፋ ተደርጓል፡፡ በርካታ እድሜ ጠገብ ዛፎች እና ቁጥቋጦዎች ተቆርጠው ተጥለዋል .... ተቃጥለዋል፡፡

ከእነዚህ ህገወጥ እርሻዎች ጎን ለጎን፣ ማንነታቸው ባልታወቀ ጣውላ አምራቾች በተፈጥሮ ደኑ ላይ እየደረሰ ያለው ጥፋት የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ትኩረት እና የተቀናጀ የመፍትሄ እርምጃ የሚሻ የአካባቢው ዋነኛ ችግር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ፣ በተፈጥሮ ደኑ እድሜ ጠገብ ግራር፣ ዝግባ፣ ጥቁር እንጨት ዋርካ፣የእጣን ዛፍ ፣ብርብራ ወዘተ ዛፎች ላይ እየደረሰ ያለውን የከፋ ችግር ለመረዳት፣ ከጣውላ አምራቾቹ እለታዊ ፍላጎት ተርፈው በየቦታው ወድቀው የሚታዩት ቁራጭ ዛፎች አይነትና ብዛት በቂ አስረጂዎች ናቸው፡፡

ሌላው የታሳቢ ፓርኩ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ሁነት መገለጫ፣ በአካባቢው ያለው የዳልጋ ከብት እርባታ ነው፡፡ ምንም እንኳን የእንስሳቱን ብዛትና ስርጭት ገላጭ የሆነ መረጃ ለማግኘት ባይቻልም፣ በሸለቆው ውስጥ በተሰሩ እና አካባቢው ነዋሪ ደረባ በሚል ስያሜ በሚጠራቸው ማደሪያዎች ተጠብቀው የሚራቡ በርካታ ከብቶች በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ከብቶች በሌላ ስራ ላይ የተሰማሩ የአካባቢው ተወላጆች በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ እየኖሩ ለሚጠብቁ እረኞች ሰጥተው የሚያራቧቸው ናቸው፡፡ የአንድ ሰው ንብረት የሆኑ (በአንድ ደረባ የሚጠበቁ) ከ100 በላይ ከብቶች በአካባቢው ሊገኝ እንደሚችል በመስክ ስራው ተረጋግጧል፡፡

8.2.3. የታሳቢ ጥብቅ ቦታው የቱሪዝም ሀብት እና ለዘርፉ ልማት ያለው ጠቀሜታ፣

የወለቃ አባይ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በክልሉ የጥብቅ ቦታ አስተዳደር ስርአት ተጠብቆ ቢለማ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቱሪዝም ዘርፍ ለአገሪቷና ለክልሉ ማህበረ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ሚና ማበርከት የሚችል ልዩ ተፈጥሯዊ ሀብት ነው፡፡ ይህን እውነታ ከሚያሳዩ መግለጫና አመልካቾች አንዱ፣ ፓርኩ አለም አቀፍ ትኩረትና እውቅና ለተቸረው የአባይ ወንዝ ስነምህዳር ወካይ መሆኑ ነው፡፡

የአባይ ወንዝ፣ እስከ ሳህል በረሀ ድረስ በሚጋልበው መንገድ ርዝመት ፣ አልፎ በሚሄድባቸው 11 ሀገራት መካከል በተለያዩ ወቅቶች ለሚነሱ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እሰጥ እገባዎች እምብርት በመሆኑ እና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች በሰፊው ይታወቃል። በዚህ ምክንያትም፣ በርካታ ግለሰቦችና አለም አቀፍ ተቋማት ወንዙን በመጎብኘት እና የአካባቢውን ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁነቶችን በማጥናት በመላው አለም እንዲሰራጭ አድርገዋል።

በመሆኑም፣ የአባይ ወንዝ አለም አቀፍ እውቅና፣ ታሳቢ ፓርኩ በቱሪዝም እንደስትሪ ውስጥ ለሚኖረው ቦታ ዋነኛ መሰረት ነው። እስካሁን ካለው እውቅናና ዝና በተጨማሪ፣ ወደፊት ስለወንዙ ገና ብዙ በሚነገሩት እና በሚነሱ እሰጥ እገባዎች ተማርከው የሚመጡ በርካታ አለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ይህን ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ምርጫቸው እንደሚያደርጉት የሚያጠራጥር አይደለም።

ከአለም አቀፍ እውቅናው ጎን ለጎን፣ የወለቃ አባይ ወንዝ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለአገራችን የቱሪዝም ልማት ለሚኖረው ጉልህ ስፍራ የሚያስይዙት በርካታ መስህባዊ እሴቶችን አሰባጥሮ የያዘ ልዩ ቦታ ነው። ለአብነት ከሚጠቀሱት መካከል፣ እጨ ፓርኩ ለውሀ መዝናኛዎች ምቹ መሆኑ የመጀመሪያው ነው።

የአባይና ወለቃ ወንዞችን በማልማት፣ ለዋናና የጀልባ ጉዞ መዝናኛ እንዲውሉ ማድረግ ይቻላል። በተለይ በበጋ ወቅት፣ በወንዞቹ ዳርቻ፣በአሸዋ ደለልና በጠጠር ድንጋዮች የተነጠፉት ሰፋፊ መሬቶች፣ አካባቢው ለውሀ መዝናኛ ያለውን ምቹነት ይበልጥ የሚያሳዩ ናቸው። የፓርኩ ጎብኚዎች፣ በእነዚህ የወንዝ ዳርቻዎች ላይ አረፍ ብለው በዋናና በጀልባ የሚዝናኑትን በመመልከት፣ ጉብኝታዊ ጉዞ በማድረግ፣ አሳ በማጥመድና በሌሎች በርካታ የእረፍት መዝናኛዎች ይበልጥ እንዲረኩ ማድረግ ይቻላል። በክረምት ወራት ወደ ፓርኩ የሚመጡ ጎብኚዎች የሁለቱ ትላልቅ ወንዞች መላት እና መገናኛ ቦታ ላይ ያለውን ሁነት የሚመለከቱበት ማማ ወይም ሌላ ተመራጭ መሰረተ ልማት በማዘጋጀት በርካታ ቱሪስቶችን መሳብ ይቻላል።

በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በአካባቢው የሚገኘው ተራራማ መሬት ያለው ተፈጥሯዊ ውበትና የብዝሀ ህይወት ሀብት የእጨ ፓርኩ ሌላው ዋነኛ የቱሪስት መስህብ ነው። ከባህር ጠለል በ1000 ሜትር ላይ ከሚገኘው የአባይና ወለቃ ወንዞች ዳርቻ እስከ 2500 ሜትር ከፍታ ባለው በዚህ የዱር እንስሳት መጠለያ ውስጥ በርካታ የዱር እንስሳትና እጽዋት ዝርያዎች ተሰባጥረው ይኖራሉ።

በዚህ ሪፖርት ተራ ቁጥር 8.2 ላይ እንደተዘረዘረው፣ በዳሰሳ ጥናቱ የመስክ ቅኝት ብቻ በርካታ የእጽዋት ዝርያዎች በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ በቅለው እንደሚገኙ ተረጋግጧል። ከእድሜ ጠገብ ዋርካ፣ ጥቁር እንጨት ዛፎች በተጨማሪ፣ በደኑ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ዛፎች፣ ሐረጎችና ቁጥቋጦዎች በአካባቢው ያላቸው ስብጥርና ክምችት የአባይና ወለቃ ወንዝ ሸለቆ ማራኪ ውበት ናቸው።

በሌላ በኩልም፣በጥናቱ አካባቢና የጉዞ መስመር ውስጥ ያገራችንን ቀደምት የባህል፣ የስልጣኔና ታሪካዊ ሁኔቶች አሻራ የሆኑ በርካታ መስህባዊ ቅርሶች ይገኛሉ። ከእነዚህ ቅርሶች መካከል፣ ከፍልፍል ዋሻ የተሰሩት የደብረ ከርቤ አባ ያቆብ ገዳም፣አባ ገብረ እንድሪያስ ገዳም፣ አፄ ድንግል ገዳም እና የምስካቤ ቅዱሳን የገዛዝ ገ/መንፈስ ቅዱስ ገዳማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ሰንጠረዥ 3 በወለቃና አባይ ወንዞች ዙሪያ የሚገኙ ባህላዊና ታሪካዊ መስህብ ሀብቶች ዝርዝር፣

ተ.ቁ	ታሪካዊ ቦታው	የታሪኩ ወቅት	መግለጫ
1.	ደብረ ከርቤ አባ ያቆብ ገዳም	4ተኛው ክ/ዘመን	ከ800 አመት በላይ እድሜ ያለው
2	አባ ገብረ እንድርያስ ገዳም፣	በ995	1005 ዓመት በላይ እድሜ ያለው
3	አፄ ድንግል ገዳም	14ተኛው መቶ ክ/ዘመን	
4	ምስካቤ ቅዱሳን የገዛዝ ገ/መንፈስ ቅዱስ፣	12ተኛው መቶ ክ/ዘመን	
5	ወለቃ ዘካርያስ ገዳም		
6	አባ ቅዱስ የስላሴ ጠበል		
7	ወለቃ መቁጠሪ ፀበል፣	14ተኛው ክ/ዘመን	ከ600ዓመት በላይ

ረጅም እድሜ ያስቆጠሩት እነዚህ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች የአካባቢውን የቱሪዝም ፍሰት እና የቆይታ ጊዜ በማሳደግ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ይታመናል።

8.2.4. የወለቃና አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን ላይ እየደረሱ ያሉ ችግሮች

የወለቃና አባይ የተፈጥሮ ደን በወግዲ ወረዳ አማካኝነት ጥበቃ እየተደረገለት ቢሆንም የተፈጥሮ ደኑ በርካታ ችግሮችን እያስተናገደ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት በደኑ ላይ እየዱረሱ ያሉ ዋና ዋና ችግሮችና ስጋቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ህገ ወጥ ደን ጭፍጨፋ፡- በህዝብና የቤት እንስሳት ቁጥር መጨመር፣ በእርሻ መስፋፋትና በጣውላ ንግድ ምክንያት በተፈጥሮ ደኑ ላይ ለረጅም ጊዜ ጭፍጨፋ ሲካሄድበት ቆይቷል። በ7 ቀበሌዎች ውስጥ በጥብቅ ስፍራነት ሊከለል ከሚችለው ከ15000 ሄ/ር በላይ የተፈጥሮ የደን መሬት ውስጥ ከ180 ሄ/ር በላይ በህገ ወጥ መንገድ ደን ተጨፍጭፎ የታረሰ መሬት ሊኖር እንደሚችል ገምተናል። የደን ጭፍጨፋ በዋናነት የሚካሄደው በእርሻ መስፋፋት ምክንያት እንደሆነ በጥናቱ ወቅት በተለይም አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (*Acacia-Boswellia-Commiphora* ecosystem) በሚወክለው የተፈጥሮ ደኑ አካባቢ ተመልክተናል። በቅርብ ጊዜ ደን የነበሩ የወል የደን መሬቶች ታርሰው ለእርሻ አገልግሎት ውለው ተመልክተናል። በጥናታችን ወቅት በደኑ ውስጥ ከ38 በላይ የከብት ማሳደሪያ የደረባ ቤቶችን አግኝተናል። እነዚህ የደረባ ቤቶች የሚዘጋጁት በአካባቢው የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖች ተመንጥረው ነው። በአባይና ወለቃ ወንዞች አካባቢ የሚገኙ ዕድሜ ጠገብ የሆኑ እንደ ዋርካና ጥቁር እንጨት ያሉ ዛፎች ተጨፍጭፈው ዕፅዋቶቹ ለጣውላ ምርት መሬቱ ደግሞ ለእርሻ እንደ ዋለ ማረጋጥ ችለናል።

የህገ ወጥ እርሻ መስፋፋት፡- አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (*Acacia-Boswellia-Commiphora* ecosystem) ተከትሎ በሁሉም ቀበሌዎች በህገ ወጥ መንገድ ከፍተኛ የእርሻ መስፋፋት ይታያል፡፡ በተለይም የአባይ ሸለቆን ተከትሎ ያለው የዕጣን ዛፍ ደን በህገ-ወጥ መንገድ የእርሻ ማሳን ከማስፋፋት ጋር ተያይዞ በአብዛኛው በመጨፍጨፍ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ምክንያት ይህንን ለመከላከል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የህግ አካላት የያዘ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ በየቀበሌው በመዞር በህገ ወጥ መንገድ እርሻ ያረሱ ግለሰቦችንና እርሻዎቻቸውን የመለየትና አስፈላጊውን ቅጣት የማስወሰን እንስቃሴ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ልቅ ግጦሽ፡- ከህገ ወጥ እርሻና ደን ጭፍጨፋ ቀጥሎ የተፈጥሮ ደኑ ዋነኛ ችግር ነው፡፡ በጥናታችን ወቅት እኛ በሜድንበት መስመር ከ38 በላይ የከብት ማደሪያ የደረባ ቤቶችን ተመልክተናል፡፡ እነዚህ የቤት እንስሳት ከአዋሳኝ ቀበሌዎች በተጨማሪ ከሩቅ ቀበሌዎች አካባቢ የሚመጡ ናቸው፡፡ ይህ በመሆኑም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የቤት እንስሳት በደኑ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ይህም በዱር እንስሳት የመመገቢያና መኖሪያ ቦታ ላይ ጫና በመፍጠሩ ምክንያት እንዲሰደዱ፣ አንዲታደኑና እንዲተፉ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ለእርሻ መስፋፋት፣ ለጣውላ ንግድና ለደረባ ቤት ግባታ ደን ጭፍጨፋና ህገ ወጥ አደን እንዲስፋፋ አስተዋፅዖ አድረጓል፡፡ እንዲሁም በዕዕዋት እድገት ላይ አሉታዊ ተዕዕኖ ከማሳደሩም በላይ መጤ ዕዕዋት አካባቢው እንዲስፋፉ አድርጓል፡፡

ህገ ወጥ አደን፡- በከርከሮ፣ ቆቅ፣ ዝግራ፣ ድኩላ ወዘተ በመሳሰሉ የዱር እንስሳት ላይ ህገ ወጥ አደን ይፈፀማል፡፡ በሰብል ውቀት በሰውና በዱር እንስሳት በተለይም በጭላዳ ዝንጀሮና በከርከሮ መካከል ግጭት ስለሚፈጠር ጭላዳን ጨምሮ በከርከሮ ላይ ከፍተኛ አደን እየተፈፀመ ይገኛል፡፡ በ2003 ዓ.ም ብቻ በቀበሌ 015 የሚኖር አንድ ግለሰብ 7 ከርከሮዎችን እንደ ገደለ ከአይን እማኞች ተነግሮናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጭላዳ ዝንጀሮ በወረዳው ውስጥ ከ34 ቀበሌዎች በ26ቱ ይገኛል፡፡ ይሁን ተፈጥሮዊ መኖሪያው በእርሻ መስፋፋትና በልቅ ግጦች የተመናመነ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ሰውና ሰብል ወደ ሚገኝበት ተሰዶ እየኖረ ስለሆነ ከፍተኛ ችግር እየደረሰበት ያለ ብርቅ እንስሳ ነው፡፡

የእርሻ ኢንቨስትመንት፡- በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ ወንዞችን ተከትለው ከሚገኙ የደን አካባቢዎች መካከል አጋማይት፣ አቡ ጠንጠቃ፣ ደድሃሬ፣ ጠማሜ፣ መጋጠሚያ፣ ሰንበቶ፣ ዲዳ ዋጮና ቀዋ ዳባ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ እነዚህ የደን ቦታዎች በጣም ሜዳማ፣ በዚህ ዓይነት፣ ቁመትና ውፍረት የትም ቦታ የማይገኙ ዛፎችን አቅፈው የሚገኙ ቢሆንም ሜዳማና ለመስኖ እርሻ አመቺ በመሆናቸው የተነሳ ለእርሻ ኢንቨስትመንት እንዲውሉ ለማድረግ የተጠኑ መሆኑና ለኢንቨስተሮች ለመስጠት በመታሰቡ ከፍተኛ ችግር ያሉ መሆናቸውን ተረድተናል፡፡

የአካባቢው ህብረተሰብ የግንዛቤ ችግር፡- የህዝብና የቤት እንስሳት ቁጥር መጨመር፣ በተፈጥሮ ደኑ አካባቢ ሰፈራና ህገ ወጥ እርሻ እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡ አማራጭ የሀይል ምንጮችና የማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎች አለመስፋፋት፣ ከሰል ማክሰልና የጣውላ ምርት ችግሩ እንዲባባስ አድርጓል፡፡ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት በመጠበቅና በማልማት ፈንታ በግንዛቤ ችግር ምክንያት በአንድ ወቅት ደን የነበረ ቦታ ወደ እርሻና መንደር እየተቀየረ መጥቷል፡፡ ለአብነት ቀበሌ 017 መጥቀስ ይቻላል፡፡

የጥበቃ ችግር፡- ቀደም ሲል በ1980ዎቹ አካባቢ የደን ክልሉ ይጠበቅ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን በተጠናከረ መልኩ ጥበቃ ስለማይደረግለት ከኦሮምያ ክልል ከደራ ወረዳ፣ ከምስራቅ ጎጃም ዞን ከሸበል በረንታ ወረዳ፣ ከደቡብ ወሎ ዞን ከወግዲ ወረዳ ነዋሪዎችና የቤት እንስሳት ከፍተኛ ጫና እየደረሰበት ይገኛል፡፡

8.2.5. ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች

ከዳሰሳ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክትው የወለቃና አባይ ሸለቆ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ተፈጥሮዊ ደን ሲሆን በተለይ የወለቃና አባይ ወንዞች ሜዳማ አካባቢዎችን ተከትለው የሚገኙት እነዚህ ደኖች በውስጣቸው እጅግ በጣም ግዙፍና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎችን አቅፈው የያዙ ናቸው፡፡ ይህ ደን ምናልባትም በክልላችን የአባይ ሸለቆ በሚገኝባቸው በየትኛውም አካባቢዎች ጨርሰው የጠፉ ወይም የሌሉ ቅሪት ደኖችን የያዘ የተለየና ማራኪ ስፍራ ነው፡፡ አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን የሚወክል ሲሆን ይህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ በየትኛውም ቦታ እንደልብ የማይገኙና ለመጥፋት የተቃረቡና መጠበቅ የሚገባቸው እንደ ጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ኮመር፣ የጣን ዛፍ፣ ላሎ፣ ዋርካና ባምባ ያሉ ዛፎች ለዘቦታ ጥበቃ /In-situ conservation/ አገልግሎት ሊውል የሚችል ቦታ ስለሆነ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን የሚገባው ስፍራ ነው፡፡ በተለይም በአማራ ክልል በተመሣሣይ ስርዓተ ምህዳር የዚህ ዓይነት የእጽዋትና የደን ስብጥር በዚህ ሁኔታ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የተፈጥሮ ደን ተገቢው ጥበቃና እንክብካበቤ ቢደረግለት ለዱር እንስሳት ደህንነት፣ ለሥርዓተ-ምህዳር ጥበቃና ለቱሪዝም ከሚሠው ጥቅም ባሻገር ለትምህርትና ለበርካታ ሣይንሣዊ ምርምሮች በሚኖረው አስተዋጽዖ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን የሚገባው የተፈጥሮ ደን ነው፡፡

1. ጥብቅ ሰፍራ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች

የአለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት /IUCN/ ለጥብቅ ስፍራነት ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ስፍራ እንዲሆን የሚያስችለውን ነጥቦች የሚያሟሉ የተፈጥሮ ዕፅዋትና የዱር እንስሣት ማዕከል እንደሆነ በሚከተለው ሁኔታ ተዘርዝረዋል፡፡

1. **ወካይነት /representativeness/**

- የተፈጥሮ ደኑ በልቅ ግጦሽ፤ በደን ጭፍጨፋና በእርሻ መስፋፋት እየተጎዳ ያለ ቢሆንም አካባቢው አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራና የውሀ ዳርቻ ስርዓተ-ምህዳርን የሚወክል ስለሆነ በጥብቅ ስፍራነት ቢከለል በልማት ቀጠናው ወካይ የሆነ የጥበቃ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡
- ከስርዓተ-ምህዳር ውክልና በተጨማሪ ሶረኔ ቆቅ፣ ሩፔልስ ቻትና የጭላዳ ዝንጀሮን የመሳሰሉ ብርቅየ የዱር እንስሳት እንዲሁም የተለያዩ አዕዋፋትና አጥቢዎችንን ለመጠበቅ ወካይ አካባቢ ነው፡፡ የወለቃ-አባይ ወንዝ የተፈጥሮ ደን በጣም ረጣኝቦምና ከፍተኛ ዉፍረት ያላቸዉ ጥቁር እንጨትና ዋርካ ዛፎች ያሉበት ነዉ፡፡ስለሆነም በዚህ ስርዓተ-ምህዳር ባሉ ሌሎች ደኖች ከ20 ሜትር በላይ ቁመትና ከ8ሜትር በላይ መጠነ ዙሪያ ያላቸዉ ዛፎች ማግኘት አስቸጋሪ ነዉ::

2. **የብዛ-ህይወት ክምችት / Diversity/**

- ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በውስጡ ከ20 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሣት፣ ከ35 በላይ የአዕዋፍት ዝርያዎችና ከ62 በላይ የተለያዩ የእፅዋት ዝርያዎችን ያቀፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የባዝራ ግራር፣ላሎ (የልጅልጅ) ፣ጥቁር እንጨት፣ ዋርካ፣ የጣን ዛፍ፣ደሞ(በደኖ)፣ሰፋ፣...ወዘተ የመሳሰሉት ዛፎች በብዛት ይገኙበታል፣
- የጭላዳ ዝንጅሮ ቁጥር በበቂ ሁኔታና ለጎብኝወች በቀላሉ ለማስጎብኘት በሚያስችል ቁጥርና ስርጭት ይገኛል፣
- አካባቢው በርካታ የብዝሃ-ህይወትንና የደረቅ ወይና ደጋውንና የቆላማውን ስርዓተ-ምህዳር ስለያዘ የድንቅየና ብርቅየ የዱር እንስሳት መናኸሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡
    ለምሳሌ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትን
        - የሶርኔ ቆቅ/*Francolinus harwoodi*/
        - ሩፔልስ ቻት (Rupell's chat) *የያዘ በመሆኑ::*

3. **ልዩ መገለጫ / Distinctiveness/**

- ከፍታን መሰረት ያደረገ የተያያዘ የዕፅዋት ስብጥርን በአብዛኛው የደረቅ ቆለማውንና በተወሰነ መልኩ ደግሞ የወይና ደጋ ስርዓተ-ምህዳርን አካቶ የያዘ በመሆኑ ረግጭጥምና ከፍተኛ ዉፍረት ባላቸዉ ዛፎችም ጭምር የተሸፈነ ነዉ፡፡
- በውስጡ ለጥናትና ምርምር የሚገለግሉ የተለያዩ ዕፅዋትንና ብርቅ የዱር እንስሳትን ይዟል፡፡
- የአባይ ወንዝን ተከትሎ የጀልባ ትራንስፖርት ለማካሄድ ያስችላል፡፡
- የአባይና ወለቃ ወንዞችን ተከትሎ የበጋ ወቅት መዝናኛዎችን ማስፋፋትና አካባቢውን ማህበረሰብ ከእርሻ ውጭ ገቢ እንዲፈጥሩ ያስችላል፡፡
- ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች (የበላይ ዘለቀ የትውልድ ቦታና የተለያዩ ገዳማት ቅርሶች) የበላይ ዘለቀ የትዉልድ ቦታ በቅርብ ርቀት መኖራቸው የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደንን ልዩ ያደርጉታል፡፡

4. ኢኮሎጂያዊ ጠቀሚታ /Ecological importance/

- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል ማለትም ከአካባቢው በተለየ የተሸለ የደን ሽፋን ስላለው ዝናብ ስርጭት የተስተካከለ እንዲሆን አስችሏል፣
- ይህ አካባቢ በክልሉ ውስጥ ለመጥፋት የተቃረቡትን ጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ኮመር፣ የጣን ዛፍ፣ ላሎ፣ ዋርካና ባምባ ያሉ ዛፎች ለመጠበቅ ያስችላል፣
- በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት በተፈጥሮአዊ ገፅታቸዉ ይጠበቃሉ፣
- ብርቅየ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በቦታቸው እንዲጠበቁና እንዳይጠፉ ይረዳል፣
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት እንዲኖር ያስችላል

5. በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ላይ እየደረሱ ያሉ አሉታዊ ተፅዕኖች/Degree of interference/

- ከፍተኛ ተዳፋትነት ያላቸው ቦታዎች ተመንጥረው ለእርሻ ስራ መዋላቸው፣
- የተራ ድኩላ፣ ከርከሮና ጭላዳ ዝንጀሮ አደን መኖር፣
- የልቅ ግጦሽና ደረባ ቤቶች መኖር፣
- ለጣውላና ለግንባታ አገልግሎት የነባር ዛፎች መመንጠር፣
- የተቀናጀ የደን ጥበቃ አለመኖር፣

6. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ /Scientific research and monitoring uses/

- የዕጽዋትንና የዱር እንሰሳትን የተፈጥሮ አካባቢቸዉን ለማጥናት በሞዴልነት ያገለግላል
- የዱር እንስሳት በሽታ ክስተትንና በቤትና በዱር እንስሳት መካከል ያለውን ስርጭት ለማወቅ ያግዛል፡፡
- ለአካባቢ ክትትል በሚኖረው ጠቀሜታ የተፈትሮ ሚዛን ለዉጥን መለካት ያስችላል
- የዱር እፅዋት ናሙናና ተፈጥሮአዊ እድገትንና በሰዎች ጣልቃ ገብነት የሚመጣዉን ለዉጥ ለማየት

7. የቦታ ስፋት/area size/

- ታሳቢ ጥብቅ ቦታው በጥብቅ ስፍራነት ተመዝግቦ በውስጡ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለመያዝ ቢያንስ አንድ ሽህ ሄክታር መጠበቅ ይኖርበታል የሚለውን የ IUCN መስፈርት የሚያሟላና ከ15769ሄ/ር በላይ የሚሸፍን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ሲሆን ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙትን ጭላዳ ዝንጀሮ፣ የሶረኔ ቆቅ እና ሩፔልስ ቻት የዱር እንስሳት መኖሪያ ነው፡፡
- የወለቃ-አባይ ሸለቆ ታሳበቢ ጥብቅ ቦታ የበቶ ወንዝን ተከትሎ እስከ ከላላ ወረዳ ድረስ ከዚህም በላይ ሊሰፋ ይችላል፡፡

8. ቅርፅ /መጠነ ዙሪያ/shape/

- ጥብቅ ስፍራዎች በሚቋቋሙበት ወቅት በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መጠነ ዙሪያ እንዲኖራቸው ይጠበቃል ። የወለቃ-አባይ የተፈጥሮ ደን የአባይና ወለቃ ወንዞችን ተከትሎ በሸለቆዎች ውስጥ የሚገኘውን ወጣገባ፣ ገደላማና ተራራማ ስፍራዎችን የያዘ ሲሆን በቂ የደጀን መሬት ሊኖረው የሚችል ቦታ ነው። ይሁን አንጅ በአንድ ጎኑ ተራራ፣ ኮረብታ፣ ገደልና ተዳፋት የሚበዛበት፣ የዳር ድንበር ወጣገባነት የማይበዛበትና ቅርጹም ሾጣጣ ሆኖ ከስፋቱ አንጻር ሲታይ ረጂም መጠነ ዙሪያ ነው ያለው ቢሆንም ለጥበቃና ቁጥጥር አስቸጋሪ አይደለም።

9. በውስጡ የሚገኙ ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች/Endemicity/

- ከታለላቅ አጥቢዎች ውስጥ የጭላዳ ዝንጀሮ የሚገኝ ሲሆን ከአዕዋፍት ዝርያዎች የሶረኔ ቆቅና ሩፔልስ ቻት የሚገኙበት በመሆኑ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን ይገባዋል።

2. ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ

1. *ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ*

- ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ያላቸዉ ግብግበ ዘለቂታዊ የተፈጥሮ ገጽታ መኖርን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ ያስችላል።
- በደኑ ውስጥና በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል ፣
- ለመጥፋት የተቃረቡትን ጥቁር እንጨት፣የጣን ዛፍ፣ዋርካ፣ ዛና፣ ዳርሌ፣ ላሎ፣ የቆላ ዋንዛና አባሎ ዛፍን ለመጠበቅ ያስችላል፣
- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር ያደርጋል፣
- የአካባቢውን የአየር ሚዛን እንዲጠበቅ ያስችላል፣
- የዱር እንስሳት፣አዕዋፋትና ዕፅዋት በቦታቸው እንዲጠበቁና እንዳይጠፉ ይረዳል።

2. ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ

- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከጐብኝዎች ጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ ገቢዎች ለህብረተሰቡና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል፣
- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጥበቃ ሠራተኝነትና ባለሙያነት እንዲሁም በተፈቀደ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ በመሣተፍ የአካባቢው ህብረተሰብ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ይሆናል፣
- ከምርምርና ሣይንሳዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፣
- የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴ ስለሚስፋፋ ለአካባቢው ህብረተሰብ አንድ የገቢማስገኛ ምንጭ ይሆናል፣
- የአካባቢው የአየር ሚዛን ስለሚጠበቅ ከእርሻ ስራ የሚገኘው ገቢ ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል፣
- በሆቴልና አገልግሎት በመስጠት በርካታ ነዋሪዎች ኑሮአቸዉን ማሻሻል ይችላሉ፣

3. *ማህበራዊ ጠቀሜታ*

- ዓለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህልና ልምድ ልውውጥ ይኖራል፣
- ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው መቋቋም ጋር ተያይዞ የመሠረተ ልማቶች መስፋፋት ት/ቤት፣ የኢኮ ቱሪዝም ማህበራት መደራጀት የሰውና የእንስሳት ጤና ኬላዎች ይገነባሉ፣
- በአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች ደኑን ለመጠበቅም ሆነ በአገባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል።
- የአባይና ወለቃ ወንዞችን በማልማት፣ ለዋናና የጀልባ ጉዞ መዝናኛ እንዲውሉ ማድረግ ይቻላል።

4. የሳይንሳዊ ምርምር ጠቀሜታ

- የዱር እንስሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈጥሮዊ አኗኗራቸዉ ለሚደረግ ምርምር በማእከልነት ያገለግላል፣
- የባህላዊ መድሃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሣይንሳዊ ጥናትንም ለማካሄድ ይረዳል፣
- በመጥፋት ላሉ የዱር እንስሳትና እጽዋት ላይ ሳይንሳዊ ምርምር ሊድረግ ያስችላል፣
- የተፈጥሮ ደኑና ገጽታዉ ለከባቢያዊ ደህንነት፤ ለብዝሃ ህይወትና ለስርአተ ምህዳር መስተካከል ያላቸዉ አስተዋጾ ይታወቃል በዚህ ረገድ ለሚደረጉ ምርምሮች የመስክ ላቦራቶር ሊሆን ይችላል።

5. የተፈጥሮዊነት ጠቀሜታ

- ምንም እንኳን አካባቢው ከሰው ልጆች ተጽዕኖ ነጻ ባይሆንም በአንጻራዊነት ከአካባቢው የተሻለ በመሆኑ ተፈጥሯዊነትን ጠብቆ ለመቆየት ያስችላል። በዉስጡ ያሉትን ብዝሃ ህይወትና ሌሎች (አፈር፤ዉሃና የመሬት አቀማማጥ) በተፈጥሮአዊ ገጽታቸዉ ቆይተዉ ዘለቄታ ባለዉ መልክ ጥቅም እነዲሰጡና ተፈጥሮአዊ ይዘታቸዉ እነዳይጓደል ይረዳል።

6. የቱሪዝም መስህብነት ጠቀሜታ

- አካባቢው በተፈጥሮአዊ ይዘቱ የሰው ልጅን (የጎብኝዎችን) ቀልብ ሊስቡ የሚችሉ ማራኪ ገጽዋች፣ እርካታ የሚሰጡ የወንዝ ዳር ምቹ መዝናኛዎችና መመልከቻ ቦታዎች ያለው ሲሆን ከተፈጥሮአዊ መስህብነቱ በተጨማሪ በአካባቢው ሐይማኖታዊ፣ታሪካዊና ባህላዊ እምቅ የቱሪዝም ፖቴንሻል ያሉበት ነዉ ማለት ይቻላል።

8.2.6. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና

የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለውና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ከተጠበቀ የሚሰጣቸው ጠቀሜታዎች አካባቢያዊ፣ አገራዊና ዓለማቀፋዊ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል። በተለይም ያለው የደን ሽፋንና መልካምድራዊ አቀማመጥ የብዝሃ ህወትና ተፈጥሮዊ ገፅታ ከመጠበቅ አልፎ የዓለም ሙቀትንና የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ የጎላ እስተዋፅዖ ይኖረዋ።

ስለሆነም የተፈጥሮ ደኑ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን የሚሰጠውን ጠቀሜታ (Values) በIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች (Quality Criteria) ጋር በማነፃፀር የቦታውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መፈተሽ ያስፈልጋል። ስለዚህ ከዚህ በታች የተቀመጠው ሰንጠረዥ የወለቃና አባይ ሸለቆዎች የተፈጥሮ ደን የሚሰጠውን ጠቀሜታ ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች ጋር በማነፃፀር ሊጠበቅ የሚገባወን ደረጃ (Protected Area Category) ለመወሰን ያስችላል። ይህም የመመዘኛ መስፈርቶች በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ላይ ያላቸውን ጠቀሜታ ያመላክታል።

ሰንጠረዥ 4: የወለቃ-አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን ጠቀሜታና ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መመዘኛ መስፈርቶች ንፅፅር

አቅም / ጠቀሜታ	ወካይነት	ብዝሃ ህይወት	ልዩ መገለጫ	ኢኮሎጂያዊ ጠቀሜታ	በአካባቢው ላይ ያለ ጫና መጠን	የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	የቦታ ስፋት/	ቅርፅ /መጠነ ዙሪያ/	ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች	ደረጃ ከፍተኛ %
ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100%
የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	89%
ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100%
ማህበራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	78%
ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100%
የመስህብነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100%
ደረጃ ከፍተኛ ቦ%	100%	*100%*	*100%*	*100%*	*100%*	*100%*	*90%*	*43%*	*86%*	***91%***

መፍቻ፡ ከ፡- ከፍትኛ 1-2 ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ

ዝ፡- ዝቅተኛ ከሁለት በላይ ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ

አንድ የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ቦታው ጥብቅ ስፍራ ቢሆን የሚሰጠው ጠቀሜታ (Values) በIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች (Quality Criteria) ጋር ሲነፃፀር ቢያንስ 75 ከመቶ በላይ ውጤት ማሳየት ይኖርበታል፡፡ ከሠንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው ንፅፅሩ ወደ ጎንም ሆነ ወደ ታች 75 ከመቶ በላይ የሚያሳይ በመሆኑ የተፈጥሮ ደኑ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም እንዳለው ያመላክታል፡፡

8.2.6. የወለቃ-አባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ የመሆን ዋና ዓላማ

የተፈጥሮ ደኑ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ባለው የብዝሃ ህይወት ሃብት፣ ከሚሰጠው ጠቀሜታና በIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች (Quality Criteria) አንፃር ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጅ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በIUCN የጥብቅ ስፍራዎች ደረጃ (protected area category) መሰረት የትኛውን ምድብ (Protected area category I-VI) ሊያሟላ እንደሚችል እና የጥብቅ ስፍራውን የመጀመሪያ ደረጃ ዓለማዎች (Primary management objectives) መለየትና መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ለውሳኔ ያመች ዘንድ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በየትኛው ደረጃ ሊመደብ እንደሚችል ያሉ አማራጮች (possibilities) በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት ተመላክቷል፡፡

Table 5 Matrix for protected area categories and Management objectives (IUCN, 1994)

No.	Management categories	IUCN protected area categories							Total (%)
		Ia	Ib	II	III	IV	V	VI	
		Strict natural reserve	Wilderness area	National Park	Natural Monument	Habitat/Species Management Area	Protected Landscape/Seascap	Managed Resource Protected Area	
1	Scientific research	3	2	3	1	2	1	2	22
2	Wilderness	2	3	2	0	0	0	0	11
3	Preservation of species and genetic diversity	2	3	3	2	2	2	2	22
4	Maintenance of environmental services	0	0	3	2	2	2	2	11
5	Protection of species, natural /culture features	2	3	3	3	3	2	2	44
6	Tourism and recreation	0	0	3	2	2	2	2	11
7	Education	2	2	3	1	2	1	2	11
8	Sustainable use of resources from natural ecosystems	0	0	1	0	1	2	3	11
9	Maintenance of natural/cultural/traditional attributes	0	2	3	3	1	3	2	33
	Total (%)	11	33	77	22	11	11	11	

Note: 3= Primary management objective, 2= Secondary management objective, 1=potentially applicable objectives, 0=Not Applicable

አንድ የተፈጥሮ ደን በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (protected area category) እንደሚመደብ ለመወሰን ደኑ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ማሳካት ያለበትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎችን (Primary management objective) በመለየትና በማወቅ መሆን ይኖርበታል። ሠንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው ደኑ በደረጃ ሁለት (protected area category II) መሰረት ጥብቅ ስፍራ ቢሆን በተራ ቁጥር 2 እን 8 ከተቀመጡት የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች በስተቀር ሁሉንም የሚያሳካ ይሆናል። ስለዚህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን

በብሄራዊ ፓርክ ደረጃ ማቋቋም ይቻላል። ይሁን እንጅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በአሁኑ ወቅት ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመፍታት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እና ቦታው ህጋዊ ዕውቅና እስኪያገኝ ድረስ በአግባቡ ማስጠበቅ ይገባቸዋል። ስለዚህ በተፈጥሮ ደኑ ላይ እየተፈፀሙ ያሉ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ እስከተቻለ ድረስ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚከተሉትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች (Primary management objective) የሚያሳካ ይሆናል።

- **ለብዝሃ ህይወትና ስርዓተ ምህዳር ጥበቃ**፡ በአኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ እና ወንዞችን ተከትለው የሚገኙ የውሃ ዳር ደኖች ስርዓተ-ምህዳር ውስጥ በሚገኘው የብዝሃ ህይወት ሃብት የዘቦታ ልማትና ጥበቃ ለማካሄድ የሚያስችል የዕጽዋትና እንሰሳት ስብጥር በማልማትና በመጠበቅ ለተተኪ ትውልደ ማስተላለፍ፣
- **የተፈጥሮ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦችን በመጠበቅና በማልማት ለቱሪዝም መጠቀም፡-** ተፈጥሮአዊና ማረኪ የሆነዉን የመሬት አቀማመጥ፣ ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦችን በመጠበቅና በማልማት ለሰዉ ልጆች አእምሮ ማደሻ በማድረግ የመዝናኛ እድሎችን መፍጠርና ከነተፈጥሮዊ ገፅታዉ በማቆየት በዉስጡ ያሉትን ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሃብቶች በዘለቄታዊ ቱሪዝም ልማት ጥቅም ላይ ማዋል፣
- **ለትምህርትና ሳይንሳዊ ምርምር፡-** ብዝሃ ህይወትን፣ አኬሽያ ቦስዌሊያ ኮሚፎራ ስርዓተ ምህዳርን (*Acacia-Boswellia-Commiphora* ecosystem) እና ወንዞችን ተከትለው የሚገኙ የውሃ ዳር ደኖችን (Riverine Vegetation) የሚወክል ስነ ምህዳር ለትምህርትና ምርምር ማዕከል በማድረግ በዘርፉ የሚጠበቀውን ሳይንሳዊ ዕድገት ማምጣትና የተፈጥሮ ሃብታችንን አግባብ ባለው መንገድ ማልማትና መጠቀም፣

8.3. የጎፍ ታሰቢ ጥብቅ ስፍራ

8.3.1. ስለ ደኑ የጥበቃ ስልትና ታሪክ

የጎፍ ትኩረት ከተሰጣቸው 58 የመንግስት ደኖች ውስጥ አንዱ ነው። የጥበቃ ስራው የተጀመረው በ1965 ዓ.ም ሲሆን በወቅቱ በ63 የደን ዘበኞች ይጠበቅ ነበር። በተጨማሪም ከ1965 እስከ 1976 ዓ.ም የደን ተከላው በሚከናወንበት ጊዜ በመንገድ ስራ፣ የዱር እንስሳት የውሃ መጠጫ ገንዳ በመንከባከብ፣ በእሳት መከላከያ ክትር ስራና በጥበቃ ስራ የሚሳተፉ በዓመት እስከ 300 የሚሆኑ የአካባቢው ሰዎች ከተከላ ስራው ውጭ የስራ ዕድል ያገኙ ነበር። በወቅቱም ለጥበቃ ስራ ተብሎ 5 የጥበቃ ካምፖችና 2 የእንግዳ ማረፊያዎች ተገንብተው ከአንዱ የጥበቃ ካምፕ በስተቀር አገልግሎት ይሰጡ እንደነበር ከጥበቃ ሠራተኞች ያገኘነው መረጃ ያስረዳል። ይሁን እንጅ በአሁኑ ወቅት ከመናፈሻ የእንግዶች ማረፊያ ካምፕ በስተቀር ሁሉም ግንባታዎች ፈራርሰው ቅሪታቸው ብቻ በቦታው ላይ ይታያል። የመናፈሻ የእንግዶች ማረፊያ ካምፕ ቀደም ሲል ለእንግዶች ማረፊያነት የተገነባ ቢሆንም አስሩ ሚሊሻዎች በጥበቃ ካምፕነት ተረክበው እየተጠቀሙበት ይገኛል። ለጥበቃ ስራና ለእንግዶች ማሪፊያነት የተመረጡ ካምፖችና ቦታዎችም፡-

- ☞ አቦምሳ የጥበቃ ካምፕ፡- ኮምቦልቻ ከተማ ቀበሌ 010 ጠጋ ብሎ የሚገኝ፣
- ☞ ማርዬ የጥበቃ ካምፕ፡- ኮምቦልቻ ከተማ ቀበሌ 010 ጠጋ ብሎ የሚገኝ፣
- ☞ መካከለኛ የጥበቃ ካምፕ፡- በደኑ ውስጥ የሚገኝ፣
- ☞ መናፈሻ የጥበቃ ካምፕ፡- በደኑ ውስጥ የሚገኝና ደሴ ዙሪያ ወረዳ ወደ 09 ቀበሌ ጠጋ ብሎ የሚገኝ፣
- ☞ ጣበታ የጥበቃ ካምፕ፡- ኮምቦልቻ ከተማ ቀበሌ 010 ጠጋ ብሎ የሚገኝ፣

- ☞ መናፈሻ የእንግዶች ማረፊያ፡- በደኑ ውስጥ የሚገኝና በአሁኑ ወቅት አስሩ ሚሊሻዎች እየተገለገሉበት ያለ ብቸኛው የጥበቃ ካምፕ፣
- ☞ ቁንዲ የእንግዶች ማረፊያ፡- በደኑ ወስጥ ይጃራ አካባቢ ያለና ደሴ ዙሪያ ወረዳ ወደ 041 ቀበሌ ጠጋ ብሎ የሚገኝ ነው። ይህ አካባቢ የደኑ ከፍተኛ ቦታ (3000 ሜ) ሲሆን እግር ኳስ ሜዳ የሚያህል ደልዳላና በእሳር የተሸፈነ ቦታ አለው። በ1987 ዓ.ም አንድ ጊዜ አንድ ሄሌኮፕተር እንዳስተናገደ ይነገራል።

ከዚህ ሌላ በወቅቱ 5 ኪ.ሜ የእሳት መከላከያ ክትር እና 58.5 ኪ.ሜ የመኪና መንገድ ተሰርቷል። በወቅቱም ሁለቱ የደኑን ከፍተኛ ቦታዎች ጨምሮ በርካታ ቦታዎችን በመኪና በመንቀሳቀስ አሳሳና ቁጥጥር ማካሄድ ይቻል ነበር። ይሁን እንጅ በጥናቱ ወቅት በደኑ ውስጥ ያለው ከፊሉ የመኪና መንግድ በጎርፍ የተበላሸና አግልግሎት የማይሰጥ መሆኑን ስለተመለከትን ጥገና እንደሚያስፈልገው ተረድተናል። በተመሳሳይ መልኩ የእሳት መከላከያ ክትሮችም አልፎ አልፎ በደን የተሸፈኑ ስለሆነ ጽዳት ያስፈልጋቸዋል።

በአሁኑ ጊዜ በጥበቃ ስራ ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ተቆጣጣሪውን ጨምሮ 35 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ አስሩ በልዩ ኃይል የተመደቡ ሚሊሻዎች ናቸው። እነዚህ ሚሊሻዎች በደኑ ላይ ከፍተኛ ጫና በመፈጠሩ ምክንያት ለጥበቃ ስራው ኃላፊነት በተሰጠው የደሴ ዙሪያ ወረዳ ሐምሌ 1996 ጀምሮ ደኑ ውስጥ እየኖሩ እንዲጠብቁ በኮንትራት የተቀጠሩ ናቸው። ጠቅላላ የሰራተኞች ክፍያ ወጭ የሚሸፈነው በክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮና በደሴ ዙሪያ ወረዳ ነው። የኮምቦልቻ ከተማ በቅርብ ርቀት (8 ኪ.ሜ) የሚገኝ መሆኑ፣ የህገ ወጥ ጣውላ ቤቶች መበራከትና በወቅቱ ደኑ ለምርት የደረሰ በመሆኑ ከፍተኛ የደን ጭፍጨፋ ሲካሄድበት ቆይቷል። ሚሊሻዎች የተቀጠሩትም ይህንን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ነበር። ሚሊሻዎች ከተቀጠሩ በኋላ ግን ደኑ ለኮምቦልቻ ከተማ ቅርብ እንደመሆኑ መጠንና በ5 ወረዳዎች እንደመዋሰኑ ሙሉ በሙሉ ደን ጭፍጨፋው ቁሚል ባይባልም በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል።

8.3.2. የጎፍ ታሰቢ ጥብቅ ስፍራ ስፍራ ዝርዝር የተፈጥሮ ሃብት ሁኔታ ትንተና

የሰዓተ ምህዳር ሁኔታ

ጠቅላላ ደኑ ሲመሰረት ከ1965 ጀምሮ እስከ 1976 ዓ.ም ድረስ ባሉ ዓመታት እንደተተከለና ከዚህ ውስጥም 80 ከመቶ የሚሆነው በፕላንቴሽን (በተከላ) የተገኘ ዕፅዋት ያለበት ደን እንደሆነ ከደሴ ዙሪያ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል። ይሁን እንጅ በርካት በደኑ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ወደ ተፈጥሮዊ ይዘታቸው እየተመለሱ ስለሆነ በደኑ ውስጥ በተፈጥሮ የበቀሉት ዕፅዋቶች 20 ከመቶ በላይ የሚሆነውን ሊሸፍኑ እንደሚችሉ በመስክ ጥናታችን ወቅት ለመረዳት ችለናል።

የየጎፍ የመንግስት ጥብቅ ደን ከደሴ ከተማ ቀበሌ 015 የሐረጎ ደን ይነሳና የደሴ ዙሪያ ወረዳ 012፣ 040 እና 41 ቀበሌዎችን በማዋሰን፣ ቀጥሎም የአልብኮ 014 ከዚያም የደሴ ዙሪያ ወረዳ 09 ቀበሌን በመጨረሻም የኮምቦልቻ ከተማ 10 እና 011 ቀበሌዎችን በማዋሰን ከሐረጎ ደን ጋር ዙሮ ይገጥማል። ደኑ ከዳር ወደ ውስጥ ሲገባ ከፍታው እየጨመረ ስለሚሄድ የደኑ ክፍተኛ ቦታ የሚገኘው ከመሃል ነው። ይህ በመሆኑም በዙሪው ላሉት ወንዞችና ምንጮች መገኛ ሲሆን እንደ ተፋሰስ አናት ሆኖ ያገለግላል። የደኑ ጠቅላላ ከፍታም ከ2000 እስከ 3000 ሜ ይደርሳል።

ከዚህ የተነሳ ደኑ የኮምቦልቻን ከተማ ከ8 ኪ.ሜ ርቀት እንዲሁም አጠቃላይ የደኑን ክልል በቀላሉ ለማየት የሚያስችል ማራኪ የስርዓት ምህዳር የያዘ አምባ ነው። የደኑ ምዕራባዊ ክፍል (ደሴ ዙሪያ

041 ቀበሌ ይጃራና የጎፍ ሽንቁር ድንጋይ አካባቢ) በብዛት በፈረጅና የአበሻ ጽድ የተሸፈነ ቢሆንም በሰሜናዊ ክፍሉ በኮምቦልቻ 010 ቀበሌ እና ደሴ ከተማ 015 ቀበሌ፣ እንዲሁም በምስራቃዊ ክፍሉ ደሴ ዙሪያ 09 ቀበሌ አካባቢዎች ያሉ የደኑ ስፍራዎች በተፈጥሮ ዕፅዋቶች በዋናነት ወይራ፣ የአበሻ ጽድ፣ አስታ፣ ዝግባ፣ ኮሶ፣ አምጃ፣ ቀጨሞ፣ አዛምር፣ እምብስ፣ ቀለዋና ጥቁር እንጨት፣ አስኳር፣ ከፈቶ፣ ወዘተ የተሸፈነ ነው።

ስለዚህ የጎፍ በዋናነት የደረቅ ሞንታኔ ስርዓተ ምህዳርን (**Dry Evergreen Montane Forest**) የሚወክል ቢሆንም ከታራራው ጫፍ ጀምሮ ቁልቁል የሚፈሱ አንደ መጠራ፣ ቦሰና፣ ማርዬ፣ ጓሮ ሸለቆዎች አካባቢ ግን የእርጥብ ሞንታኔ ሥርዓተ ምህዳርን (Moist Montane Forest Ecosystem) የሚወክል ደን ነው።

የዱር እንስሳት

ይህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ አጀማመሩ በአብዛኛው በፕላንቴሽን ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ወደ ተፈጥሮዊ ይዘቱ እየተመለሰና በብዝሃ ሕይወት ሃብቱም ባልተለመደ መልኩ በተመሳሳይ ከፍታና ሁኔታ ላይ ከሚገኙ ሌሎች ቦታዎች ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ሁኖ ይገኛል። የየጎፍ ደን በውስጡ ከ29 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሣት እንደተጠለሉበት ይታወቃል። ከእነዚህም ውስጥ በአሁኑ ሰዓት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚታወቁት ነብር፣ ተራ ቀበሮ፣ አነር፣ የደልጋ አንበሳ፣ ጦጣ፣ ጥርኝ፣ መሳዛ፣ ሽልምልም ጅም፣ ተራ ጅብ፣ ጃርት፣ ሚዳቋ፣ ሰሳ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ፣ ተራ ዝንጅሮ ፣ ሽክኮ፣ ከርከሮ፣ የዱር ዓሳማ፣ ተራ ጥንቸል፣ አወልድ ጌሳ፣ ተራና የሚኒሊክ ድኩላ ጥቂቶቹ ናቸው።

ከየጎፍ ተራራ ጭፍ ጀምሮ ገደላ ገደሉን፣ ትንንሽ ሸለቆዎችና ጅረቶችንና ጓሳ ያለበትን ተከትሎ አስከ ሐረጎ ደን ድረስ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙት የጭላዳ ዝንጀሮና የሚኒልክ ድኩላ በብዛት በደኑ ውስጥ ይኖራሉ።

በተጨማሪም ቀደም ሲል በበርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል በ1988 ዓ.ም በደኑ ውስጥ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ከ62 በላይ አእዋፋት በቦታው እንደሚገኙ ተረጋግጧል። በዚህ የዳሰሳ ጥናትም በቀጥታና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ከ75 በላይ አእዋፋት በአካባቢው ሊኖሩ እንደሚችሉ አረጋግጠናል። ከእነዚህም ውስጥ 4 ያህሉ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ናቸው።

- ግንደ ቀርቁር /Abyssinian Woodpecker/
- የአበሻ ድመት መሳይ ወፍ/Abyssinian catbird/
- የሶረኔ ቆቅ /Harwood's Francolin/
- አቢስንያን ሎንግ ክሎው /Abyssinian long claw/

ከእነዚህ ሌላ ከኤርትራ ጋር ብቻ የምንጋራቸው እንደ

- ጋጋኖ (Wattled ibis)፣
- ቁሱ (Thick billed raven)፣
- ብላክ ዊንግድ ላቭ በርድ (Black winged lovebird or Abyssinian lovebird)፣
- ኋይት ባክድ ብላክ ቲት (White backed Black Tit)፣

አእዋፍት መጠልያም ነው። እንዲሁም በብዙ ቦታ የማይገኘው ቅልጥም ሰባሪም (Lammergeyer) በዚህ ቦታ ይገኛል።

ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) በዓለም አቀፍ ደረጃ በአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም (Afrotropical Highland Biome) ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ 49 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ 18

የአዕዋፍት ዝርያዎች በደን ክልሉ ተጠልለው እንደሚኖሩ አስቀምጠዋል። በዚህ መሰረትም ከአዕዋፍት ጥበቃ አንፃር ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በአይ ቢ ኤ መስፈርት (IBA Criteria) መሰረት ኤ ደረጃ 3 (Category A3) እንደሚያሟላ ታውቋል።

ስለዚህ እነዘህ 18 የአዕዋፍት ዝርያዎች ከአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም (Afrotropical Highland Biome) ውጭ በሌላ ባዮም (Biome) የማይገኙ በመሆኑ የደን ክልሉ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም እንዳለው ያመላክታል።

ስለሆነም የየጎፍ ደን ባለው የዱር እንስሣት ሀብት ክምችቱና በኢትዩጵያ ብቻ የሚገኙ አጥቢዎችና አእዋፋት መጠለያነቱ ምክንያት በበርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል እንደ አእዋፍ መጠለያ (Important Bird Area category A3) ተደርጎ ሲወሰድ በመንግስት ደግሞ አጠቃላይ ባለው የብዝሃ ሕይወት ሃብት የተነሳ ትኩረት ከተሰጣቸው 9 የመንግስት ደኖች (National Forest Priority Area) ውስጥ አንዱ ተደርጎ ተይዟል። ስለሆነም የጎፍ IUCN ለጥብቅ ስፍራዎች ማቋቋሚያ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች (criteria for protected areas) በቀጥታ የሚያሟላ በመሆኑ ጥብቅ ስፍራ እንዲሆን ያስችለዋል።

የዱር ዕፅዋት ሽፋንና ዓይነት

የየጎፍ ደን ከቁጥቋጦ ጀምሮ እስከ ትላልቅ የጣውላ ዛፎች ድረስ ከ85 በላይ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የያዘ ነው። ደኑ ልክ እንደ ወፍ ዋሻ ታሳቢ ጥበቅ ስፍራ በአብዛኛው በአረጁና ግዙፍ በሆኑ የፈረንጅና በአበሻ ጽድ፣ ባህር ዛፍ፣ በዝግባና በወይራ ዛፎች የተሸፈነ ቢሆንም ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው የፈረንጅና አበሻ ጽድ ነው።

የየጎፍ ደንን ከውስም ሆነ ከውጭ ከተለየያ አቅጣጫ ሲመለከቱት ከወፍ ዋሻ ታሳቢ ጥበቅ ስፍራ በተሻለ ጥቅጥቅ ያለ ሲሆን ለጣውላ ምርት ሊውል የሚችል በርካታ የፈረንጅና የአበሻ ጽድ እንዲሁም ለግንባታ የደረሰ ባህር ዛፍ ያለው በመሆኑ ጊዜው አልፎበት (Over aged) እና በተለያዩ ምክንያቶች እየደረቀ፣ እየወደቀና እየበሰበሰ መሆኑን ተመልክተናል። በተጨማሪም በተፈጥሮ ጥቅጥቅ ብለው እየበቀሉ ያሉ ብዙ የአበሻ ጽድ ችግኞችን በደኑ ውስጥ ብዙ ቦታዎች ላይ ተመልክተናል። ይሁን እንጅ የማሳሳት ስራ ባለመሰራቱና በቂ የዕሐይ ብርሃን ባለማግኘታቸው ምክንያት እድገታቸው ውጤታማ እንዳከልሆነ ተመልክተናል። ይህም ደኑ ውስጥ የሚገኙትን መጤ ዕፅዋቶች እንደ ፈረንጆ ጽድ፣ ባህር ዛፍ፣ ፓይነስ፣ ፓቹላ፣ ወዘተ በሀገር በቀልና በተፈጥሮ የሚበቅሉ ዕፅዋቶች ለመቀየር ያስችላል። በተጨማሪም ደኑ በተፈጥሮው ሊይዝ የሚገባውን የደን ስብጥር ለመጠበቅ የሚያስችል ሲሆን ችግኞችን መትከል ላያስፈልግ ይችላል።

በደኑ ውስጥ የሚገኙ ዕፅዋቶችን በተመለከተ የአበሻና የፈረንጅ ጽድ፣ ኮሶ፣ አምጃ፤ ቀጨሞ፣ ዝግባ፣ አስታ፣ ወይራ፣ እምብስ፣ ብሳና፣ ዋነዛ፣ አጣጥ፣ የተፈጥሮ ስብጥሩን በመጠበቅ የሚበቅሉ በርካታ የቁጥቋጦ ዝርያዎች ዋና ዋና ዕፅዋቶች ናቸው። በተለይ በአገራችን ቁጥራቸው እየተመናመኑና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸዉ የአበሻ ጽድ፤ ዝግባ፣ ኮሶ፣ ወይራና ጥቁር እንጨት ሊጠበቁበት የሚችል ዋነኛ ተፈጥሮአዊ የሆነ ቦታቸዉና በሚፈለገው ቁመትና መጠን ሊጠበቁበት የሚችል የቅርስ አምባ ነዉ።

የደኑ ሽፋንም የስርዓተ ምህዳሩን የዕጽዋት ስብጥር በመያዝ በደረቅ ሞንታኒ ደን የላይኛው ክፍል /አስታ፤አምጃ ኮሶና የአበሻና ፈረንጅ ጽድ/ በደረቅና እርጥብ ሞንታኔ ደን በታችኛውና በማዕከላዊ ክፍል /ዝግባና ወይራ በመሆን የደን ሽፋን ስብጥሩ ተይዞ ይገኛል። ሆኖም ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉት የአበሻና የፈረንጅ ጽድ እና ባህር ዛፍ ለምርት የደረሱ፣ በጣም ያረጁና እድሜ ጠገብ

ሲሆኑ እየደረቁ፣ እየወደቁና እየበሰበሱ እንዲሁም በአካባቢው ሰዎች በስርቆት ጉዳት እየደረሰባቸው ይገኛሉ፡፡

የጎፍ በእጽዋት ስብጥርና ቁመት የወፍ ዋሻ ታሳቢ ጥበቅ ስፍራ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በአገሪቱ ዋነኛ የደን ሽፋን መገለጫ ነው የሚባለውን የሃረና ደን እንዲሁም እረጃጅምና ግዙፍ ዛፎች የሚገኙበትን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሊወክል የሚችል ቦታ ነው፡፡ በተለይም በአማራ ክልል በተመሣሣይ ስርዓተ ምህዳር የዚህ ዓይነት የእጽዋትና የደን ስብጥር በዚህ ሁኔታ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡

8.3.3. የየጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ

የየጎፍ ጥብቅ ቦታ

የሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታ

ጥብቅ የመንግስት ደኑ ድንበር በሚያካልላቸው ቀበሌዎች ውስጥ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ 9658 ቤተሰቦች (2089 በእማወራና 7548 በአባወራ የሚመሩ) ይገኛል፡፡ በእነዚህ ቤተሰቦች በድምሩ 41362 የሚሆኑ ነዋሪዎች (22643 ወንድና 17719 ሴት) ያስተዳድራሉ፡፡

የደኑ ዙሪያ መሬት አቀማመጥ፣ ተዳፋትና ገደላማ መሬቶች የሚበዛበት ነው፡፡ በመሆኑም፣ በጥናቱ አካባቢ ከሚገኘው ህብረተሰብ አብዛኛው በዋናነት ለሚያመርተው የማሽላ፣ በቆሎ. ና ስንዴ አዝመራ የሚጠቀምበት መሬት ለእርሻ ስራ አመቺ አይደለም፡፡ ከወረዳ ጽ/ቤቶች በተገኘው መረጃ መሰረት በጥናቱ 7 ቀበሌዎች እየታረሰ የሚገኘው መሬት አጠቃላይ ስፋት 7586 ሄክታር ነው፡፡ ይህም በቤተሰብ ደረጃ በአካባቢው ያለው አማካኝ የእርሻ መሬት ይዞታ 0.79 ሄ/ር ብቻ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

በዚህ አነስተኛ የእርሻ መሬት ላይ የሚከወነው የሰብል አዝመራ ስራ፣ ከ12 አይነት የቤት እንስሳት እርባታ (ንብን ጨምሮ) በሚገኝ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚደገፍ ነው፡፡ በጥናቱ ቀበሌዎች በልቅ ግጦሽ የሚራባው ቤት እንስሳት ብዛት በትቤእመ [TLU] 23389 ይደርሳል፡፡ የቀንድ ከብት የአካባቢው ዋነኛ የቤት እንስሳት ናቸው፡፡ ከቤት እንስሳቱ እርባታ ጋር በ135 ዘመናዊ፣ 49 የሽግግርና 87 ባህላዊ ቀፎዎች በሚገኙ የንብ መንጋዎች የማር ምርት ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ የቤት እንስሳቱ በአካባቢው ለወል ግጦሽና በግብርና ስራ አጠቃላይ መሬት ላይ በሄክታር ያለው አማካኝ የትቤእመ 13.87 እና 2.52 የሚደርስ ነው፡፡ ይህ ከፍተኛ የሆነ የቤት እንስሳት ግጦሽ መጠን፣ እጅግ ተዳፋታማና ለእርሻ ስራ አመቺ እስካልሆኑ ተራራማ ቦታዎች ድረስ ከተስፋፋው እርሻ ጋር ተዳምሮ በአንድ በኩል በአካባቢው የዱር እንስሳት መጠለያ ላይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በነዋሪው የግብርና ስራ ላይ የፈጠረው ችግር በቀላሉ ጎልቶ የሚታይ ነው፡፡

በዚህ ረገድ፣ በተለይ በመስክ ስራው ወቅት ከተደረገው መደበኛ ያልሆነ ውይይትና ከቅኝታዊ ጉዞው ምልከታ ለመገንዘብ የሚቻለው፣ በአካባቢው የግብርና ኑሮ ላይ፡

- ☞ *በየጊዜው የእርሻ መሬት ለምነትና ምርታማነት መቀነስ*
- ☞ *በእርሻ መሬት ላይ እየተስፋፋ የሚገኘው ቦረቦር፣*
- ☞ *የዱር እንስሳት የሰብል ምርቱን በመመገብ የሚያደርሰብት ጥፋት እና ሰብሉን ለደር እንስሳት ለመጠበቅ የሚጠፋዉ ጊዜና ጉልበት ትልቅ ጫና እየፈጠሩ ያሉ ችግሮች መሆናቸው ነው።*

ስለዚህ፣ ታሳቢ ጥብቅ ቦታውን በክልሉ የጥብቅ ቦታ አስተዳደር ስርአት ማስተዳደር፣ ለዱር እንስሳቱ መጠለያ ልማት ካለው ፋይዳ በተጨማሪ ለአካባቢው ነዋሪ ደህንነት አስፈላጊ የሆነው የደኑን ስነ ምህዳራዊ አገልግሎት በዘለቄታዊነት ለመጠበቅ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡

ለእጩ ጥብቅ ቦታዉ በታጩ አካባቢዎች ዙሪያ ካለው ሁኔት ጎን ለጎን፣ በጥብቅ ደኑ ውስጥ የሚኖረው ህብረተሰብ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሌላው ትኩረት የሚሻ አብይ ጉዳይ ነው።

8.3.4. የታሳቢ ጥብቅ ቦታው የቱሪዝም ሀብት እና ለዘርፉ ልማት ያለው ጠቀሜታ፣

የየጎፍ ታሳቢ ጥብቅ ቦታ ለክልሉ የቱሪዝም እድገት የበኩል ሚና ማበርከት የሚያስችል አቅም ያለው የተፈጥሮ ሀብት ነው። ታሳቢ ጥብቅ ቦታውን በክልሉ የጥብቅ ቦታ አስተዳደር ስርአት ጠብቆ በማልማት ወደፊት በቱሪዝም ዘርፍ ለሚኖረው ድርሻ መነሻ የሚሆኑ ሁለት ዋና መሰረቶች አሉ።

የመጀመሪያው ታሳቢ ጥብቅ ቦታው አሰባስቦ የያዘው የብዝሀ ህይወት ሀብት ነው ።. እስካሁን በተደረጉ ጥናቶች ብቻ በእጩ ጥብቅ ቦታው የሚገኙ 86 የእጽዋት ሀብት 28 አጥቢ እንስሳት 82 አእዋፋት ተመዝግበው ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ 3 እጽዋት 2 የአጥቢና 4 የአእዋፍ ዝርያዎች በተወሰኑ የአገራችን ክፍሎች ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ ሀብቶች ናቸው። እነዚህ ልዩ ተፈጥሯዊ እሴቶች፣ የመንግስት ደኑ በክልሉ የጥብቅ ቦታ አስተዳደር ስርአት ጠብቆ በማልማት በቱሪዝም ዘርፍ ወደፊት ለሚኖረው አስተዋጽኦ ዋነኛ መነሻ ናቸው።

ታሳቢ ጥብቅ ቦታው የአገራችን ዋነኛ የቱሪስት መተላለፊያ መስመር ከሆኑት የደሴና ኮምቦልቻ ከተሞች አቅራቢያ መገኘት ወደፊት በአገር ውስጥና አለም አቀፍ ጎብኚዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ለሚኖረው ድርሻ ትልቅ ግብአት የሚሆን መልካም አጋጣሚ ነው። በተለይ ታሳቢ ጥብቅ ቦታውን አልምቶ ለደሴ፣ ኮምቦልቻና ለሌሎች የአጎራባች ከተማ ነዋሪዎች የመዝናኛና እረፍት አገልግሎት ክፍት ማድረግ ለአካባቢው ማህበረ-ኢኮኖሚ እና ለአገር ውስጥ ቱሪዝም እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ ይቻላል።

ከዚህ ጎን ለጎን፣ የእጩ ጥብቅ ቦታውን ተፈጥሯዊ ሀብቶች አልምቶ የደሴና አጎራባች አካባቢ መስህቦችን ለመጎብኘት ለሚመጣው እና፣ ለላሊበላና የአክሱም ከተሞች ቅርስ ጉብኝት በጉዞ መስመሩ ለሚያልፉ አለም አቀፍ ጎብኚዎች በማስተዋወቅ ለዘርፉ የሚኖረውን ፋይዳ ማጎልበት ይቻላል።

8.3.5. የየጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን ላይ እየደረሱ ያሉ ችግሮች

የጥበቃ ስራው የተጀመረው ደኑ ሲቋቋም ከ1965 ዓ.ም ጀምሮ ቢሆንም ደኑ በርካታ ችግሮችን ሲያስተናግድ ቆይቷል። በደኑ ላይ እየዱረሱ ካሉ ዋና ዋና ችግሮችና ስጋቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ህገ ወጥ ደን ጭፍጨፋ፡- የየጎፍ ደን በአሁኑ ጊዜ ከ35 ዓመት በላይ የሆናቸው ለምርት ደረሱ የአበሻና የፈረንጅ ዕድ እንዲሁም ባህር ዛፍ የደን ውጤቶች ባለቤት ነው። ይህም በመሆኑም ለጣውላ ምርት በአካባቢው ሰዎች ከፍተኛ ጭፍጨፋ ሲካሄድበት ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት በ32 የጥበቃ ሠራተኞች የሚጠበቅ ቢሆንም ካለው የቦታ ስፋትና መጠነ ዙሪያ አንፃር በቂ ባለመሆናቸው ችግሩ አሁንም ድረስ እየተስተዋለ ይገኛል። በመሰክ ጥናት ወቅት 12 ግንዲላ በ3 ግመል ተጭኖ ወደ ኮምቦልቻ ከተማ ሊገባ የነበረ የፈረንጅ ጽድ ዛፍ አግኝተን ለሚመለከተው አካል አስረክበናል። በተለይ በቅርብ ርቀት ላይ የኮምቦልቻ ከተማ መኖሩ (8 ኪ.ሜ)ና በአካባቢው የህገ ወጥ ጣውላ ቤቶች መበራከት ደኑ በከፍተኛ ሁኔታ የችግሩ ሰለባ እየሆነ ይገኛል። በኮምቦልቻ ከተማ አንዱ ግንዲላ እስከ 190 ብር ይሸጣል።

መንደር ግንባታና የእርሻ መስፋፋት፡- በጥሩ ሁኔታ የሚገኘውን የሐረጎ ደን ከቀረው የየጎፍ ደን ጋር አያይዞ ጥብቅ ስፍራ ለማድረግ ደሴ ዙሪያ ወረዳ ቀበሌ 012 ጭቃ በረት ጎጥ ልዩ መጠሪያው ጎልቦ አካባቢ በእርሻ ተቋርጧል። እርሻው ወደ 40 ሄ/ር ስፋት ሊኖረው እንደሚችል ገምተናል። ይህ ቦታ ቢያንስ ከ45 ድግሪ በላይ ተዳፋትነት (Slope) ያለው ሲሆን ያለ እርከን መጠቀም

አይችሉም። ይሁን እንጅ ከግርጌው የኮምቦልቻ 011 ቀበሌ የሆኑ መንደሮች ይገኛሉ። በተጨማሪም ከመንደሮች ከፍ ብሎና ከእርሻው ግርጌ ጀምሮ መሬቱ እየተንሻራተተ ትልቅ ገደል (Gully) መስራት ስለጀመረ በቀላሉ ማየት ይቻላል። ስለሆነም መሬቱ በችግኝ ተከላ እንዲተርፍ ካልተደረገ በቀር በአጭር ጊዜ ውስጥ ማጋጋምም ሆነ ለረጅም ጊዜ ለእርሻ ሊያገለግል አይችልም።

በሆኑም ሁለቱን ደኖች ለማገናኘትና ጥብቅ ስፍራ ለማድረግ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት እየተጎዳ ያለውን መሬት ለመታደግ ይህን አካባቢ ለእርሻ እንዳይውል ማድረግ፣ ለአርሶ አደሮች ትክ መሬት መስጠት፣ አካባቢው ላይ ችግኝ ተካላ ማካሄድና ቦታውን ለዱር እንስሳት መተላላፊያነት (wildlife corridor) ክፍት ማድረግ በትልቁ ሊታሰብባቸው የሚገባ ጉዳዮች ናቸው። ምክንያቱም በመስክ ጥናት ወቅት ከየጎፍ ደን አቅጣጫ መጥተው የነበሩ የጭላዳ ዝንጀሮ መንጋዎች እርሻው አካባቢ ከደረሱ በኋላ ማቋረጥና ወደ ሐረጎ ደን ማለፍ ስላልቻሉ ሲመለሱና ወደ መጡበት አቅጣጫ ሲሄዱ በመመልከታችን ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በደሴ ዙሪያ ወረዳ 040 ቀበሌ ወፍ ከሌ መንደር አካባቢ ከ041 እና 012 ቀበሌዎች የሚያያዘውን ተዳፋት ተከትሎና ከመንደሩ ራሰጌ ጀምሮ በእርሻ መሬት (ወደ 4 ሄ/ር የሚገመት) የተቋረጠ ቦታ አለ። ይህም የዱር እንስሳት መተላለፊያ ቦታ ስለሆነ መከፈት ይኖርበታል።

ሌላው በቃሉ ወረዳ የ031 ቀበሌ ከደሴ ወረዳ 09 እና 041 ቀበሌዎችና ከአልብኮ ወረዳ 014 ጋር የሚያያዝ ሰፊ ደን ያለው ቢሆንም መሃል ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው መንደርና አርሻ ያለው በመሆኑ በጥብቅ ስፍራነት ሊካተት እንደማይችል አረጋግጠናል። ከዚያ ይልቅ 09፣ 041 እና 014 ቀበሌዎች አካባቢ ያሉ ደኖችን በቀጥታ ከሀረጉ ደንና ከዋናው የየጎፍ ደን ጋር በማገናኘት ጥብቅ ስፍራውን ማቋቋምና ከቃሉ ወረዳ ቀበሌ 031ን መቁረጥና ከክለላው ውጭ ማድረግ አማራጭ የሌለው ሃሳብ እንደሆነ ተረድተናል።

ከዚህ በተጨማሪ ሌላው በጣም አስቸጋሪ ሁኖ ያገኘነው በደሴ ዙሪያ ወረዳ በደኑ ውስጥ የሚገኙ የ09 እና 041 ቀበሌዎች አካል የሆኑ 8 ትናንሽ መንደሮችና የእርሻ መሬቶች ናቸው።

- ሐቤ ቁርቁር መንደር (041 ቀበሌ፣ 6 ቤቶች፣ወ 15፣ ሴ 17፣ ደ 32 ቤተሰብ ይኖራሉ)
- ሶስትያ መንደር (041 ቀበሌ፣ 16 ቤቶች፣ ወ 30፣ ሴ 33፣ ደ 63 ቤተሰብ ይኖራሉ)
- ቀጣኒት መንደር (041 ቀበሌ፣ 19 ቤቶች)
- የራበሽ መንደር (041 ቀበሌ፣ 18 ቤቶች)
- ጉባ መንደር (041 ቀበሌ፣ 11 ቤቶች)
- ሽንቁር ድንጋይ መንደር (09 ቀበሌ፣ 14 ቤቶች)
- ጀሩ አገር መንደር(09 ቀበሌ፣ 20 ቤቶች)
- ቦሰና መንደር (09 ቀበሌ፣ 17 ቤቶች)

የሃቤ ቁርቁርና ሶስትያ መንደሮችን አማካኝ የቤተሰብ ቁጥር በመውሰድ (በቤተሰብ በአማካኝ 4 ሰዎች) ቀጣኒት 76፣ የራበሽ 72፣ ጉባ 44፣ ሽንቁር ድንጋይ 56፣ ጀሩ አገር 80 እና ቦሰና 68 በአጠቃላይ ከ491 የማያንሱ ሰዎች በእነዚህ መንደሮች ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ ብለን ገምተናል። ከእነዚህ መንደሮች ውስጥ በቃሉ ወረዳ ከ031 ቀበሌ ጋር የተያያዙትን በተለይም በቀበሌ 09 ውስጥ ያሉ መንደሮችን በሙሉ እንዲሁም በቀበሌ 041 የራበሽና ጉባ መንደሮችን ከደን ክልሉ ውጭ ማድረግ ይቻል ይሆናል ለሌሎቹ መንደሮች ግን አማራጭ መፍትሄ መፈለግ ይኖርበታል። ለመንደሮቹ ሲባል በርካታ የደኑ ክፍል ከደን ክልሉ ውጭ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ሌላ በደኑ ውስጥ የእነዚህ መንደሮች የእርሻ መሬት በመኖሩ የዱር እንስሳቱን እንቅስቃሴ ከመግታቱም ባሻገር የተፈጠሮ ሃብቱን በማራቆት ለአፈር ክለት እያጋለጠው ይገኛል። በተለይ በአዝመራ ወቅት በህብረተሰቡና በጭላዳ ዝንጀሮ መካከል ገጭቶች ይስተዋላሉ።

የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ደጀን የሌለው መሆን፡-

የየጎፍ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ አብዛኛው ቦታ በመንደርና በእርሻ የተከበበ ስለሆነ ጥብቅ ስፍራው ላይ የሚኖረውን ጫና ለመቀነስ የሚያስችል ደጀን መከለል አስፈላጊ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህን ጫና ለመቀነስ የሚያስችል ሊከለል የሚችል የወል መሬት ስለሌለው ለጥበቃው አስቸጋሪ ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ በየጊዜው የእርሻ መስፋፋት ስለሚታይ የደን መሬቱ እየተጣበበ ይገኛል፡፡

የደን አጠቃቀም ችግሮች

ደኑ በአሁኑ ወቅት ለጥቅም የደረሱ ዛፎች ያሉት በመሆኑ መሬቱንና በውስጡ ያሉትን የዱር እንስሳት ተፈጥሮዊ ደህንነት በማይጎዳ መንገድ ደኑን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የማኔጅመንት ፕላንና ዝርዝር የአጠቃቀም ስልት ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ለጥቅም የደረሱ ዛፎች ቢወገዱ (ጥቅም ላይ ቢውሉ) በአጠቃላይ በአካባቢው ሚዛናዊ ስርዓተ ምህዳር (Ecosystem Balance) ላይ የሚያመጡት የአካባቢ ተፅዕኖ (Environmental Impact) መጠናት ይኖርበታል፡፡ ይህ ባለመሆኑም ምክንያት በርካታ ሰዉ ሰራሽ ደኖች አርጅተዉና ጥቅም ከሚሰጡበት ደረጃ አልፈዉ ወድቀውና በስብሰው ይታያሉ፡፡ በተጨማሪም ለጥቅም የደረሱ ደኖች የማንጅመንት ፕላን ተሰርቶላችው ጥቅም ላይ አለመዋላቸውና የአካባቢውን ህብረተሰብ ተጠቃሚ አለማድረጋቸው ህብረተሰቡ በደኑ ላይ የነበረው የባለቤትነት ስሜት እንዲቀንስና ህገ ወጥ የደን ጭፍጨፋ እንዲባባስ አድርጓል፡፡

የበጀት እጥረትና የጥበቃ ችግሮች

ደኑ የደሴ ዙሪያ ወረዳን ጨምሮ 5 (ቃሉ፣ ኮቦልቻ ከተማ፣ ደሴ ከተማ፣ አልብኮና ደሴ ዙሪያ) ወረዳዎች የሚያዋስኑት ቢሆንም ለጥበቃ ስራው ኃላፊነት የተሰጠው የደሴ ዙሪያ ወረዳ ብቻ ነው፡፡ የሰራተኞች ክፍያ ወጭ የሚሸፈነውም በክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮና በደሴ ዙሪያ ወረዳ ብቻ ነው፡፡ በአንጻሩ ሌሎቹ ወረዳዎች ለጥበቃ ስራው ትኩረት እንዳይሰጡ አድርጓል፡፡ በተለይ የኮምቦልቻ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ መገኘትና ደኑ ለጣውላ ስራ በስፋት የሚፈለግ መሆኑ የጥበቃ ስራውን ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ከዚህ አልፎ ተርፎ የጥበቃ ሰራተኞች ቁጥር ከቦታው ስፋትና ከችግሩ ውስብስብነት አንጻር በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ይህም የጥበቃ ስራው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲያደርግ አስችሎታል፡፡ በጥበቃው ስራ ላይ ሁሉም ወረዳዎች እኩል ኃላፊነት ቢሰጣቸው ኑሮ የጥበቃ ሰራተኞች ቁጥር አሁን ካለው የተሻለ ሰለሚሆን የጥበቃ ስራውም የተሻለ ይሆን ነበር፡፡

ለጥበቃ ሰራተኞች የሚከፈለዉ ደመወዝ አነስተኛና አንድ ዓይነት አለመሆኑ በሠራተኞች መካከል ልዩነት ፈጥሯል፡፡ ከዚህ ሌላ የስራ ማስካሄጃ የሌላቸዉ በመሆኑ ወጭ የሚጠይቁ ስራዎችን ለማከናወን የማይችሉ በመሆኑ ችግሮችን የሚያባብስ ሁኗል፡፡ እንዲሁም ለጥበቃ ስራ የሚያስፈልጉ፣ በቂ የጦር መሣሪ፣ የጥበቃ አልባሳት፣ ጫማ፣ የጥበቃ ካምፕ ወዘተ የሚያገኙበት ሁኔታ አለመኖር ችግር እየፈጠረ ይገኛል፡፡

8.3.6. የየጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም

ከዳሰሳ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክትው የየጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን ተፈጥሮዊ ይዘቱ የሚያመዝን ሲሆን ዛሬ በአገሪቱ ዋነኛ የደን ሽፋን መገለጫ ነው የሚባለውን የሃረና ደን፣ የደንቆሮ ጫካን፣ እረጃጅምና ግዙፍ ዛፎች የሚገኙበትን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያንና በክልላችን ደግሞ የወፍ ወሻ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራን ሊወክል የሚችል ስርዓተ ምህዳር በመሆኑ ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ቢደረግለት ለዱር እንስሳት ደህንነት፣ ለሥርዓተ-ምህዳር ጥበቃና ለቱሪዝም ከሚሠው

ጥቅም ባሻገር ለትምህርትና ለበርካታ ሣይንሣዊ ምርምሮች በሚኖረው አስተዋጽዖ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን የሚገባው ደን ነው፡፡

1. ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች

የአለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት /IUCN/ ለጥብቅ ስፍራነት ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የጎፍ ጥብቅ የመንግስት ደን ጥብቅ ስፍራ እንዲሆን የሚያስችለውን ነጥቦች የሚያሟሉ የተፈጥሮ ዕፅዋትና የዱር እንስሣት ማዕከል እንደሆነ በሚከተለው ሁኔታ ተዘርዝረዋል፡፡

1. ***<u>መካይ የሆነ ስነምህዳር (Representativeness):-</u>*** የየጎፍ የመንግስት ጥብቅ ደን በዋናነት በደረቅ ሞንታኔ ስርዓተ ምህዳር (Dry Evergreen Montane Forest) ይጠቃለላል፡፡ ይህ ስርዓተ ምህዳር ለክለት የተጋለጠ (Fragile Land) እና ጥበቃን የሚሻ ሥርዓተ ምህዳር ነው፡፡ የየጎፍ ደን አሁን የያዘውን ገፅታ እንዲይዝ ያስቻለው ከ1965 እስከ 1976 ዓ.ም አካባቢውን ከሰውና ከእንስሳት ተዕዕኖ በመጠብቅ የደን ተከላ ከተካሄደበት በኋላ ነው፡፡ ከእነዚያ ሁሉ ዓመታት ጥበቃና ልፋት በኋላ ቦታው ወደ ተፈጥሮዊ ሁኔታው እየተመለሰ ይገኛል፡፡ ይህ በመሆኑም የጎፍ በሃገራችን ብቻ ከሚገኙ ታላላቅ አጥቢዎች ሁለቱን (የጭላዳ ዝንጀሮና የሚኒልክ ድኩላ) አቅፎ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም በአደጋ ላይ ያለችውና በሀገራችን ብቻ የምትገኘው የሶረኔ ቆቅ የጥበቃ ሽፋን ልታገኝ የምትችለው በእዚህ አካባቢ ጭምር ነው፡፡ የጎፍ በሰው ልጅ ጥረት ወደ ተፈጥሮዊ ሁኔታው የተመለሰ ደን በመሆኑ በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ላይ ላሉና ወደ ተፈጥሮዊ ይዘታቸው መመለስ ለሚኖርበቸው አካባቢዎች እንደ ሰርቶ ማሳያ (Role Model) ሊወሰድ የሚችልን ስርዓተ ምህዳር የሚወክል ደን ነው፡፡ በአገራችንም ሆነ በክልላችን እንዲህ ባለ ተመሳሳይ ስርዓተ ምህዳር መሬቶች ተፈጥራዊ የብዝሃ-ሕይወት ገጽታቸው ሙሉ ለሙሉ ተቀይሮ ለግብርና ስራ የዋሉ ሲሆን የየጎፍ ደን ግን በሰው ልጅ ጥረት ወደ ተፈጥሮዊ ይዘቱ እየተመለሰ በመሆኑ ወካይነቱ የጎላ ነው፡፡ በተለይም በአማራ ክልል በተመሣሣይ ስርዓተ ምህዳር የዚህ ዓይነት የእጽዋትና የደን ስብጥር በዚህ ሁኔታ ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ የየጎፍ ደን ጥብቅ ስፍራ ሊሆን ይገባል፡፡

2. ***<u>የብዝሃ ህይወት ክምችት (Diversity):-</u>*** ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በውስጡ ከ29 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሣት፣ ከ75 በላይ የአዕዋፍት ዝርያዎችና ከ85 በላይ የተለያዩ የእፅዋት ዝርያዎችን ያቀፈ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 2 ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት፣ የሶረኔ ቆቅን ጨምሮ 4 አዕዋፍትና 3 የእፅዋት ዝርያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡
3. ***<u>ማራኪና ለየት ያለ የተፈጥሮ ገፅታ (Distinctiveness):-</u>*** የጎፍ ቀደም ሲል በሰው ተዕዕኖ ምክንያት ተፈጥሮዊ ይዘቱን እንዲያጣ ቢደረግም ከ1965 ዓ.ም ጀምሮ በተደረገው ጥረት ግን ወደ ተፈጥሮዊ ሁኔታው እየተመለሰ ያለ ደን በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ሌላው ደኑን ልዩና ማራኪ የሚያደርገው ከዳር ወደ ውስጥ ሲገባ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድና የደኑ ክፍተኛ ቦታ (3000 ሜ) ከመሃል ላይ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ደኑ የኮምቦልቻን ከተማ ከ8 ኪ.ሜ ርቀት እንዲሁም አጠቃላይ የደኑን ክልል በቀላሉ ለማየት የሚያስችል ሲሆን በዙሪው ላሉት ወንዞችና ምንጮች መገኛ በመሆን እንደ ተፋሰስ አናት ሆኖ ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም በውስጡ ለጥናትና ምርምር የሚገለግሉ የተለያዩ ዕፅዋትንና ብርቅ የዱር እንስሳትን ይሏል፡፡ እነዚህም በራሳቸው የቦታውን ማራኪነት የሚያጎሉ የተፈጥሮ ስጦታዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህንን ስርዓት ምህዳር ባለበት ሁኔታ በመጠበቅና ተፈጥሮዊ ውበቱን በማጉላት ከቱሪዝም የሚገኘው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም ህገ-ወጥ በሆነ መልኩ በእዚህ አካባቢ የሚከናወኑ ተግባራትን በመከላከልና በመቆጣጠር፣ ደኑን ጥብቅ ስፍራ በማድረግ መጠበቅና ማልማት በአስከፊ ሁኔታ እየተሰፋፉ ያሉ ህገ ወጥ የደን ጭፍጨፋዎችን፣ እርሻዎችንና ሰፈራዎችን የሚገታና የሚስቀር ነው፡፡

4. ***<u>ሰነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ (Ecological Importance)፦</u>*** የአካባቢውን ብዝሃ ህይወት የአፈር ለምነት የውሃና አየር ሁኔታ ተሻሽሎና ተስተካክሎ እንዲኖር ያደርጋል። በታሳቢ ጥብቅ ስፍራውና በአካባቢው እርጥብና ደረቅ ሞንታኔ ሰርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል። በአካባቢው ያለውን ያልተስተከከለ የዝናብ ሥርጭት የተስተካከለ እንዲሆን በእጅጉ ያግዛል፡ አካባቢያዊ ውበትን ይጨምራል፣ ማራኪ የሆነ ገፅታ ይኖረዋል። ይህ አካባቢ በክልሉ ውስጥ ለመጥፋት የተቃረቡትን ኮሶ፣ ዝግባና የወይራ ዛፎችን ተፈጥሮዊ በሆነ ገፅታቸው ለመጠበቅ ያስችላል። በውስጡ የሚኖሩ የዱር እንስሳትና እፅዋት በዓይነትም ሆነ በብዛት በተፈጥሮዊ አኗኗራቸው ተጠብቀው፣ ተደጋግፈውና ተመጣጥነው እንዲኖሩ ያስችላል። በአካባቢው የምነጮች፣ወንዞችና ጅረቶች ፍሰት የተስተካከለና አስተማማኝ እንዲሆን የደርጋል።

5. ***<u>በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ላይ እየደረሱ ያለ አሉታዊ ተፅዕኖዎች /</u>***Degree of interference/

1. በታሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች አጐራባች ያሉ ቀበሌዎች መሬት በአፈር ክለት ምክንያት የአፈር ለምነቱን ያጣ በመሆኑና ምርታማነቱም ዝቅተኛ በመሆኑ ተጨማሪ የእርሻ መሬት ለማግኘ ት ከፍተኛ የእርሻ መሬት መስፋፋት መከሰቱ፣
2. ታሣቢ ጥብቅ ስፍራዎች በሰፈራና በእርሻ የተቆራረጡና የተጣበቡ በመሆናቸው ለዱር እንስሳት እንቅስቃሴ አስቸጋሪ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ (1ኛ. ደሴ ዙሪያ ወረዳ 012 ቀበሌ ጭቃ በረት ጎጥ አካባቢ ያለ እርሻ፣ 2ኛ. ደሴ ዙሪያ ወረዳ 040 ቀበሌ ወፍ ከሌ መንደር አካበቢ፣ 3ኛ. በደሴ ዙሪያ ወረዳ ቀበሌ 09 እና 041 የሆኑ በደኑ ወስጥ ያሉ 8 መንደሮች)፣
3. ለጣውላ ስራ ከፍተኛ የደን ጭፍጨፋ ያለ መሆንና ይህም በአካባቢውም ላይ ተፅዕኖ የሚያደርስ መሆኑ፣
4. የየጎፍ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ አብዛኛው ቦታ በመንደርና በእርሻ የተከበበ ስለሆነ ጥብቅ ስፍራው ላይ የሚኖረውን ጫና ለመቀነስ የሚያስችል ሊከለል የሚችል የወል መሬት ስለሌለው ለጥበቃው አስቸጋሪ መሆኑ፣
5. ለጥቅም የደረሱ ዛፎች ቢወገዱ በአጠቃላይ በአካባቢው ሚዛናዊ ስርዓተ ምህዳር (Ecosystem Balance) ላይ የሚያመጡትን የአካባቢ ተፅዕኖ (Environmental Impact) በማጥናት፣ የማኔጅመንት ፕላንና ዝርዝር የአጠቃቀም ስልት በማዘጋጀት መሬቱንና በውስጡ ያሉትን የዱር እንስሳት ተፈጥሮዊ ደህንነት በማይጎዳ መንገድ ደኑን መጠቀም ባለመቻሉ ምክንያት በርካታ ሰዉ ሰራሽ ደኖች አርጅተዉና ጥቅም ከሚሰጡበት ደረጃ አልፈዉ ወድቀውና በስብሰው መታየት፣

6. ደኑ የደሴ ዙሪያ ወረዳን ጨምሮ 5 (ቃሉ፣ ኮቦልቻ ከተማ፣ ደሴ ከተማ፣ አልብኮና ደሴ ዙሪያ) ወረዳዎች የሚያዋስኑት ቢሆንም ለጥበቃ ስራው ኃላፊነት የተሰጠው የደሴ ዙሪያ ወረዳ ብቻ መሆኑና ሌሎቹ ወረዳዎች ለጥበቃ ስራው ትኩረት አለመስጠታቸው፣

6. ***<u>የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ</u>*** /Scientific and monitoring uses/፦-የዱር እንስሳትንና ዕፅዋትን የተፈጥሮ አካባቢያቸውን ለማጥናት በሞዴልነት ያገለግላል። የዱር እንስሳት በሽታ ክስተትንና በቤትና በዱር እንስሳት መካከል ያለውን ስፍርጭት ለማወቅ ያግዛል። ለአካባቢ ክትትል በሚኖረው ጠቀሜታ የተፈጥሮ ሚዛን ለውጥን ለመለካት ያስችላል። የዱር እፅዋት ናሙናና ተፈጥሮዊ ዕድገትንና በሰዎች ጣልቃ ገብነት የሚመጣውን ለውጥ ለመለካት ያስችላል።
7. ***<u>የቦታ ሰፋት</u>*** /area size/፦ ታሳቢ ጥብቅ ቦታው በጥብቅ ስፍራነት ተመዝግቦ በውስጡ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለመያዝ ቢያንስ አንድ ሽህ ሄክታር መጠበቅ ይኖርበታል የሚለውን የ IUCN መስፈርት የሚያሟላና ከ13000ሄ/ር በላይ የሚሸፍን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙትን የሚኒልክ ድኩላ፣ጭላዳ ዝንጀሮ፣ የሶረኔ

ቆቅ፣ ግንደ ቁርቁር፣ አቢስኒያን ሎንግ ክሎው እና የአበሻ ድመት መሳይ አዕዋፋት መኖሪያ ነው ::

8. ***ቅርጽ (መጠነ ዙሪያ)*** /shape/፡- ጥብቅ ስፍራዎች በሚቋቋሙበት ጊዜ በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መጠነ ዙሪያ እንዲኖራችው ይጠበቃል፡፡ ከዚህ አንፃር በየጎፍ እና በሐረጎ መካከል ካለው ረጅም ሰንሰለታማ ኮረብታ በስተቀር ደኑ መጠነ ዙሪያው ላይ ወጣ ገባነት የበዛበት አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ከፍታው ከዳር ወደ መሃል እየጨመረ የሚሄድና ዙሪያውን በእርሻ መሬትና መንደር የተከበበና በተለይም በየጎፍ አካባቢ ቅርፁ ወደ ክብነት የተጠጋና ዋናው ደን በገደልና በተራራዎች ላይ የሚገኝ በመሆኑ ለቁጥጥርና ጥበቃ አመችነት አለው፡፡
9. ***በውስጡ የሚገኙ ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች*** /Endemicity/ ፡- ከታላላቅ አጥቢዎች ውስጥ የሚኒልክ ድኩላና ጭላዳ ዝንጀሮ፣ ከአእዋፋት መካከል የሶረኔ ቆቅ፣ ግንደ ቁርቁር፣ አቢስኒያን ሎንግ ክሎው እና የአበሻ ድመት መሳይ አዕዋፋት፣ እንዲሁም አዕዕዋት መካከል ደግሞ አስታ፣ ወይራ፣ ዝግባ የአበሻ ዕድ፣አምኃ የሚገኙበት በመሆኑ ጥብቅ ስፍራ ሊሆን ይገባል፡፡

2. ታሳቢ ጥብቅ የሚኖረው ጠቀሜታ

1. **ስርዓተ ምህዳራዊ ጠቀሜታ** (Ecosystem values)፡-ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ያላቸው ግብግብ ዘለቄታዊ የተፈጥሮ ገፅታ መኖርን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ ያስችላል፡፡ በዚህም ዘለቄታዊ ጥቅም አለው፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ እና በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡ ለመጥፋት የተቃረቡትን ኮሶ፣ ዝግባና የወይራ ዛፎችን ተፈጥሮዊ በሆነ ገፅታቸው ለመጠበቅ ያስችላል፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሚዛኑን ጠብቆ እንዲኖር ያስችላል፡፡ የአካባቢው የአየር ሚዛን እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡ በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሣትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት ይጠበቃሉ፡፡ በተለይም በአገራችን ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት ባሉበት ሁኔታ ተጠብቀው እንዲኖሩና እንዳይጠፉ ያደርጋል፡፡ ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚወጡ ምንጮችና ጅረቶች ዓመቱን በሙሉ እንዲፈሱ ስለሚያስችል የተስተካከለ የውሃ ሃብት እንዲኖር ያደርጋል፡፡
2. **ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ** (Economical values)፡-በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከጐብኝዎችጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ ገቢዎች ለህብረተሰቡና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጥበቃ ሠራተኝነትና በተፈቀደ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ በመሣተፍ የአካባቢው ህብረተሰቡ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ በታሳቢው ጥብቅ ስፍራ ደጀን አካባቢ ለሚካሄዱ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ሰለዘላቂ የአካባቢ ጥበቃና ልማት ጠቀሜታና አስፈላጊነት ትምህርት ይሰጣል፡፡ ከምርምርና ሣይንሣዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፡፡ የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴ ስለሚስፋፋና ስለሚጠናከር ለአካባቢው ህብረተሰብ አማራጭ የገቢ ምንጭ ይሆናል፡፡ የአካባቢው የአየር ሚዛን ስለሚስተካከልና ስለሚጠበቅ ከእርሻ ስራ የሚገኘው ገቢ ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል፡፡ በሆቴልና በሌሎች መስተንግዶ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ለቱሪስቶች አግልግሎት በመስጠት በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ኑሮቸውን እንዲያሻሽሉ ያግዛል፡፡
3. **ማህበራዊ ጠቀሜታ** (Social values)፡-አለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህል ልውውጥ እንዲኖር ያስችላል፡፡ ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጋር ተያይዞ በአካባቢው የመሠረተ ልማቶች መስፋፋት ስለሚኖር ት/ቤት፣ የኢኮ-ቱሪዝም ማህበራት መደራጀት፣ የሰውና የእንስሳት ጤና ኬላዎች ግንባት ወዘተ ይኖራል፡፡
4. **ሳይንሳዊ ጠቀሜታ** (Scientific values)፡-የዱር እንስሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈጥሮዊ አኗኗሯቸው ለሚደረግ ምርምር በማዕከልነት ያገለግላል፡፡ የባህላዊ መድኃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሳይንሳዊ ጥናትም ለማከሄድ

ይረዳል፡፡ በመጥፋት ላይ ላሉ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት ሳይንሳዊ ምርምር ሊደረግ ይችላል፡፡ የተፈጥሮ ደኑና ገፅታው ለአካባቢያዊ ደህንነት፣ ለብዝሃ ህይወትና ለስርዓተ ምህዳር መስተካከል ያላቸው አስተዋፅዖ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ ለሚደረጉ ምርምሮች የመስክ ላቦራቶር ሊሆን ይችላል፡፡

5. **የተፈጥሮዊነት ጠቀሜታ** (Naturalness)፡-ምንም እንኳን አካባቢው ከሰው ልጆች ተፅዕኖ ነፃ ባይሆንም በአንፃራዊነት ከአካባቢው የተሻለ በመሆኑ ተፈጥሮዊነትን ጠብቆ ለማቆየት ያስችላል፡፡ በውስጡ ያሉትን ብዝሃ ሕይወትና ሌሎች (አፈር፣ ውሃና የመሬት አቀማመጥ) በተፈጥሮዊ ገፅታቸው ቆይተው ዘለቄታዊነት ባለው መልኩ ጥቅም እንዲሰጡና ተፈጥሮዊ ይዘታቸው እንዳይጓደል ይረዳል፡፡
6. **የመስህብነት ጠቀሜታ** (Aesthetic values)፡-አካባቢው የሰው ልጆችን ቀልብ ሊገዙ የሚችሉ መመልከቻ ቦታዎችና ማራኪ ገፅታዎች የያዘ ሲሆን ከእነዚህም ቦታዎች ውስጥ እንደ ሐረጎ፣ የጎፍ ቁንዲ ወዘተ የመሳሰሉ የመመልከቻ ታራራዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ አካባቢዎች እራሳቸው ማራኪ ከመሆናቸው ባሻገር የደኑን ስብጥርና ሽፋን እንዲሁም የብዝሃ ህይወት ክምችት ለመቃኘት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ በተፈጥሮ ይዘቱ ለጎብኝዎች ማራኪ የሆነ መዝናኛና እርካታ ሊሰጡ የሚችሉ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች ያሉበት ነው ማለት ይቻላል፡፡

የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና

የጎፍ የመንግስት ጥብቅ ደን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለውና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ከተጠበቀ የሚሰጣቸው ጠቀሜታዎች አካባቢያዊ፣ አገራዊና ዓለማቀፋዊ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም ያለው የደን ሽፋንና መልካምድራዊ አቀማመጥ የብዝሃ ህወትና ተፈጥሮዊ ገፅታ ከመጠበቅ አልፎ የዓለም ሙቀትንና የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ የጎላ እሰተዋፅዖ ይኖረዋ፡፡

ስለሆነም የተፈጥሮ ደኑ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን የሚሰጠውን ጠቀሜታ (Values) በIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች (Quality Criteria) ጋር በማነፃፀር የቦታውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የተቀመጠው ሰንጠረዥ የየጎፍ ደን የሚሰጠውን ጠቀሜታ ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች ጋር በማነፃፀር ሊጠበቅ የሚገባወን ደረጃ (Protected Area Category) ለመወሰን ያስችላል፡፡ ይህም የመመዘኛ መስፈርቶች በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ያመላክታል፡፡

ሠንጠረዥ 6፡ የጎፍ የመንግስት ጥብቅ ደን ጠቀሜታና ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መመዘኛ መስፈርቶች ንፅፅር

	ውሀይነት	ብዝሃ ህይወት	ልዩ መለኮቻ	ለነ ምህዳራዊ ጠቀሜታ	በአካባቢው ላይ ሀላ ፊና መጠን	የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	የቦታ ስፋ	ቁርፅ (መጠነ ዙሪያ)	ባርቅነና ተፈጥሮአዊ ቅቅሉኔ	ደረጃ
ስርዓተ ምህዳራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ዝ	ከ	ዝ	ከ	ከ	67%
የተፈጥሮዊነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ከ	89%
ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ከ	78%
ማህበራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	78%
ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100%
የመስህብነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ከ	89%
ደረጃ	100%	100%	89%	44%	22%	100%	89%	100%	89%	83.5%

መግለጫ፡ ከ፡- ከፍተኛ 1-2 ችግሮችና የሚያሟላቸው ነጥቦች ካሉ

ዝ፡- ዝቅተኛ ከሁለት በላይ ችግሮችና የማያሟላቸው ነጥቦች ካሉ

አንድ የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ቦታው ጥብቅ ስፍራ ቢሆን የሚሰጠው ጠቀሜታ (Values) በIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች (Quality Criteria) ጋር ሲነፃፀር ቢያንስ 75 ከመቶ በላይ ውጤት ማሳየት ይኖርበታል፡፡ ከሠንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው ንፅፅሩ ወደ ጎንም ሆነ ወደ ታች በአብዛኛው 75 ከመቶ በላይ የሚያሳይ በመሆኑ የተፈጥሮ ደኑ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም እንዳለው ያመላክታል፡፡

8.3.7. የየጎፍ የመንግስት ጥብቅ ደን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ የመሆን ዋና ዓላማ

የተፈጥሮ ደኑ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ባለው የብዝሃ ህይወት ሃብት፣ ከሚሰጠው ጠቀሜታና በIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባው መስፈርቶች (Quality Criteria) አንፃር ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጅ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በIUCN የጥብቅ ስፍራዎች ደረጃ (protected area category) መሰረት የትኛውን ምድብ (Protected area category I-VI) ሊያሟላ እንደሚችል እና የጥብቅ ስፍራውን የመጀመሪያ ደረጃ ዓለማዎች (Primary management objectives) መለየትና መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ለውሳኔ ያመች ዘንድ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በየትኛው ደረጃ ሊመደብ እንደሚችል ያሉ አማራጮች (possibilities) በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት ተመላክቷል፡፡

Table 7 Matrix for protected area categories and Management objectives (IUCN, 1994)

No.	Management categories	IUCN protected area categories							Total (%)
		Ia	Ib	II	III	IV	V	VI	
		Strict natural reserve	Wilderness area	National Park	Natural Monument	Habitat/Species Management Area	Protected Landscape/Seascap	Managed Resource Protected Area	
1	Scientific research	3	2	3	1	2	1	2	22
2	Wilderness	2	3	2	0	0	0	0	11
3	Preservation of species and genetic diversity	2	3	3	2	2	2	2	22
4	Maintenance of environmental services	0	0	3	2	2	2	2	11
5	Protection of species, natural /culture features	2	3	3	3	3	2	2	44
6	Tourism and recreation	0	0	3	2	2	2	2	11
7	Education	2	2	3	1	2	1	2	11
8	Sustainable use of resources from natural ecosystems	0	0	1	0	1	2	3	11
9	Maintenance of natural/cultural/traditional attributes	0	2	3	3	1	3	2	33
	Total (%)	11	33	77	22	11	11	11	

Note: 3= Primary management objective, 2= Secondary management objective, 1=potentially applicable objectives, 0=Not Applicable

አንድ የተፈጥሮ ደን በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (protected area category) እንደሚመደብ ለመወሰን ደኑ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ማሳካት ያለበትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎችን (Primary management objective) በመለየትና በማወቅ መሆን ይኖርበታል። ሠንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው ደኑ በደረጃ ሁለት (protected area category II) መሰረት ጥብቅ ስፍራ ቢሆን በተራ ቁጥር 2 እን 8 ከተቀመጡት የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች በስተቀር ሁሉንም የሚያሳካ ይሆናል። ስለዚህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን

በብሄራዊ ፓርክ ደረጃ ማቋቋም ይቻላል። ይሁን እንጅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በአሁኑ ወቅት ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመፍታት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እና ቦታው ህጋዊ ዕውቅና እስኪያገኝ ድረስ በአግባቡ ማስጠበቅ ይገባቸዋል። ስለዚህ በተፈጥሮ ደኑ ላይ እየተፈፀሙ ያሉ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ እስከተቻለ ድረስ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚከተሉትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች (Primary management objective) የሚያሳካ ይሆናል።

- **ለብዝሃ ህይወትና ስርዓተ ምህዳር ጥበቃ**፡ የደረቅና እርጥብ ሞንታኔ ስርዓተ ምህዳር ውስጥ በሚገኘው የብዝሃ ህይወት ሃብት የዘቦታ ልማትና ጥበቃ ለማካሄድ የሚያስችል የዕጽዋትና እንሰሳት ስብጥር በማልማትና በመጠበቅ ለተተኪ ትውልደ ማስተላለፍ፣
